ኦሪት ዘፍጥረት

መግቢያ

ኦሪት ዘፍጥረት ስለ ዓለማት አፈጣጠር ፥ ስለሰው ዘር አመጣጥ ፥ ስለ ኃጢአትና የሥቃይ ኑሮ እጀማመርና እግዚአብሔር ከሰው ዘር ጋር ስለአለው ግንኙነት ይናገራል ፥ ኦሪት ዘፍጥረት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደብ ይችላል ፦

1. ከምዕራፍ 1 እስከ 11 ፦ ስለ ዓለም አፈጣጠርና ስለ ሰው ዘር ቅድመ ታሪክ ይናገራል ፥ የአዳምና የሔዋን ፥ የቃየልና የአቤል ፥ የኖኅና የጥፋት ውሃ ፥ እንዲሁም የባቤል ግንብ ታሪክ የሚገኘው በዚህኛው ክፍል ነው ።
2. ከምዕራፍ 12 እስከ 50 ፦ ይህ ክፍል ስለ እስራኤላውያን ቅድመ አባቶች ታሪክ ይናገራል ፥ ከእነርሱም መካከል የመጀመሪያው በእምነቱና ለእግዚአብሔር በነበረው ታማኝነት ታዋቂ የነበረው አብርሃም ነው ፥ ከዚያም የልጁ የይስሐቅ ፥ የልጁም ልጅ የነበረው የያዕቆብና ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ታሪክ ይከተላል ፥ እነዚህም ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ፥ በሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶችን የመሠረቱ ናቸው ፥ ከእነዚህም ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ልጆች መካከል በተለይ ዮሴፍ ላይ ፥ እንዲሁም ፥ ያዕቆብንና የቀሩት ልጆቹን ከነቤተሰባቸው ወደ ግብጽ ባመጣው ሁኔታ ላይ ያተኮራል ።

ምንም እንኳ ይህ መጽሐፍ ስለሕዝቦች ታሪክ የሚናገር ቢሆንም ከሁሉ በላይ የሚቀርበው እግዚአብሔር ስላደረገው ሥራ ነው ፥ እግዚአብሔር ዓለማትን የመፍጠሩን ታሪክ መናገር ይጀምርና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ማስቡን እንደማያቋርጥ የሚያመለክተውን ተስፋ በመግለጥ ይፈጸርሳል ፥ በመጽሐፉ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ዋናው ባለ ታሪክ ስሕተት በሚፈጽሙት ላይ ፍርድና ቅጣት የሚያስተላልፈው ፥ ሕዝቡን የሚመራውና የሚረዳው ፥ የታሪካቸውንም ሂደት የሚያስተካክለው ራሱ እግዚአብሔር ነው ። ይህ ጥንታዊ መጽሐፍ የተጻፈው የሕዝቦችን እምነት ለማሰፈርና ያንንም እምነት ሕያው ሆኖ እንዲኖር ለማድረግ ነው ።

ምዕራፍ 1

የዓለም አፈጣጠር ታሪክ

1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። 2 በዚያን ጊዜ ምድር ቅርጽ የሌላትና ባዶ ነበረች ፥ ጨለማም በጥልቁ (ውቅያኖስ) ላይ ነበር ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃው ላይ ይሰፍ ነበር ።

3 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ብርሃን ይሁን" አለ ፥ ብርሃንም ሆነ ። 4 እግዚአብሔርም ፥ ብርሃን መልካም ነገር መሆኑን ተመለከተ ፥ ስለዚህም እግዚአብሔር ብርሃንን ከጨለማ ለየ ። 5 ብርሃኑን "ቀን" ብሎ ጠራው ፥ ጨለማውንም "ሌሊት" ብሎ ሰየመው ። ቀኑ መሸ ፥ ሌሊቱም ነጋ ፥ ይህም መጀመሪያ ቀን ሆነ ።

6 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ውሃውን ከውሃ የሚለይ ጠፈር ይሁን" አለ ፥ 7 በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ጠፈርን ፈጠረ ፥ ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር "ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉት ውሆች ይለያዩ" አለ ፥ እንዳለውም ሆነ ። 8 እግዚአብሔር ጠፈርን "ሰማይ" ብሎ ጠራው ። ቀኑ መሸ ፥ ሌሊቱም ነጋ ፥ ይህም ሁለተኛ ቀን ሆነ ።

9 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "የብሱ ግልጥ ሆኖ እንዲታይ ከሰማይ በታች ያለው ውሃ ሁሉ በአንድ ሰፍራ ይሰብሰብ" አለ ፥ እንዳለውም ሆነ ። 10 የብሱን "ምድር" ብሎ ጠራው ፥ በአንድ ሰፍራ የተሰበሰበውንም ውሃ "ባሕር" ብሎ ሰየመው ፥ እግዚአብሔርም ይህ መልካም መሆኑን ተመለከተ ። 11 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ምድር አትክልትን ፥ የእህል አዝርእትንና ዘር በውስጡ ያለውን ፍራፍሬ የሚያስገኙ ተክሎችን በየዐይነቱ ታብቅል" አለ ፥ እንዳለውም ሆነ ። 12 በዚህ ዐይነት ምድር አትክልትን ፥ በየዐይነቱ የእህል አዝርእትንና ዘር በውስጡ ያለውን ፍራፍሬ የሚያስገኙ ተክሎችን አበቀለች ፥ እግዚአብሔርም ይህ

1:3 ፦ 2ቆሮ. 4:6 ። 1:6-8 ፦ 2ጴጥ. 3:5 ።

መልካም መሆኑን ተመለከተ ። 13 ቀኑ መሸ ፥ ሌሊቱም ነጋ ፤ ይህም ሦስተኛ ቀን ሆነ ።

14 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ቀንን ከሌሊት ለመለየት ልዩ ልዩ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ላይ ይሁኑ ፤ ለዕለታት ፥ ለክፍላተ ዓመት ና ለዓመታት መለያ ምልክት ይሁኑ ፤ 15 ለም ድር ብርሃን ለመስጠት በሰማይ ጠፈር ላይ ሆነው ያብሩ" አለ ፤ እንዳለውም ሆነ ። 16 በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን ፈጠረ ፤ ታላቁ ብርሃን ፀሐይ በቀን ፥ ታናሹ ብርሃን ጨረቃ በሌሊት እንዲያበሩ እደ ረገ ፤ እንዲሁም ከዋክብትን ፈጠረ ፤ 17 እነዚህን ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ላይ እየራቸው ፤ ይህን ንም ማድረጉ ለምድር ብርሃንን እንዲሰጡ ፥ 18 በቀንና በሌሊት ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸ ውና ጨለማን ከብርሃን እንዲለዩ ነው ። እግዚአ ብሔርም ይህ መልካም መሆኑን ተመለከተ ። 19 ቀኑ መሸ ፥ ሌሊቱም ነጋ ፤ ይህም አራተኛ ቀን ሆነ ።

20 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ውሃ ሕይወት ባላቸው በልዩ ልዩ ፍጥረቶች የተሞላ ይሁን ፤ ወፎችም ከምድር በላይ ባለው በሰማይ ጠፈር ይብረሩ" አለ ። 21 በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ታላላቅ የባሕር አውሬዎችን ፥ ሌሎችንም በውሃ ውስጥ የሚኖሩና የሚንቀሳቀሱ ልዩ ልዩ ፍጥረቶ ችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ወፎችን ፈጠረ ። እግዚ አብሔርም ይህ መልካም መሆኑን ተመለከተ ። 22 እግዚአብሔር "ብዙ ተባዙ ፤ ዘራችሁ የባሕ ርን ውሃ ይሙላ ፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ" ብሎ ባረካቸው ። 23 ቀኑ መሸ ፥ ሌሊቱም ነጋ ፤ ይህም አምስተኛ ቀን ሆነ ።

24 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ምድር ልዩ ልዩ የሆኑ ሕይወት ያላቸው ፍጥረቶችን ፥ ማለ ትም ልዩ ልዩ የሆኑ እንስሳትን ፥ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችንና አራዊትን ታስገኝ" አለ ፤ እንዳለውም ሆነ ። 25 በዚህ ዐይ ነት እግዚአብሔር አራዊትን በየዐይነቱ ፥ እንስ ሳትን በየዐይነቱ ፥ በምድር ላይ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችን በየዐይነቱ ፈጠረ ። እግዚአብሔርም ይህ መልካም መሆኑን ተመለከተ ።

26 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ሰውን በመል ካችንና በአምሳያችን እንፍጠር ፤ ሰዎችም በባ ሕር ውስጥ በሚኖሩ ዓሣዎች ፥ በሰማይ በሚ በሩ ወፎች ፥ በእንስሳትና በምድር ላይ በደረታ ቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች ፥ እንዲ ሁም በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ ።

27 በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክና በራሱ አምሳያ ፈጠረው ፤ እግዚአብ ሔር ሰዎችን ሲፈጥራቸው ወንድና ሴት እድ ርጎ ነው ። 28 እግዚአብሔርም "ብዙ ተባዙ ፥ ዘራችሁ ምድርን ይሙላ ፥ ምድርም በቁጥጥራ ችሁ ሥር ትሁን ፤ በባሕር ውስጥ በሚኖሩ ዓሣ ዎች ፥ በሰማይ በሚበሩ ወፎችና በምድር ላይ በሚንቀሳቀሱ ሕያዋን ፍጥረቶች ሁሉ ላይ ሥል ጣን ይኑራችሁ" ብሎ ባረካቸው ። 29 እግዚአብ ሔር እንዲህ አለ ፤ "ምግብ እንዲሆኑአችሁ በምድር ገጽ ላይ የሚገኙትን የእህል እዝርእት ንና ዘር በውስጡ ያለውን ፍራፍሬ የሚያበጉ ተክሎችን ሁሉ ሰጥቻችኋለሁ ። 30 እንዲሁም በምድር ላይ ለሚኖሩ እንስሳት ሁሉ ፥ በሰማይ ለሚበሩ ወፎች ሁሉ ፥ በምድር ላይ ለሚንቀሳ ቀሱ ሕያዋን ፍጥረቶች ሁሉ ፥ በእጠቃላይ የሕ ይወት እስትንፋስ ላለው ፍጥረት ሁሉ ምግብ እንዲሆናቸው ልምላሜ ያለውን ግርና ቅጠል ሁሉ ሰጥቻቸዋለሁ ።" እንዳለውም ሆነ ። 31 እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ አየ ፤ እጅግ መልካም መሆኑንም ተመለከተ ። ቀኑ መሸ ፥ ሌሊቱ ነጋ ፤ ይህም ስድስተኛ ቀን ሆነ ።

ምዕራፍ 2

1 የሰማይና የምድር ፥ በውስጣቸው ያሉትም ነገሮች ሁሉ አፈጣጠር በዚህ ሁኔታ ተፈጸመ ።

2 እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ሥራውን ሁሉ ፈጽሞ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ ። 3 እግዚአ ብሔር የመፍጠር ሥራውን ሁሉ ፈጽሞ ያረ ፈው በዚህ ቀን ስለሆነ ስባተኛውን ቀን ባረ ከው ፤ ቀደሰውም ። 4 እንግዲህ ሰማይና ምድር በተፈጠሩ ጊዜ የእፈጣጠራቸው ታሪክ ይህ ነበር ፤

አዳምና ሔዋን በዔደን ገነት

እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን በፈ ጠረ ጊዜ ፥ 5 ገና ምን ባለማዝነሙና ምድርንም የሚያለማ ሰው ባለመኖሩ ፥ በምድር ላይ ምንም ዐይነት ተክል አልነበረም ፤ ምንም ዐይነት ቡቃያ አልበቀለም ። 6 ይሁን እንጂ ከምድር ውስጥ የሚመነጭ ውሃ የብሱን ያጠጣ ነበር ።

7 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ከመ ፌት ዐፈር ወስዶ ፥ ሰውን ከዐፈር እበጀው ፤ በአፍንጫውም ሕይወትን የሚሰጥ እስትንፋስ "እፍ" አለበት ፤ ሰውም ሕይወት ያለው ፍጡር ሆነ ።

8 እግዚአብሔር አምላክ በስተምሥራቅ በኩል በዔደን የአትክልት ቦታን አዘጋጀ ፤ የፈጠረውንም ሰው በዚያ እንዲኖር አደረ ገው ። 9 በዚያም ለዐይን የሚያስደስቱና ለም ግብነት የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ዛፎች እንዲበ ቅሉ አደረገ ፤ ደግሞም በአትክልቱ ቦታ

1:26 ፦ 1ቆሮ. 11:7 1:27 ፦ ማቴ. 19:4 ፤ ማር. 10:6 ። 1:27-28 ፦ ዘፍ. 5:1-2 ። 2:2 ፦ ዕብ. 4:4 ፤ 10 ። 2:2-3 ፦ ዘፀ. 20:11 ። 2:7 ፦ 1ቆሮ. 15:45 ። 2:9 ፦ ራእ. 2:7 ፤ 22:2 ፤ 14 ።

መካከል ሕይወት የሚሰጥ ዛፍ ነበረ፥ እንዲ
ሁም ደኑን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል
ዕውቀት የሚሰጥ ሌላ ዛፍ ነበረ።
10 የአትክልት ቦታውን የሚያጠጣ ወንዝ
ከዔደን ይፈስ ነበር፥ ይህም ወንዝ ከዔደን
ከወጣ በኋላ በአራት ወንዞች ይከፈላል። 11 የመ
ጀመሪያው ወንዝ ፈሾን ይባላል፤ እርሱም
ወርቅ በሚገኝበት ሐዊላ በሚባለው ምድር
ሁሉ ላይ ይፈስሳል፥ 12 የዚያ አገር ወርቅ
ንጹሕ ነበር፤ በተጨማሪም በዚያ አገር ውድ
የሆነ ሽቶና የከበሩ ድንጋዮች ይገኛሉ። 13 ሁለ
ተኛው ወንዝ ግዮን ይባላል፤ እርሱም ኢትዮ
ጵያ በምትባል አገር ዙሪያ ይፈስሳል። 14 ሦስተ
ኛው ወንዝ ጤግሮስ ይባላል፥ እርሱም በአሦር
በስተምሥራቅ ይፈሳል፤ አራተኛው ወንዝ ኤፍ
ራጥስ ይባላል።
15 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን
በዔደን የአትክልት ቦታ አኖረው፤ ይህንንም
ያደረገው ሰው የአትክልቱን ቦታ እንዲያለማና
እንዲከባከበው ነው። 16 እግዚአብሔር አምላክ
ሰውን "በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙት ዛፎች ሁሉ
ፍሬ ልትበላ ትችላለህ፤ 17 ነገር ግን ደኑን
ከክፉ ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ከሚሰ
ጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ፤ ምክንያቱም ከዚህ
ዛፍ ፍሬ በበላህበት ቀን በእርግጥ ትሞታለህ"
ብሎ አዘዘው።
18 ቀጥሎም እግዚአብሔር አምላክ "ሰው
ብቻውን መኖሩ መልካም አይደለም፤ ስለዚህ
ተስማሚና ረዳት ጓደኛ እፈጥርለታለሁ" አለ።
19 እግዚአብሔር አምላክ ከምድር ዐፈር
ወስዶ እንስሶችንና ወፎችን ሁሉ ፈጠረ፤ ምን
ዐይነት ስም እንደሚያወጣላቸው ለማየት ወደ
አዳም አመጣቸው፤ አዳም ለእያንዳንዱ
ሕያው ፍጡር ያወጣለት ሰም መጠሪያው
ሆነ። 20 በዚህ ዐይነት አዳም ለወፎቹና ለእን
ስሶቹ ሁሉ ስም አወጣላቸው፤ ለአዳም ግን
ተስማሚና ረዳት ጓደኛ ገና አልተገኘለትም
ነበር።
21 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ አዳ
ምን ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገ፤
አንቀላፍቶም ሳለ ከጐኑ አጥንቶች አንዱን ወሰ
ደና ባዶውን ቦታ በሥጋ ሞላው፤ 22 እግዚአብ
ሔር አምላክ ከአዳም ጐን የወሰዳትን አጥንት
ሴት እድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት።
23 አዳምም፥

"እነሆ በመጨረሻ እኔኑ የምትመስል
አገኘሁ፤
አርሰዋ ከአጥንቴ የተገኘች አጥንት
ናት፤
ከሥጋዬም የተገኘች ሥጋ ናት፤
ከወንድ የተገኘች ስለሆነች 'ሴት'*
ትባል" አለ።

24 ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር
የሚተባበረው ስለዚህ ነው፤ ሁለቱም አንድ
ይሆናሉ።
25 አዳምና ሚስቱ ራቁታቸውን ነበሩ፤
ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር።

ምዕራፍ 3
የሰው አለመታዘዝ

1 እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው አራ
ዊት ሁሉ፥ እባብ እጅግ ተንኰለኛ ነበረ፤ ስለ
ዚህ እባብ "በአትክልቱ ቦታ ካሉት ዛፎች ሁሉ
ፍሬ እንዳትበሉ በእርግጥ እግዚአብሔር እገዞ
አችኋልን?" ሲል ሴቲቱን ጠየቃት።
2 ሴቲቱም "በአትክልት ቦታ ካሉት ዛፎች
ፍሬ ልንበላ እንችላለን፤ 3 ነገር ግን እግዚአብ
ሔር 'በአትክልቱ ቦታ መካከል ካለው ዛፍ ፍሬ
አትብሉ፤ በእጃችሁም አትንኩት፤ ይህን ብታ
ደርጉ ትሞታላችሁ' ብሎ አስጠንቅቆናል"
ስትል መለሰችለት።
4 እባቡም "በፍጹም አትሞቱም፤ 5 እግዚአ
ብሔር ይህን ያዘዛችሁ ከዚያ ዛፍ ፍሬ በበላ
ችሁ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑና
ደኅን ከክፉ ለይታችሁ እንደምታውቁ አስቀ
ድሞ ስለሚያውቅ ነው" አላት።
6 ሴቲቱ ዛፉ የሚያምር፥ ፍሬውም ለመብ
ላት የሚያስጐመጅና ጥበብን የሚያስገኝ እንደ
ሆነ በተመለከተች ጊዜ ከፍሬው ወስዳ በላች፤
ለባሏም ከፍሬው ሰጠችው፤ እርሱም በላ።
7 እንደዚሁ ሁለቱም ወዲያውኑ የማስተዋል
ጥበብ አገኙ፤ እራቁታቸውንም እንደሆኑ ተገነ
ዘቡ፤ ስለዚህ የበለስ ቅጠሎችን አገናኝተው
ሰፋፉና በማገልደም እርቃናቸውን ሸፈኑ።
8 በዚያኑ ቀን ምሽት እግዚአብሔር አምላክ
በአትክልቱ ቦታ ውስጥ ሲመላለስ ድምፁን
ሰሙ፤ ስለዚህም አዳምና ሚስቱ እግዚአብሔር
አምላክ እንዳያያቸው በዛፎች መካከል ተደ
በቁ። 9 ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ሰውየ
ውን ጠርቶ "የት ነው ያለኸው?" ሲል ጠየ
ቀው።
10 አዳምም "በአትክልቱ ቦታ ውስጥ የአን
ተን ድምፅ ሰማሁ፤ እራቁቴንም ስለሆንሁ እን
ተን በመፍራት ተደበቅሁ" አለ።
11 እግዚአብሔርም "እራቁትህን እንደሆንህ
ማን ነገረህ? እትብላ ያልኩህን ፍሬ ከዛፉ ወስ
ደህ በላህን?" አለው።
12 ሰውየውም "ይህች አብራኝ እንድትኖር
የሰጠኸኝ ሴት ፍሬውን ከዛፉ ወስዳ ሰጠችኝና
በላሁ" አለ።

1* 2፡23 በዕብራይስጥ "ኢሽ" ማለት ወንድ ሲሆን "ኢሻ" ማለት ሴት ነች።
2፡24 ፡- ማቴ. 19፡5፤ ማር. 10፡7-8፤ 1ቆሮ. 6፡16፤ ኤፌ. 5፡31። 3፡1 ፡- ራእ. 12፡9፤ 20፡2።

13 እግዚአብሔር አምላክ ሴቲቱን "ለምን
ይህን አደረግሽ" ብሎ ጠየቃት ።
እርስዋም "እባብ አታለለኝና በላሁ"
አለች ።

የእግዚአብሔር ፍርድ

14 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እምላክ
እባቡን እንዲህ አለው ፥
"ይህን በማድረግህ ከእንስሳትና
ከአራዊት ሁሉ ተለይተህ
የተረገምህ ሁን ፥
ከዛሬ ጀምሮ በደረትህ እየተሳብህ
ሂድ ፥
ዕድሜህን ሙሉ ዐፈር ብላ ፥
15 በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት
እንዲኖር አደርጋለሁ ፥
የእርሷ ዘርና የአንተ ዘርም ዘመትር
ጠላቶች እንደሆኑ ይኖራሉ ።
የእርስዋ ዘር የአንተን ራስ ይቀጠቅጣል ፥
አንተም የእርስዋን ዘር ተረከዝ
ትነክሳለህ ።"

16 ሴቲቱንም ፥
"በእርግዝናሽ ወራት ጭንቀትሽን ፥
በምትወልጅበትም ጊዜ የምጥ
ሥቃይሽን አበዛዋለሁ ፥
ይህም ሁሉ ሆኖ ለባልሽ ያለሽ የግብረ
ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት
አይቀንስም ፥
ለእርሱም ታማኝ ትሆኛለሽ" አላት ።

17 አዳምንም እንዲህ አለው ፥
"የሚስትህን ቃል ስምተህ 'አትብላ'
ያልኩህን ፍሬ ከባቱ ወሰደህ
ስለበላህ ፥
አንተ በፈጸምከው ክፉ ሥራ ምክንያት
ምድር የተረገመች ትሁን ፥
ምድር በቂ ምግብ እንድትሰጥህ ፥
ዕድሜህን ሙሉ በብርቱ ድካም
ትሠራለህ ።
18 ምድር እሾህና አሜከላ ታበቅላለች ፥
አንተም የዱር ተክሎችን ትበላለህ ።
19 አንተ ዐፈር ነህ ፥
ወደ ዐፈር ተመልሰህ ትሄዳለህ ፥
ስለዚህ ወደተገኘህበት ዐፈር
እስከምትመለስበት ጊዜ ድረስ
ምግብህን ለማግኘት ላብህን
እያንጠፈጠፍህ ትሠራለህ ።"

20 አዳም ሚስቱ ሕይወት ላላቸው ሰብአዊ
ፍጡሮች ሁሉ እናት ስለሆነች "ሔዋን"
የሚል ስም አወጣላት ። 21 እግዚአብሔር አምላ
ክም ለአዳምና ለሔዋን ከቆዳ ልብስ ሠርቶ አለ
በላቸው ።

የአዳምና የሔዋን ከገነት መባረር

22 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ "እነሆ
አዳም ደኑን ከክፉው ለመለየት የሚያስችል
ዕውቀት በማግኘቱ ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖ
አል ፥ ከእንግዲህ ወዲህ እጁን ዘርግቶ ከሕይ
ወት ዛፍ ፍሬ ወስዶ በመብላት ለዘላለም
መኖር አይገባውም" አለ ። 23 በዚህ ምክንያት
እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከኤደን የአትክ
ልት ቦታ አስወጣው ፥ የተገኘበትንም የምድር
ዐፈር እንዲያለማ አደረገው ። 24 አዳምንም ካስ
ወጣው በኋላ ከኤደን የአትክልት ቦታ በስተ
ምሥራቅ በኩል ኪሩቤል የተባሉትን መላእክት
ነና በየአቅጣጫው እየተገለባበጠ እንደ እሳት
የሚንበለበለውን ሰይፍ እኖረ ፥ ይህንንም ያደረ
ገው ማንም ወደ ሕይወት ዛፍ እንዳይጠጋ
ነው ።

ምዕራፍ 4

ቃየልና አቤል

1 ከዚህ በኋላ አዳም ከሚስቱ ከሔዋን ጋር
የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ ፥ እርስዋም አረገ
ዘች ፥ ወንድ ልጅም ወለደች ፥ "በእግዚአብሔር
ዕርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ" ስትል
"ቃየል"[2a] የሚል ስም አወጣችለት ። 2 ቀጥ
ሎም የቃየል ወንድም የሆነው አቤልን ወለ
ደች ፥ አቤል የበጎች ጠባቂ ሆነ ፥ ቃየል ግን
ገበሬ ሆነ ። 3 ከብዙ ቀን በኋላም ቃየል ከመረ
ተው ሰብል ወስዶ ለእግዚአብሔር መባ አቀ
ረበ ። 4 አቤልም ከበጎቹ መንጋ በመጀመሪያ
የተወለዱውን እንድ ጥቦት አመጣ ፥ ካረደውም
በኋላ የሰባውንና መልካም የሆነውን ብልት
ሁሉ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ ፥ እግዚአብሔ
ርም በአቤልና በመሥዋዕቱ ደስ አለው ። 5 በቃ
የልና በመሥዋዕቱ ግን አልተደሰተም ፥ በዚህ
ምክንያት ቃየል በጣም ተቈጣ ፥ ፊቱም በቍጣ
ተኰሳተረ ፥ 6 በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ቃየልን
እንዲህ አለው ፥ "የተቈጣኸውና ፊትህም
በቍጣ የተኰሳተረው ለምንድን ነው ? 7 መል
ካም ነገር አድርገህ ቢሆን ኖሮ ፊትህ በፈገግታ
ባበራ ነበር ፥ አሁን ግን ያደረግኸው ክፉ ነገር
በመሆኑ ኃጢአት በበርህ ላይ አድብቶአል ፥
በቍጥጥሩ ሥር ሊያደርግህም ይፈልጋል ፥
ሆኖም አንተ ልታሸንፈው ይገባል ።"

2a 4:1 ቃየል ፦ ወይም ቃይን በዕብራይስጥ "ማግኘት" ማለት ነው ።
3:13 ፦ 2ቆሮ. 11:3 ፤ 1ጢሞ. 2:14 ። 3:15 ፦ ራእ. 12:17 ። 3:17-18 ፦ ዕብ. 6:8 ። 3:22 ፦ ራእ. 22:14 ።
4:4 ፦ ዕብ. 11:4 ።

8 ከዚህ በኋላ ቃየል ወንድሙን አቤልን "ና
ወደ ሜዳ እንሂድ" አለው ፣ ወደ ሜዳም በሄዱ
ጊዜ ቃየል በጠላትነት ተነሥቶ ወንድሙን አቤ
ልን ገደለው ።
9 እግዚአብሔርም ቃየልን "ወንድምህ
አቤል ወዴት ነው?" ሲል ጠየቀው ፣ ቃየልም
"የት እንዳለ አላውቅም ፣ እኔ የወንድሜ ጠባቂ
ነኝን?" ብሎ መለሰ ።
10 እግዚአብሔርም ቃየልን እንዲህ አለው ፦
"ይህን አሠቃቂ ነገር ስምን አደረግህ? የፈሰ
ሰው የወንድምህ ደም ከምድር ወደ እኔ እየ
ጮኸ ነው ፣ 11 የተረገምህ ሁን ፣ ወንድምህን
በገደልህው ጊዜ አፍዋን ክፍታ ደሙን በጠላ
ችው ምድር ላይ ተቅበዝባዥ ። 12 ምድርንም
በምታርስበት ጊዜ ምንም ፍሬ አትሰጥህ ፣ በም
ድር ላይም ስደተኛ ሆነህ ተንከራተት ።"
13 ቃየልም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፦
"ይህ ቅጣት እኔ ልሸከመው ከምችለው በላይ
ነው ፣ 14 እነሆ ፥ ዛሬ ከምድር አባረርከኝ ፣ ከፊ
ትህም አሰወራለሁ ፣ በምድርም ላይ ስደተኛና
ተንከራታች እሆናለሁ ፣ እንግዲህ ማንም ሰው
ቢያገኘኝ ይገድለኛል ።"
15 እግዚአብሔር ግን "ማንም አይንካህም ፣
እንተነ የሚገድል ሰባት እጥፍ የበቀል ቅጣት
ይደርስበታል" አለው ። ስለዚህ እግዚአብሔር
ቃየልን ማንም ቢያገኘው እንዳይገድለው የሚያ
ስጠነቅቅ ልዩ ምልክት አደረገለት ። 16 ከዚህ
በኋላ ቃየል ከእግዚአብሔር ፊት ርቆ ሄደ ፣
በዔደን በስተምሥራቅ በሚገኘው በኖድ[3*]
ምድር ኖረ ።

የቃየል ዝርያዎች

17 ቃየል ከሚስቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙ
ነት አደረገ ፣ እርስዋም አረገዘች ወንድ ልጅ
ወለደች ፣ ሰሙንም "ሔኖክ" አሉት ። ቃየል
ከተማን መሠረተ ፣ በልጁም ስም "ሔኖክ"
ብሎ ጠራት ። 18 ሔኖክ ዒራደን ወለደ ፣
ዒራድ መሔያኤልን ወለደ ፣ መሔያኤል መቱ
ሻኤልን ወለደ ፣ መቱሻኤልም ላሜህን ወለደ ፣
19 ላሜህ ዓዳና ጺላ የተባሉትን ሁለት ሚስቶች
አገባ ፣ 20 ዓዳ ያባልን ወለደች ፣ ያባልም ከብ
ቶች እየጠበቁ በድንኳን ይኖሩ የነበሩት የዘላ
ኖች ሰዎች አባት ነበረ ። 21 የእርሱ ወንድም
ዩባልም ዋሽንትና በገና የሚጫወቱ የሙዚቀ
ኞች አባት ነበር ። 22 ጺላም "ቱባልቃይን"
የተባለ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ እርሱ ከነሐስና
ከብረት ልዩ ልዩ ዐይነት ዕቃዎችን ይሠራ
ነበር ። ቱባልቃይንም ናዕማ የተባለች እኅት ነበ
ረችው ።

23 ላሜህ ሚስቶቹን እንዲህ አላቸው ፦
"ዓዳና ጺላ ሆይ! እስቲ አድምጡኝ ፣
አንድ ወጣት ስለመታኝ
ገደልሁት ፣
24 ቃየልን የሚገድል ሰባት እጥፍ የበቀል
ቅጣት ይደርስበታል ከተባለ ፣
እኔን የሚገድል ደግሞ ሰባ ሰባት
እጥፍ የበቀል ቅጣት
ይደርስበታል ።"

ሴትና ሄኖስ

25 አዳም እንደገና ከሚስቱ ጋር የግብረ ሥጋ
ግንኙነት አደረገ ፣ ወንድ ልጅም ወለደች ፣ እር
ስዋም "ቃየል በገደለው በአቤል ምትክ አግዚ
አብሔር ወንድ ልጅ ሰጠኝ" ስትል 'ሴት'[4*]
የሚል ስም አወጣችለት ። 26 ሴትም "ሄኖስ"
የተባለውን ወንድ ልጅ ወለደ ፣ ሰዎች ቅዱስ
ስሙን በመጥራት እግዚአብሔርን ማምለክ የጀ
መሩት በዚያን ጊዜ ነው ።

ምዕራፍ 5

የአዳም ዝርያዎች
(1 ዜ.መ. 1፣1-4)

1 የአዳም ዝርያዎች የስም ዝርዝር ከዚህ
የሚከተለው ነው ፤ እግዚአብሔር ሰውን በፈ
ጠረ ጊዜ በራሱ አምሳያ ፈጠራቸው ፣ 2 ወንድና
ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፣ ባረካቸው ፣ "ሰው"
ብሎም ሰየማቸው ። 3 አዳም መቶ ሠላሳ ዓመት
በሆነው ጊዜ በመልክ አርሱን የሚመስል ወንድ
ልጅ ወለደ ፣ "ሴት" የሚል ስም አወጣለት ።
4 ከዚህ በኋላ አዳም 800 ዓመት ኖረ ፣ ሌሎች
ንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፣ 5 ዕድ
ሜው 930 ዓመት ሲሆነውም ሞተ ።
6 ሴት 105 ዓመት ሲሆነው ሄኖስን
ወለደ ፣ 7 ከዚህ በኋላ ሴት 807 ዓመት ኖረ ፣
ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፣
8 ዕድሜው 912 ዓመት ሲሆነውም ሞተ ።
9 ሄኖስ 90 ዓመት ሲሆነው ቃይናንን
ወለደ ፣ 10 ከዚህ በኋላ 815 ዓመት ኖረ ፣ ሌሎ
ችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፣ 11 ዕድ
ሜው 905 ሲሆነውም ሞተ ።
12 ቃይናንም 70 ዓመት ሲሆነው መላልኤ
ልን ወለደ ፣ 13 ከዚህ በኋላ 840 ዓመት ኖረ ፣
ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፣
14 ዕድሜው 910 ሲሆነውም ሞተ ።
15 መላልኤል 65 ዓመት ሲሆነው ያሬድን
ወለደ ፣ 16 ከዚህ በኋላ 830 ዓመት ኖረ ፣ ሌሎ
ችን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፣ 17 ዕድ
ሜው 895 ሲሆነውም ሞተ ።

3* 4፡16 ኖድ ፡- "መንከራተት" ማለት ነው ። 4* 4፡25 ሴት ፡- በዕብራይስጥ "ስጦ" ማለት ነው ።
4፡8 ፡- ማቴ. 23፡35 ፣ ሉቃ. 11፡51 ፣ 1ዮሐ. 3፡12 ። 4፡10 ፡- ዕብ. 12፡24 ። 4፡24 ፡- ማቴ. 18፡22 ።
5፡1-2 ፡- ዘፍ. 1፡27-28 ። 5፡2 ፡- ማቴ. 19፡4 ፣ ማር. 10፡6 ።

18 ያሬድ 162 ዓመት ሲሆነው ሔኖክን
ወለደ ፤ 19 ከዚህ በኋላ 800 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፤ 20 ዕድ
ሜው 962 ሲሆነውም ሞተ ።
21 ሔኖክ 65 ዓመት ሲሆነው ማቱሳላን
ወለደ ፤ 22 ከዚህ በኋላ ሔኖክ የእግዚአብሔርን
መንገድ በመከተል 300 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎች
ንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፤ 23 ዕድ
ሜው 365 እስኪሆነው ድረስ ኖረ ፤ 24 ይህን
ያህል ዘመን የኖረውም የእግዚአብሔርን መን
ገድ በመከተል ነበር ፤ ከዚህ በኋላ እግዚአብ
ሔር ስለወሰደው አልተገኘም ።
25 ማቱሳላ 187 ዓመት ሲሆነው ላሜክን
ወለደ ፤ 26 ከዚህ በኋላ 782 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ ፤ 27 ዕድ
ሜው 969 ሲሆነውም ሞተ ።
28 ላሜክ 182 ዓመት ሲሆነው ወንድ ልጅ
ወለደ ፤ 29 “ይህ ልጅ እግዚአብሔር በረገማት
ምድር ላይ ከብር-ቱ ሥራችን ያሳርፈናል” ሲል
“ኖኅ”5* ብሎ ጠራው ። 30 ከዚህ በኋላ ላሜክ
595 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች
ልጆች ወለደ ፤ 31 ዕድሜው 777 ሲሆነውም
ሞተ ።
32 ኖኅ 500 ዓመት ከሆነው በኋላ ሦስት
ወንዶች ልጆች ወለደ ፤ እነርሱም ሴም ፥ ካምና
ያፌት ይባሉ ነበር ።

ምዕራፍ 6

የሰዎች ክፋት

1 የሰው ዘር በምድር ላይ እየበዛ በሄደ ጊዜ
ሴቶች ልጆች ተወለዱ ፤ 2 በዚያን ጊዜ ልዩ
የሆኑ ፍጥረቶች6* የእነዚህን ሴቶች ልጆች
ውበት ተመለከቱ ፤ ከመካከላቸውም የሚወዱአ
ቸውን እየመረጡ ወሰዱ ። 3 እግዚአብሔርም
“ሕይወት ስጪ የሆነው መንፈሴ ከሰዎች ጋር
ለዘላለም አይኖርም ፤ ሰዎች ሟቾች ስለሆኑ ከአ
ንግዲህ ወዲያ ከ120 ዓመት የበለጠ አይኖ
ሩም” አለ ። 4 በዚያን ዘመንና ከዚያም በኋላ
ከሰዎች ሴቶች ልጆችና ከነዚያ ልዩ ከሆኑ ፍጥ
ረቶች ተዳቅለው የተወለዱ “ኔፌሊም” የሚባሉ
ግዙፎች ሰዎች ነበሩ ። እነርሱ በጥንት ዘመን
በጀግንነታቸው የታወቁ ዝነኞች ሰዎች ነበሩ ።
5 እግዚአብሔር በምድር ላይ ያሉ ሰዎች
ሁሉ ምን ያህል ዐመፀኞች እንደሆኑና አሳባች
ውም ዘወትር ክፋት ብቻ እንደሆነ ተመለከተ ፤
6 ስለዚህ ሰዎችን በመፍጠሩና በምድር ላይ እን
ዲኖሩ በማድረጉ አዘነ ፤ እጅግም ተጸጸተ ።
7 በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር “እነርሱን በመ
ፍጠሬ እዝኛለሁ ፤ ስለዚህ እነዚህን የፈጠርሁአ
ቸውን ሰዎች ፥ እንስሳት ፥ በደረታቸው እየተ
ላቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችንና ወፎችንም
ጭምር ከምድር ላይ እጠፋለሁ” አለ ። 8 ይሁን
አንጂ ኖኅ የተባለው ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ
ሞገስን አግኝቶ ነበር ።

ኖኅ

9 የኖኅ ታሪክ እንደሚከተለው ነው ፤ ኖኅ
በዘመኑ ምንም በደል የማይሠራና የእግዚአብሔ
ርን መንገድ የሚከተል ደግ ሰው ነበር ፤
10 ኖኅም ሴም ፥ ካምና ያፌት የሚባሉትን
ሦስት ወንዶች ልጆች ወለደ ። 11 በዚያን ጊዜ
በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር
ፊት ክፉዎች ስለነበሩ ፥ ዐመፅ በያሰበት ተስፋ
ፍቶ ነበር ። 12 እግዚአብሔር ዓሰምን ተመለ
ከተ ፤ የተበላሸች እንደሆነችና በውስጧም
ያሉት ሰዎች ሁሉ በክፋት እንደሚኖሩ አየ ።
13 እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው ፥ “የሰ
ውን ዘር በምድር ላይ ስማጥፋት ወስኛለሁ ፤
ምድር በሰዎች የዐመፅ ሥራ ስለተሞላች ሰዎ
ችን ፈጽሞ ከምድር እጠፋቸዋለሁ ፤ 14 ለአንተ
ግን ከጥሩ እንጨት መርከብ ሥራ ፤ በውስጡም
ብዙ ክፍሎች እንዲኖሩት እድርግ ፤ መርከቡን
ከውስጥና ከውጭ በቅጥራን ለቅልቀው ። 15 ርዝ
መቱን 133 ሜትር ፥ የጒኑን ስፋት 22
ሜትር ፥ የከፍታውን ቁመት 13 ሜትር አድ
ርግ ፤ 16 ለመርከቡ ጣራ7* አብጅለት ፤ ጣራውና
ግድግዳው በሚጋጠሙበት ቦታ ላይ 44 ሳንቲ
ሜትር ባዶ ቦታ ተውለት ፤ መርከቡ ባለሦስት
ፎቅ እንዲሆን እድርግ ፤ በጒኑም በኩል በር
አድርግለት ፤ 17 ሕይወት ያለውን ነገር ሁሉ
ከምድር ላይ ለመደምሰስ የጥፋት ውሃ አመጣ
ለሁ ፤ በምድር ላይ ያለ ሕያው ፍጥረት ሁሉ
ይጠፋል ። 18 ከአንተ ጋር ግን ቃል ኪዳን እገባ
ሰሁ ፤ አንተና ሚስትህ ፥ ልጆችህና የልጆችህ
ሚስቶች ወደ መርከቡ ግቡ ።
19 “ከእንተ ጋር በሕይወት እንዲጠበቁ ሥጋ
ከለበሱ ሕያዋን ፍጥረቶች ከየዐይነቱ ሁለት
ሁለት ወንድና ሴት እየወሰድህ ወደ መርከቡ
አስገባ ፤ 20 በሕይወት እንዲኖሩ ከልዩ ልዩ
ወፎች ፥ ከልዩ ልዩ እንስሳት ፥ በደረታቸው እየ
ተሳቡ ከሚንቀሳቀሱ ከልዩ ልዩ ተንቀሳቃሽ
ፍጥረቶች ሁለት ሁለት ወደ እንተ ይምጡ ።
21 እንዲሁም ለአንተና ለእነዚህ ፍጥረቶች ሁሉ
የሚበቃ ልዩ ልዩ ዐይነት ምግብ በመርከቡ
ውስጥ አከማች ።” 22 ኖኅም አግዚአብሔር ያዘዘ
ውን ሁሉ አደረገ ።

5* 5፡29 ኖኅ ፦ በዕብራይስጥ “ዕረፍት” ማለት ነው ። 6* 6፡2 “ልዩ የሆኑ ፍጥረቶች” ወይም “የእግዚአብሔር ልጆች ።”
7* 6፡16 “ጣራ” ወይም “መስኮት ።”
5፡24 ፦ ዕብ. 11፡5 ፤ ይሁዳ 14 ። 6፡1-4 ፦ ኢዮብ 1፡6 ፤ 2፡1 ። 6፡4 ፦ ዘኍ. 13፡33 ። 6፡5-8 ፦ ማቴ. 24፡37 ፤ ሉቃ. 17፡26 ፤ 1ጴጥ. 3፡20 ። 6፡9 ፦ 2ጴጥ. 2፡5 ። 6፡22 ፦ ዕብ. 11፡7 ።

ምዕራፍ 7
የጥፋት ውሃ

1 እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው ፥
“በዚህ ዘመን ካለው ትውልድ መካከል ደግ
ሰው አንተ ብቻ ሆነህ ስላገኘሁህ ፥ ከመላው
ቤተሰብህ ጋር ወደ መርከቡ ግባ ። 2 ለምግብነት
ንጹሕ ከሆኑት ወንዶችና ሴቶች እንስሳት ሁሉ
ሰባት ፥ ሰባት ከአንተ ጋር ወደ መርከቡ አስ
ገባ ፤ ለምግብነት ንጹሕ ካልሆኑት ወንዶችና
ሴቶች እንስሳት ሁሉ ግን አንድ አንድ አስገባ ።
3 ከያንዳንዱ ዐይነት ወፍ ወንድና ሴት ሰባት
ሰባት አስገባ ፤ ይህንንም የምታደርገው እያንዳ
ንዱ ዐይነት እንስሳና ወፍ በሕይወት እንዲኖ
ርና በምድር ላይ ለዘር እንዲተርፍ ነው ። 4 የፈ
ጠርሁትን ሕያው ፍጡር ሁሉ ከምድር ገጽ
ላይ ለማጥፋት ከለሳት ቀን በኋላ አርባ ቀንና
አርባ ሌሊት ሙሉ ዝናም አዘንማለሁ ።”
5 ኖኅም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ አደረገ ።

6 የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በመጣ ጊዜ
የኖኅ ዕድሜ 600 ዓመት ነበር ። 7 ኖኅ ፥
ሚስቱ ፥ ልጆቹና ሚስቶቻቸው ከጥፋት ውሃ
ለማምለጥ ወደ መርከቡ ገቡ ። 8 ለምግብነት
ንጹሕ ከሆኑትና ካልሆኑት ከያንዳንዱ ዐይነት
እንስሳትና ወፎች ፥ 9 ጥንድ ወንድና ሴት እየ
ሆኑ ፥ ወደ ኖኅ መጡ ፤ እግዚአብሔር ኖኅን
ባዘዘውም መሠረት ወደ መርከቡ ገቡ ። 10 ከሰባ
ትም ቀን በኋላ የጥፋት ውሃ መጣ ።

11 ኖኅ 600 ዓመት በሆነው ጊዜ በሁለተ
ኛው ወር በዐሥራ ሰባተኛው ቀን ላይ ከምድር
በታች ያለው የታላቁ ውሃ መፍለቂያዎች ሁሉ
በድንገት ተነደሉ ፤ በሰማይ ያሉት የውሃ መስኮ
ቶች ሁሉ ተከፈቱ ። 12 ዝናምም አርባ ቀንና
አርባ ሌሊት ባለማቋረጥ በምድር ላይ ዘነመ ።
13 ዝናሙ መዝነም በጀመረበት ቀን ኖኅና
ሚስቱ ከልጆቻቸው ከሴም ፥ ከካም ፥ ከያፌትና
ከሦስቱም ልጆቻቸው ሚስቶች ጋር ወደ መር
ከቡ ገቡ ። 14 ከአራዊት ፥ ከእንስሳት ፥ በደረታ
ቸው እየተሳቡ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችና በስ
ማይ ከሚበሩ ወፎች ከእያንዳንዱ ዐይነት አብረ
ዋቸው ገቡ ። 15 በዚህ ዐይነት እስትንፋስ ካላ
ቸው ፍጥረቶች ከእያንዳንዱ ዐይነት ሁለት
ሁለት እየሆኑ ከኖኅ ጋር ወደ መርከቡ ገቡ ፤
16 ፍጥረት ሁሉ ወንድና ሴት ሆነው ወደ መር
ከቡ የገቡት እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት
ነው ፤ ከዚህ ቀጥሎ እግዚአብሔር ከኖኅ
በስተኋላ የመርከቡን በር ዘጋ ።

17 የጥፋት ውሃ አርባ ቀን ድረስ በመዝነም
እየበረታ ሄደ ፤ የውሃውም ጥልቀት እየጨመረ
ስለሄደ መርከቡን ከምድር በላይ ከፍ አደረ
ገው ፤ 18 ውሃ በምድር ላይ እያደገና እየበረታ
በሄደ መጠን መርከቡ በውሃው ላይ መንሳፈፍ
ጀመረ ። 19 ውሃውም ከሰማይ በታች ያሉትን
ታላላቅ ተራራዎችን እንኳ እስከሚሸፍን ድረስ
ጥልቅ ሆነ ። 20 ውሃው ከተራራዎች ጫፍ በላይ
ሰባት ሜትር ያህል ከፍ አለ ። 21 ወፎችና እንስ
ሳት ፥ ሰዎችም ሁሉ ሳይቀሩ ሞቱ ። በምድር
ላይ ያሉት ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ጠፉ ።
22 በምድር ላይ የሚኖር እስትንፋስ ያለው ነገር
ሁሉ ተደመሰሰ ። 23 እግዚአብሔር በምድር ላይ
ያለውን ሕያው ፍጥረት ሁሉ ፥ ሰዎችንም ፥
እንስሳትንም ፥ ወፎችንም ፥ በደረታቸው እየተ
ላቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች ሳይቀሩ ሁሉንም
አጠፋ ። ከሞት የተረፉት ኖኅና ከእርሱ ጋር
በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ብቻ ነበሩ ።
24 ውሃው እስከ መቶ ሃምሳ ቀን እልጐደለም
ነበር ።

ምዕራፍ 8
የጥፋት ውሃ ፍጻሜ

1 እግዚአብሔር ኖኅንና ከእርሱ ጋር በመር
ከቡ ውስጥ ያነበሩትን አራዊትና እንስሳት ሁሉ
አሰበ ፤ ነፋስ በምድር ላይ እንዲነፍስ አደረገ ፤
ውሃውም መጕደል ጀመረ ። 2 ከምድር በታች
ያለው ታላቅ ውሃ መፍለቂያዎችና በሰማይ
ያሉት የውሃ መውረጃ በሮች ሁሉ ተዘጉ ፤ ዝና
ሙም ከሰማይ መውረዱን እቆመ ። 3 ውሃው
ቀስ በቀስ ከምድር ላይ መጕደል ጀመረ ፥
ከመቶ ሃምሳ ቀኖችም በኋላ ውሃው ከምድር
ላይ ጨርሶ ደረቀ ። 4 በሰባተኛው ወር ፥ በዐ
ሥራ ሰባተኛው ቀን መርከቡ “እራራት” ከተባ
ሉት ተራራዎች በአንደኛው ጫፍ ላይ ዐረፈ ።
5 ውሃው እስከ ዐሥረኛው ወር ድረስ ቀስ በቀስ
እየጐደለ ሄደ ፤ በዐሥረኛው ወር መጀመሪያው
ቀን የተራራዎቹ ጫፎች ታዩ ።

6 ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ ከመርከቡ መስኮቶች
አንዱን ከፈተና ፥ 7 ቊራን ወደ ውጪ ላከው ፤
ቊራውም ውሃው ከምድር እስኪደርቅ ድረስ
ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር ። 8 ከዚህ በኋላ ኖኅ
ውሃው ከምድር ላይ መጕደሉን ለማወቅ እን
ዲት ርግብ ላከ ። 9 ነገር ግን ውሃው ገና ምድ
ርን ሁሉ ሸፍኖ ስለነበር ርግቢቱ የምታርፍበት
ቦታ አላገኘችም ፤ ስለዚህ ኖኅ ወዳለበት መር
ከብ ተመልሳ መጣች ፤ ኖኅም እጁን ዘርግቶ
ወደ ውስጥ አስገባት ። 10 ሰባት ቀን ከቆየም
በኋላ ርግቢቱን እንደገና አውጥቶ ላካት ።
11 እርስዋም ወደ ማታ ጊዜ የለመለመ የወይራ
ዛፍ ቅጠል ብእፍኝ ይዛ ወደ ኖኅ ተመለሰች ፤
በዚህ ሁኔታ ኖኅ ውሃው ከምድር መጕደሉን
ዐወቀ ። 12 ደግሞም ሰባት ቀን ከቆየ በኋላ ኖኅ
ርግቢቱን እንደገና አውጥቶ ላካት ፤ በዚህን ጊዜ
ግን ርግቢቱ ሳትመለስለት ቀረች ።

7፥7 ፡- ማቴ. 24፡38-39 ። ሉቃ. 17፡27 ። 7፥11 ፡- 2ጴጥ. 3፡6 ።

13 የኖኅ ዕድሜ 601 ዓመት በሆነ ጊዜ በመ
ጀመሪያው ወር ፥ በመጀመሪያው ቀን ውሃው
ከምድር ላይ ደረቀ ፤ ኖኅ የመርከቡን ክዳን አን
ሥቶ ዙሪያውን ተመለከተ ፥ ምድሪቱ እንደ ደረ
ቀች አየ ። 14 በሁለተኛው ወር ከወሩም በሃያ
ሰባተኛው ቀን ምድር ፈጽማ ደረቀች ።

15 እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው ፥
16 "አንተ ከሚስትህ ፥ ከልጆችህና ከልጆችህ
ሚስቶች ጋር ሆነህ ከመርከቡ ውጣ ፤ 17 ተራብ
ተውና ተባዝተው ምድርን ሁሉ እንዲሞሉ ከአ
ንተ ጋር ያሉትን ሕያዋን ፍጥረቶች ሁሉ ወፎ
ችን ፥ እንስሳትንና ሌሎችን በምድር ላይ በደረ
ታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱትን ፍጥረቶች
ሁሉ ይዘህ ውጣ ።" 18 ከዚህ በኋላ ኖኅ ከሚ
ስቱ ፥ ከልጆቹና ከልጆቹ ሚስቶች ጋር ሆኖ
ከመርከቡ ወጣ ፤ 19 አራዊትና እንስሳት ፥ ወፎ
ችም በየረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረ
ቶችም በየወገናቸው ሆነው ከመርከቡ ወጡ ።

ኖኅ መሥዋዕት አቀረበ

20 ኖኅ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ ፤
ለምግብነት ንጹሕ ከሆኑት እንስሳትና ወፎች
ሁሉ ከየዐይነቱ አንዳንድ ወሰደ ፤ መሥዋዕት
እንዲሆኑም ሁሉንም በመሠዊያው ላይ አቃጠላ
ቸው ። 21 የመሥዋዕቱም መዓዛ እግዚአብሔርን
ደስ አሰኘው ፤ በአሰቡም እንዲህ አለ ፥ "ሰው
በሚፈጽመው ዘይል ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ
ምድርን አልረግምም ፤ ምክንያቱም ገና ከሕፃን
ነቱ ጊዜ ጀምሮ የሰው አሳብ ክፉ መሆኑን ዐው
ቃለሁ ፤ በአሁኑ ጊዜ እንዳደረግሁት ሕይወት
ያለውን ፍጥረት ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ ከቶ
አላጠፋም ።

22 "ዓለም እስካለች ድረስ ፥
ለመዝራትና ለማጨድ ፥ ለብርድና
ለሙቀት ፥
ለበጋና ለክረምት ፥ ለቀንና ለሌሊት
የማያቋርጥ ጊዜ ይኖራል ።"

ምዕራፍ 9

እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባው ቃል ኪዳን

1 እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው ፥
እንዲህም አላቸው ፥ "ብዙ ፥ ተባዙ ምድርንም
ሙሉአት ፤ 2 እንስሳት ፥ ወፎች ፥ በደረታቸው
እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችና ዓሣዎች
ሁሉ እናንተን በመፍራት ይኑሩ ፤ ሁሉም በሥ
ልጣናችሁ ሥር ይሁኑ ። 3 ከዚህ በፊት የአትክ
ልት ዐይነቶችን ምግብ አድርጌ እንደሰጠኋችሁ
ሁሉ እነዚህም ተንቀሳቃሽ ፍጥረቶች ሁሉ
ምግብ እንዲሆኑአችሁ ሰጥቼአችኋለሁ ። 4 ነገር
ግን ደም ያለበትን ሥጋ አትብሉ ፤ ምክንያቱም
በደም ውስጥ ሕይወት አለ ። 5 ሰውን የሚገድል
ሁሉ ይቀጣል ፤ እንስሳ እንኳ ሰውን ከገደሰ
በሞት እቀጣዋለሁ ።

6 ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳያ
ነው ፤
ስለዚህ ሰውን የሚገድል ሁሉ በሰው
እጅ ይሞታል ።

7 "እናንተ ብዙ ፥ ተባዙ ፥ ዘራችሁ ምድርን
ይሙላ ።"

8 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹ
እንዲህ አላቸው ፥ 9 "እነሆ ከእናንተና ከዘራ
ችሁ ፥ 10 ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሁሉ ፥
ማለትም ከወፎች ፥ ከእንስሳትና ከአራዊት ፥ ከአ
ንተ ጋር ከመርከቡ ውስጥ ከወጡት ፍጥረቶችና
በምድር ከሚወለዱ ዝርያዎቻቸው ሁሉ ጋር
ቃል ኪዳን እገባለሁ ፤ 11 በዚህም በገባሁላችሁ
ቃል ኪዳን መሠረት ፥ ከእንግዲህ ወዲህ ሕያ
ዋን ፍጥረቶች ሁሉ በጥፋት ውሃ ከቶ አይደመ
ሰሱም ፤ ምድርም ዳግመኛ በጥፋት ውሃ አትጠ
ፋም ። 12 ከእናንተና ከሕያዋን ፍጥረቶች ሁሉ
ጋር ለምገባው ለዚህ ለዘላለማዊ ቃል ኪዳን
ምልክት ይሆን ዘንድ ፥ 13 ቀስቴን በደመናዎች
ላይ አደርጋለሁ ፤ ይህም ቀስት ከዓለም ጋር ለገ
ባሁት ቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ ይኖራል ።
14 ለማደጋ በደመና በምሸፍንበትና ቀስትም በደ
መና ላይ በሚታይበት ጊዜ ሁሉ ፥ 15 "ከእንግ
ዲህ ወዲህ የጥፋት ውሃ ፥ ሕያዋን ፍጥረቶችን
ሁሉ ከቶ አያጠፋም" ብዬ ከእናንተና ከሌሎች
ሕያዋን ፍጥረቶች ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን
አስታውሳለሁ ። 16 ቀስት በደመናዎች ላይ በሚ
ታይበት ጊዜ ሁሉ በእኔና በምድር ላይ ባሉት
ሕይወት ላላቸው ፍጥረቶች መካከል ያለውን
ዘላለማዊ ቃል ኪዳን አስታውሳለሁ ። 17 ይህም
ቀስት ሕይወት ላላቸው ፍጥረቶች ሁሉ የገባሁ
ትን ቃል ኪዳን የሚያስታውስ ምልክት
ነው ።"

ኖኅና ልጆቹ

18 ከመርከቡ የወጡት የኖኅ ልጆች ሴም ፥
ካምና ያፌት ናቸው ፤ ካም የከነዓን አባት
ነው ፤ 19 አሁን በምድር ላይ ተበትነው ያሉት
ሰዎች ሁሉ የተገኙት ከእነዚህ ከሦስቱ የኖኅ
ልጆች ነው ።

20 ኖኅ ገበሬ ነበረ ፤ የወይን አትክልትንም
መትከል ጀመረ ፤ 21 ከዕለታት አንድ ቀን ኖኅ
የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰከረ ፤ ልብሱንም አውልቆ
ራቁቱን በድንኳን ውስጥ ተኛ ። 22 የከነዓን
አባት የሆነው ካም አባቱ ኖኅ እራቁቱን እንደ
ሆነ ባየ ጊዜ ወደ ውጭ ወጥቶ ለሁለቱ

9:1 ፦ ዘፍ. 1:28 ። 9:4 ፦ ዘሌ. 7:26-27 ፤ 17:10-16 ፤ 19:26 ፤ ዘዳ. 12:16,23 ፤ 15:23 ። 9:6 ፦ ዘፍ. 1:26 ፤ ዘጸ. 20:13 ። 9:7 ፦ ዘፍ. 1:28 ።

ወንድሞቹ ነገራቸው። 23 ሴምና ያፌትም ጋቢ
በስተኋላቸው ፥ በትከሻቸው ያዙ ፤ ወደ ድንኳ
ኑም የኋሊት ሄዱና የአባታቸውን ራቁትነት
እንዳያዩ ፊታቸውን አዙረው ሐፍረተ ሥጋውን
ሸፈኑ። 24 ኖኅ ስካሩ አልፎለት ሲነቃ ፥ ትንሹ
ልጁ ያደረገበትን ዐወቀ ፤ 25 እንዲህም አለ ፥

“ከነዓን የተረገመ ይሁን!
ለወንድሞቹ አገልጋይ ይሁን!

26 የሴም አምላክ የሆነው እግዚአብሔር
የተመሰገነ ይሁን ፤
ከነዓንም የሴም አገልጋይ ይሁን ፤
27 እግዚአብሔር የያፌትን ምድር ያስፋ ፥
የያፌት ዝርያዎች ከሴም ዝርያዎች
ጋር አብረው ይኑሩ ፤
ከነዓን የያፌት አገልጋይ ይሁን።”

28 ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅ 350 ዓመት
ኖረ። 29 ዕድሜውም 950 ዓመት ሲሆነው
ሞተ።

ምዕራፍ 10

የኖኅ ልጆች ትውልድ
(1 ዜ.መ. 1፥5-23)

1 የኖኅ ልጆች የሴም ፥ የካምና የያፌት ዝር
ያዎች የሚከተሉት ናቸው ፤ እነዚህ ሦስቱ ከጥ
ፋት ውሃ በኋላ ልጆች ወለዱ ፤

የያፌት ዝርያዎች

2 የያፌት ልጆች ፦ ጎሜር ፥ ማጎግ ፥
ማዳይ ፥ ያዋን ፥ ቱባል ፥ ሜሼክና ፥ ቲራስ
ናቸው። 3 የጎሜር ልጆች ፦ አሽኬናዝ ፥ ሪፋትና
ቶጋርማ ናቸው። 4 የያዋን ልጆች ፦ ኤሊሻ ፥
ተርሴስ ፤8* ኪቲምና9* ሮዳኒም10* ናቸው።
5 እነዚህ ሁሉ በባሕር ዳርቻና በደሴቶች
ላይ ለማኖሩ የያፌት ዝርያዎች ቅድመ አያቶች
ናቸው ፤ በየአገራቸውና በየጐሳቸውም ተከፋፍ
ለው የሚኖሩ ሕዝቦች ነበሩ ፤ እያንዳንዱም
ጐሳ የሚነጋገርበት የራሱ ቋንቋ ነበረው።

የካም ዝርያዎች

6 የካም ልጆች ፦ ኩሽ ፥ ምጽራይም ፤11*
ፉጥና12* ከነዓን ናቸው። 7 የኩሽ ልጆች ፦
ሳባ ፥ ሐዊላ ፥ ሳብታ ፥ ራዕማና ሳብተካ
ናቸው። የራማ ልጆች ፥ ሳባና ደዳን ናቸው።
8 ኩሽ በዓለም ላይ የመጀመሪያው ታላቅ
ጦረኛ የነበረውን ናምሩድን ወለደ። 9 ናምሩድ
በእግዚአብሔር ድጋፍ ታላቅ አዳኝ ነበረ ፤
ሰዎች “እንደ ናምሩድ ታላቅ አዳኝ ያድርግህ”
እያሉ የሚመርቁት ስለዚህ ነው። 10 በመጀመ
ሪያ የናምሩድ መንግሥት በስናዖር የነበሩትን
የሦስት ከተሞች ግዛት ማለትም ባቢሎን ፥ ኤሬ
ክንና አካድን ያጠቃልል ነበር። 11 ከዚያም
ወደ አሦር ሄደና ነነዌ ፥ ረሖቦት ፥ ካላሕ ፥
12 እንዲሁም በነነዌና በካላሕ መካከል ያለውን
ታላቅ ከተማ ሬሴን የተባሉትን ከተሞች መሠ
ረተ።

13 የምጽራይም ዝርያዎች የሉድ ፥ የዐናም ፥
የለሃብ ፥ የናፍቱሕ ፥ 14 የፈትሮስ ፥ ፍልስጥኤማ
ውያን የተገኙባቸው የካፍቶርና የካስሉሕ ሕዝ
ቦች ናቸው።

15 የከነዓን ልጆች በኵሩ ጸዶን ፥ ተከታዩ
ሔት ይባሉ ነበር ፤ 16 ሌሎቹም የከነዓን ዝርያ
ዎች ኢያቡሳውያን ፥ አሞራውያን ፥ ጌርጌሳው
ያን ፥ 17 ሒዋውያን ፥ ዓርቃውያን ፥ ሲናውያን ፥
18 አርዋዳውያን ፥ ጻማራውያንና ሐማታውያን
ነበሩ ፤ ዘግይቶም የተለያዩት የከነዓን ጐሳዎች
በየስፍራው ተሰራጩ ፤ 19 በዚህ ወይነት የከነዓና
ውያን ድንበር ከሲዶና አንሥቶ በስተደቡብ በጎ
ራር አጠገብ አስካለው አስከ ጋዛ ድረስ ፥ በስተ
ምሥራቅ አስከ ሰዶም ፥ ገሞራ ፥ አዳማና በላ
ሻዕ አጠገብ አስካለው አስከ ጸቦይም ድረስ
ሆነ። 20 እነዚህ ሁሉ የካም ዝርያዎች ናቸው ፤
አነርሱ በተለያዩ ጐሳዎችና አገሮች ተከፍለው
ይኖሩ ነበር ፤ እያንዳንዱም ጐሳ የሚነጋገረው
በራሱ ቋንቋ ነበር።

የሴም ዝርያዎች

21 የያፌት ታላቅ ወንድም ሴም የዔቦር ዝር
ያዎች ቅድመ አያት ነው።

22 የሴም ልጆች ፦ ዔላም ፥ አሦር ፥ አርፋክ
ሳድ ፥ ሉድና አራም ናቸው። 23 የአራም
ልጆች ፦ ዑጽ ፥ ሑል ፥ ጌተርና ሜሼክ
ናቸው ፤ 24 አርፋክሳድ ሼላሕን ወለደ ፤ ሼላ
ሕም ዔቦርን ወለደ። 25 ዔቦር ሁለት ልጆች
ወለደ ፤ አንደኛው እርሱ በተወለደበት ዘመን
ሕዝቦች ስለተከፋፈሉ ፈሌግ13* ተባለ ፤ ሌላው
ዮቅጣን ይባል ነበር። 26 የዮቅጣን ልጆች ፥
አልሞዳድ ፥ ሼሌፍ ሐጸርማዌት ፥ ዬራሕ ፥
27 ሀዶራም ፥ ኡዛል ፥ ዲቅላ ፥ 28 ዖባል ፥ አቢማ
ኤል ፥ ሳባ ፥ 29 አፌር ፥ ሐዊላና ዮባብ ናቸው ፤
አነዚህ ሁሉ የዮቅጣን ዝርያዎች ናቸው።

30 እነርሱ የኖሩበት ምድር በስተምሥራቅ
ባለው በተራራማው አገር ከሜሻ እስከ ስፋር
ይደርስ ነበር። 31 እነዚህ ሁሉ የሴም ዝርያዎች
ናቸው ፤ እነርሱ በተለያዩ ጐሳዎችና አገሮች
ተከፍለው ይኖሩ ነበር ፤ አያንዳንዱም ጐሳ የሚ
ነጋገረው በራሱ ቋንቋ ነበር።

32 እነዚህ በየነገዳቸው የተከፋፈሉ ሕዝቦች
የኖኅ ዝርያዎች ነበሩ ፤ ከጥፋት ውሃ በኋላ

8* 10፥4 ተርሴስ ፦ “እስፔን” ማለት ነው። 9* 10፥4 ኪቲም ፦ “ቆጵሮስ” ማለት ነው። 10* 10፥4 ሮዳኒም ፦ “ሮድ” ማለት ነው። 11* 10፥6 ምጽራይም ፦ “ግብጽ” ማለት ነው። 12* 10፥6 ፉጥ ፦ “ሊቢያ” ማለት ነው። 13* 10፥25 ፈሌግ ፦ በዕብራይስጥ “መከፋፈል” ማለት ነው።

የምድር ሕዝቦች ሁሉ የተገኙት ከእነዚህ ከሦስ
ልጆች ነበር ።

ምዕራፍ 11

የባቢሎን ግንብ

1 በመጀመሪያ የዓለም ሕዝቦች መነጋገሪያ
ቋንቋ አንድ ብቻ ነበር ፤ 2 ሰዎች ወደ ምሥራቅ
በተጓዙ ጊዜ በባቢሎን ምድር አንድ ሜዳ
አገኙ ፤ በዚያም ተቀመጡ ። 3 እርስ በርሳቸ
ውም "ኑ ጡብ እንሥራ ፤ እንዲጠነክርም በእ
ሳት እንተኩሰው!" ተባባሉ ፤ በዚህ ዐይነት
የሚገነቡትን ጡብ አገኙ ፤ በእንድነት የሚያጣ
ብቁበትንም ቅጥራን አገኙ ። 4 እንዲህም አሉ ፤
"ኑ አንድ ከተማ እንመሥርት ፤ በዚያም ጫፉ
እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ፤ በዚህ
ዐይነት በምድር ላይ ከመበታተናችን በፊት ሰማ
ችንን እናስጠራለን ።"

5 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሰዎቹ የሠሩትን
ኩተማና ግንብ ለማየት ወረደ ፤ 6 እንዲህም
አለ ፦ "እነሆ እነዚህ ሕዝቦች አንድ ወገን
ናቸው ፤ መነጋገሪያ ቋንቋቸውም አንድ ነው ፤
ይህንንም ለመሥራት የቻሉት በዚህ ምክንያት
ነው ፤ በዚህ ዐይነት ሳይዘገዩ ያቀዱትን ሁሉ
ማድረግ አያቅታቸውም ። 7 ስለዚህ ኑ እንው
ረድ ፤ እርስ በርሳቸውም እንዳይግባቡ ቋንቋቸ
ውን እንደበላልቀው ።" 8 ከዚህ በኋላ እግዚአብ
ሔር በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው ፤ ከተማው
ንም መሥራት አቆሙ ፤ 9 የከተማውም ስም
"ባቢሎን"[14*] ተባለ ፤ ምክንያቱም በዚያ እግዚ
አብሔር የሕዝቡን ቋንቋ ስለደበላለቀና አነር
ሱን በዓለም ዙሪያ ስለበተናቸው ነው ።

ከሴም እስከ አብርሃም
(1 ዜ.መ. 1፡24-27)

10 የሴም ዝርያዎች የሚከተሉት ናቸው ፦
ከጥፋት ውሃ በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ ሴም
100 ዓመት በሆነው ጊዜ አርፋክሳድ የተባለ
ልጅ ወለደ ፤ 11 አርፋክሳድን ከወለደ በኋላ
500 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና
ሴቶች ልጆች ወለደ ።

12 አርፋክሳድም 35[15*] ዓመት ሲሆነው ሼላ
ሕን ወለደ ። 13 ከዚህ በኋላ 403 ዓመት ኖረ ፤
ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን
ወለደ ።

14 ሼላሕ 30[16*] ዓመት ሲሆነው ዔቦርን
ወለደ ፤ 15 ከዚህ በኋላ 403 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ ።

16 ዔቦር 34[17*] ዓመት ሲሆነው ፈሌግን
ወለደ ፤ 17 ከዚህ በኋላ 430 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ ።

18 ፈሌግ 30[18*] ዓመት ሲሆነው ረዑን
ወለደ ፤ 19 ከዚህ በኋላ 209 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ ።

20 ረዑ 32[19*] ዓመት ሲሆነው ሰሩግን
ወለደ ፤ 21 ከዚህ በኋላ 207 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ ።

22 ሰሩግ 30[20*] ዓመት ሲሆነው ናኮርን
ወለደ ፤ 23 ከዚህ በኋላ 200 ዓመት ኖረ ፤ ሌሎ
ችን ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ ።

24 ናኮር 29[21*] ዓመት ሲሆነው ታራን
ወለደ ፤ 25 ከዚህ በኋላ 119[22*] ዓመት ኖረ ፤
ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን
ወለደ ።

26 ታራ 70 ዓመት ከሆነው በኋላ አብራ
ም ፣ ናኮርንና ሃራንን ወለደ ።

የታራ ዝርያዎች

27 የአብራም ፣ የናኮርና የሃራን አባት የነበ
ረው የታራ ዝርያዎች የሚከተሉት ናቸው ፤
ሃራን ሎጥን ወለደ ፤ 28 ሃራን አባቱ ታራ ገና
በሕይወት ሳለ በተወለደባት ከተማ በኡር
ሞተ ፤ ኡር የምትገኘው በከለዳውያን ምድር
ነበር ። 29 አብራም ሣራይን አገባ ፤ ናኮር ደግሞ
ሚልካን አገባ ፤ እርስዋም ዬስካንን የወለደ የሃ
ራን ልጅ ናት ። 30 ሣራይ መኻን በመሆንዋ
ልጅ አልወለደችም ነበር ።

31 ታራ ልጁን አብራምን ፣ ከሃራን የተወለደ
ውን የልጅ ልጁን ሎጥን ፣ የአብራም ሚስት
የሆነችውን ምራቱን ሣራይን ይዞ በባቢሎን
የምትገኘውን የኡርን ከተማ በመተው ወደ ከነ
ዓን ምድር ለመሄድ ተነሣ ፤ ወደ ካራን ዘል
ቀው እዚያ ተቀመጡ ። 32 ታራ 205 ዓመት
ሲሆነው በካራን ሞተ ።

ምዕራፍ 12

የአብራም መጠራት

1 እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው ፦
"አገርህን ትተህ ፤ ከዘመዶችህና ከአባትህ ቤተ
ሰብ ተለይተህ ፤ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ ፤
2 ዘርህን አበዛዋለሁ ፤ ታላቅ ሕዝብም
ይሆናል ፤ እባርክሃለሁ ፤

14* 11፡9 ባቢሎን ፦ በዕብራይስጥ "መደባለቅ" ማለት ነው ። 15* 11፡12 በዕብራይስጥ "35" ሲል በሰባ ሊቃናት "135" ይላል ።
16* 11፡14 በዕብራይስጥ "30" ሲል በሰባ ሊቃናት "130" ይላል ። 17* 11፡16 በዕብራይስጥ "34" ሲል በሰባ ሊቃናት "134"
ይላል ። 18* 11፡18 በዕብራይስጥ "30" ሲል በሰባ ሊቃናት "130" ይላል ። 19* 11፡20 በዕብራይስጥ "32" ሲል በሰባ ሊቃናት
"132" ይላል ። 20* 11፡22 በዕብራይስጥ "30" ሲል በሰባ ሊቃናት "130" ይላል ። 21* 11፡24 በዕብራይስጥ "29" ሲል በሰባ
ሊቃናት "109" ይላል ። 22* 11፡25 በዕብራይስጥ "119" ሲል በሰባ ሊቃናት "129" ይላል ።
12፡1 ፦ ሐ.ሥ. 7፡2-3 ፤ ዕብ. 11፡8 ።

ስምህንም ገናና አደርገዋለሁ ፤
ለሌሎችም በረከት ትሆናለህ ።
3 የሚመርቁህን እመርቃለሁ ፤
የሚረግሙህንም እረግማቸዋለሁ ፤
በአንተም አማካይነት ሕዝቦች ሁሉ
ይባረካሉ ።”

4 አብራም እግዚአብሔር እንደነገረው ከካ
ራን ወጥቶ ሄደ ፤ በዚያን ጊዜ ዕድሜው ሰባ
አምስት ዓመት ነበር ፤ ሎጥም አብሮት ሄደ ።
5 አብራም ፥ ሚስቱ ሣራይና የወንድሙ ልጅ
ሎጥ ፥ በካራን ላሉ ያገኙትን ሀብትና አገልጋዮ
ቻቸውን ሁሉ ይዘው ወደ ከነዓን ምድር ሄዱ ።
ከነዓን በደረሱ ጊዜ ፥ 6 አብራም በሴኬም
ወደሚገኘው ቅዱስ ስፍራ ወደ ሞሬ ዛፍ እስኪ
ደርስ ድረስ ተጓዘ ፤ በዚያን ጊዜ ከነዓናውያን
በዚያች ምድር ይኖሩ ነበር ። 7 እግዚአብሔር
ለአብራም ተገለጠለትና “ለዘርህ የምሰጠው
ምድር ይህ ነው” አለው ፤ ከዚህ በኋላ አብራም
ለተገለጠለት አምላክ በዚያ ቦታ መሠዊያ
ሠራ ። 8 ቀጥሎም ከቤትኤል በስተምሥራቅ
ወዳለው ተራራማ አገር ወጣ ፤ ቤትኤልን በስተ
ምዕራብ ፥ ሀይን በስተምሥራቅ አድርጎ ድንኳ
ኑን ተከለ ፤ በዚያም መሠዊያ ሠራና ለእግዚአብ
ሔር ሰገደ ፤ 9 ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረም
ወደ ኔጌብ23* መጣ ።

አብራም በግብጽ አገር

10 በከነዓን ምድር ረሀብ ገባ ፤ ረሀቡም እየበ
ረታ በመሄዱ አብራም የረሀቡን ጊዜ ሰማላለፍ
ዘስተደዘብ ርቆ ወደ ግብጽ አገር ሄደ ። 11 አብ
ራም ወደ ግብጽ ምድር ለመግባት በተቃረበ
ጊዜ ሚስቱን ሣራይን እንዲህ አላት ፥ “አንቺ
በጣም ቈንጆ ሴት መሆንሽን ዐውቃለሁ ፤
12 ግብጻውያን አንቺን በሚያዩበት ጊዜ ‘ይህች
ሚስቱ ናት’ በማለት እኔን ይገድሉኛል ፤ አን
ቺን ግን በሕይወት እንድትኖሪ ይተዉሻል ።
13 ስለዚህ ‘እኅቱ ነኝ’ በያቸው ፤ በዚህ ዐይነት
በእንቺ ምክንያት በሕይወት እንድኖር ይተዉ
ኛል ፤ በደኅና ዐይንም ይመለከቱኛል ።”

14 ወደ ግብጽ በገቡ ጊዜ በእርግጥም ግብጻ
ውያን የአብራም ሚስት በጣም ቈንጆ እንደሆ
ነች አዩ ። 15 እንዲሁም አንዳንድ የፈርዖን
ባለሟሎች ባዩአት ጊዜ ስለ ቁንጅናዋ ሰፈርዖን
ተናገሩ ፤ ስለዚህ ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰ
ደች ። 16 በእርስዋ ምክንያት ንጉሡ አብራምን
በደኅና ዐይን ተመለከተው ፤ የበጎችና የፍየሎች
መንጋ ፥ ከብቶች ፥ አህዮች ፥ ሚመሎች ፥ ወንዶ
ችና ሴቶች አገልጋዮች ሰጠው ።

17 ነገር ግን ንጉሡ ሣራይን በመውደዱ ምክ
ንያት እግዘአብሔር በእርሱና በባለሟሎቹ ሁሉ
ላይ አሠቃቂ ዘሽታዎች አመጣባቸው ። 18 ከዚህ
በኋላ ፈርዖን አብራምን አስጠርቶ እንዲህ ሲል
ጠየቀው “ይህ ያደረግህብኝ ነገር ምንድን
ነው ? ሣራይ ሚስትህ እንደሆነች ለምን አልነገ
ርከኝም ? 19 ‘እኅቴ ነች’ ብለህ በሚስትነት እን
ድወስዳት ለምን አደረግህ ? ይህችውና ሚስ
ትህ ! ይዘሃት ውጣ !” 20 ንጉሡ ባዘዛቸው መሠ
ረት ባለሟሎቹ አብራምንና ሚስቱን ካለው
ሀብት ሁሉ ጋር ከአገር አስወጡአቸው ።

ምዕራፍ 13

አብራምና ሎጥ ተለያዩ

1 አብራም ሚስቱንና ያለውን ሀብት ሁሉ
ይዞ ከግብጽ ወደ ኔጌብ ሄደ ፤ ሎጥም አብሮት
ሄደ ። 2 አብራም ብዙ እንሰሳት ፥ ብዙ ብርና
ወርቅ ያለው ሀብታም ለው ነበረ ።
3 ከኔጌብ ተነሥቶም ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋ
ወር ወደ ቤትኤል አመራ ፤ በቤትኤልና በሀያ
መካከል ወዳለውም ሰፍራ ደረሰ ፤ ይህም ስፍራ
ከዚህ በፊት ድንኳን ተከሎ የሰፈረበትና ፥
4 መሠዊያም ሠርቶበት የነበረው ነው ፤ እዚያም
ለእግዚአብሔር ሰገደ ።
5 ከአብራም ጋር ይጓዝ የነበረው ሎጥም በበ
ኩሉ ብዙ በጎች ፥ ፍየሎችና ከብቶች ነበሩት ፤
ቤተሰቦቹና አገልጋዮቹም ብዙዎች ነበሩ ።
6 አብራምና ሎጥ ብዙ የከብት መንጋ ስለነበራ
ቸው አብረው ለመኖር አልቻሉም ፤ ምክንያ
ቱም ከብቶቻቸውን በአንድነት የሚያሠማሩበት
በቂ የግጦሽ ቦታ አልነበረም ፤ 7 ከዚህም የተነሣ
በአብራም እረኞችና በሎጥ እረኞች መካከል
ጠብ ተፈጠረ ፤ በዚያን ዘመን የዚያች ምድር
ነዋሪዎች ከነዓናውያንና ፈሪዛውያን ነበሩ ።
8 ከዚህ በኋላ አብራም ሎጥን እንዲህ
አለው ፥ “እኛ ወንድማማች ስለሆንን በእኔና
በአንተ መካከል እንዲሁም በእኔ እረኞችና በአ
ንተ እረኞች መካከል ጠብ ሊነሣ አይገባም ፤
9 ስለዚህ ተለያይተን ለየብቻ ብንኖር የተሻለ
ነው ፤ ከምድሪቱ የፈለግሽውን መርጠህ ወደ
አንድ በኩል ሂድ ፤ እኔም ወደ ሌላው በኩል
እሄዳለሁ ።”

10 ሎጥ ዙሪያውን በተመለከተ ጊዜ የዮርዳ
ኖስ ሸለቆ እስከ ጾዓር ድረስ እንደ እግዚአብ
ሔር ገነት ወይም እንደ ግብጽ ምድር ውሃ
የሞሳበት መሆኑን አየ ፤ ይህን የተመለከተው
እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች
ከማጥፋቱ በፊት ነበር ። 11 ስለዚህ ሎጥ መሳ
ውን የዮርዳኖስ ሸለቆ ለራሱ መረጠና ወደ

23* 12፡9 ኔጌብ ፡- በዕብራይስጥ "ደቡባዊ አገር" ማለት ነው ።

12፡3 ፡- ገላ. 3፡8 ። 12፡7 ፡- ሐሥ. 7፡5 ፥ ገላ. 3፡16 ። 12፡13 ፡- ዘፍ. 20፡2 ፡ 26፡7 ። 13፡10 ፡- ዘፍ. 2፡10 ።

ምሥራቅ ሄደ ፥ ሁለቱ የተለያዩት በዚህ ሁኔታ
ነበር ፥ 12አብራም በከነዓን ኖረ ፥ ሎጥ ግን በሸ
ለቆው ውስጥ ባሉት ከተሞች መካከል ተቀ
መጠ ፥ በሰዶምም አጠገብ ድንኳኑን ተከለ ፥
13በዚያን ዘመን የሰዶም ሰዎች እጅግ ክፉዎ
ችና እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ ኃጢአተኞች
ነበሩ ።

አብራም ወደ ከብሮን ሄደ

14ሎጥ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር አብራምን
እንዲህ አለው ፥ "ካለህበት ሰፍራ ወደ ሁሉ
አቅጣጫ ዙሪያውን ተመልከት ፥ 15ያለህን የም
ታየውን ምድር ሁሉ ለእንተና ለዘርህ እሰጣትኋ
ለሁ ፥ ለዘላለምም የእናንተ ይሆናል ፥ 16ዘርህን
እንደ ምድር አሸዋ አበዛሞለሁ ፥ የምድር አሸዋ
ሊቈጠር እንደማይቻል ሁሉ የእንተም ዘር እን
ዲሁ ሊቈጠር የማይቻል ይሆናል ። 17እንሆ ፥
አሁን ሂድና ምድሩን ሁሉ ተመልከት ፥ ምክን
ያቱም ሁሉንም ለእንተ አስጥሃለሁ ።"

18ስለዚህ አብራም ድንኳኑን ነቅሎ በኬብ
ሮን የመምሬ የተቀደሱ የወርካ ዛፎች ወደአሉ
በት ሰፍራ ለመኖር ሄዳ ፥ እዚያም ለእግዚአብ
ሔር መሠዊያ ሠራ ።

ምዕራፍ 14

አብራም ሎጥን ከምርኮ ነፃ አወጣው

1በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ አምራፌል ፥
የኤላሳር ንጉሥ አርዮክ ፥ የዔላም ንጉሥ ከዶር
ላዖሜር ፥ የንይም ንጉሥ ቲድዓል ነበሩ ፤ እነ
ዚህ አራቱ ነገሥታት ፥ 2ሴሎችን አምስት ነገ
ሥታት ለመውጋት ሄዱ ፤ የተዘመቱባቸውም
አምስት ነገሥታት የሰዶም ንጉሥ ቤራዕ ፥ የገ
ሞራ ንጉሥ ቢርሻዕ ፥ የአዳማ ንጉሥ ሺንአብ ፥
የሰቦይም ንጉሥ ሼሜቤርና ጾዓር ተብላ የምት
ጠራው የቤላዕ ንጉሥ ነበሩ ። 3እነዚህ አምስቱ
ነገሥታት አንድ ግንባር ፈጥረው አሁን ሙት
ባሕር ተብሎ በሚጠራው በሲዲም ሸለቆ ጦር
ነት ገጠሙ ፤ 4እነዚህ አምስቱ ነገሥታት ሰዐ
ሥራ ሁለት ዓመት በከዶርላዖሜር ቀንጥጥር
ውስጥ ነበሩ ፥ በዐሥራ ሦስተኛው ዓመት ግን
በእርሱ ላይ ዐመፁ ።

5በዐሥራ አራተኛው ዓመት ከዶርላዖሜርና
ከእርሱ ጋር የተባበሩት ነገሥታት ከነሠራዊቶቻ
ቸው መጥተው ረፋያውያንን በዐሽተሮት ቃርና
ይም ፥ ዙዛውያንን በሃም ፥ ኤማውያንን በሻዌ
ቂርያታይም ፥ 6የሖር ሰዎችንም በተራራማው
አገር በሴዒር ፥ በበረሓ አጠገብ እስካለው አስከ
ኤልፋራን ባለው ሰፍራ ድል ነሡአቸው ።
7ከዚያም ተመልሰው ወደ ቃደሽ መጡ ፥ በዚ
ያን ጊዜ የዚህ በታ ሰም ዔይንሚሽፖጥ ይባል
ነበር ። የወማሌቃውያንንም ምድር ሁሉ ያዙ ፥
በሐጸጸንታማር ይኖሩ የነበሩትን አሞራውያን
ንም አሸነፉ ።

8ከዚህ በኋላ የሰዶም ፥ የገሞራ ፥ የአዳማ ፥
የጸቦይምና የቤላዕ ነገሥታት ሠራዊታቸውን
በሲዲም ሸለቆ አሰልፈው ተዋጉ ፤ 9የተዋጉ
ትም ከዔላም ፥ ከንይም ፥ ከባቢሎንና ከኤላሳር
ነገሥታት ጋር ነበር ፥ አምስቱ ነገሥታት ከአ
ራቱ ነገሥታት ጋር የተዋጉት በዚህ ዐይነት
ነበር ። 10በሲዲም ሸለቆ ብዙ የቅጥራን ጉድጓ
ዶች ነበሩ ፥ ስለዚህ የሰዶምና የገሞራ ነገሥ
ታት ከሠርነቱ ሸሽተው ለማምለጥ በሞከሩ ጊዜ
በጉድጓዶቹ ውስጥ ወደቁ ፥ የቀሩት ሦስት ነገ
ሥታት ግን ወደ ተራራዎቹ ሸሹ ። 11አራቱ
ነገሥታት በሰዶምና በገሞራ ያገኙትን ነገር
ሁሉ ምግብ እንኳ ሳይቀር ማርከው ሄዱ ።
12የአብራም የወንድም ልጅ ሎጥ በሰዶም
ይኖር ስለነበር እርሱን ማርከው ፥ ዐብቱንም
ሁሉ ይዘው ሄዱ ።

13ነገር ግን አንድ ሰው ሸሽቶ መሳና የሆነ
ውን ሁሉ ለዕብራዊው ለአብራም ነገረው ፥ በዚ
ያን ጊዜ አብራም የሚኖረው በአሞራዊው
መምሬ የተቀደሱ የወርካ ዛፎች አጠገብ ነበር ፥
መምሬና ወንድሞቹ ኤሽኮል ፥ ዐኔር የአብራም
የጦር ቃል ኪዳን ጓደኞች ነበሩ ። 14አብራም
የወንድሙ ልጅ እንደተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ
ተወልደው የጦር ልምምድ ያላቸውን 318
ሰዎች በትጥቅ አደራጅቶ እራቱን ነገሥታት
በመከታተል እስከ ዳን ድረስ ሄደ ። 15እዚያ
ሰዎቹን በሁድን ከፍሎ ከጠላቶቹ ጋር በሌሊት
ወርነት ገጠመና ድል አደረጋቸው ፤ ከደማስቆ
በስተሰሜን እስከሚገኘው እስከ ሖባ ድረስ አሳ
ደዳቸው ። 16የተወሰደውንም ምርኮ ሁሉ
መልሶ አመጣ ፤ እንዲሁም የወንድሙን ልጅ
ሎጥን ከነ ሀብቱ መልሶ አመጣ ፥ ከእነርሱም
ጋር ሴቶችና ሌሎች አሰረኞች ነበሩ ።

መልከ ጼዴቅ አብራምን ባረከው

17አብራም ከዶርላዖሜርና ከእነርሱ ጋር
አብረው የነበሩትን ነገሥታት ድል አድርጎ
ሲመለስ ፥ የሰዶም ንጉሥ "የንጉሥ ሸለቆ" እየ
ተባለ በሚጠራው በሻዌህ ሸለቆ ሊቀበለው
ወጣ ፤ 18የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው
የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም ለአብራም እን
ጀራና የወይን ጠጅ አመጣለት ፤ 19እንዲህ
ብሎም አብራምን ባረከው ፥

"ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ልዑል
እግዚአብሔር አብራምን ይባርክ ፥
20በጠላቶችህ ላይ ድልን ያቀዳጀህ ፥
ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ
ይሁን ።"

13፥15 ፦ ሐሥ. 7፥5 ። 14፥18-20 ፦ ዕብ. 7፥1-10 ።

አብራምም በምርኮ ካገኘው ሀብት ሁሉ አንድ ወሥረኛውን ሰመልከ ጼዴቅ ሰጠው ።
21 የሰዶምም ንጉሥ አብራምን "በምርኮ
ያገኘኸውን ሀብት ሁሉ ለራስህ ውሰድ ፣ ሰዎ
ቹን ግን መልሰልኝ" አለው ።
22 አብራምም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ "ስማይ
ንና ምድርን በፈጠረ በልዑል እግዚአብሔር
ሰም እምላለሁ ፣ 23 አንተ 'አብራምን ሀብታም
ያደረግሁት እኔ ነኝ' እንዳትል ሌላው ቀርቶ
አንዲት ክር ወይም የጫማ ማሰሪያ እንኳ ከአ
ንተ አልወሰድም ። 24 ስለዚህ ለራሴ ምንም
ነገር አልወስድም ፣ የእኔ ሰዎች የያዙትን እንዲ
ወስዱ እሰማማለሁ ፣ እንዲሁም የመር ቃል
ኪዳን ዓደኞቹ ዐኔር ፥ ኤሽኮልና መምሬ ድርሻ
ቸውን ይውሰዱ ።"

ምዕራፍ 15

እግዚአብሔር ከአብራም ጋር የገባው ቃል ኪዳን

1 ከዚህ በኋላ አብራም ራእይ አየ ፣ እግዚአ
ብሔርም

"አብራም! አትፍራ ፣ እንደ ጋሻ ሆኜ
ከአደጋ ሁሉ እጠብቅሃለሁ ፣
ታላቅ በረከትም እሰጥሃለሁ" ሲል
ስማው ።

2 አብራምም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ "አግዚአ
ብሔር አምላክ ሆይ! ምንም ልጅ ስለሌለኝ
የምትሰጠኝ በረከት ምን ያደርግልኛል? ሀብ
ቴን የሚወርሰው የደማስቆ ሰው የሆነው ኤሊዔ
ዘር ነው ። 3 ምንም ዘር ስላልሰጠኸኝ ሀብቴን
የሚወርሰው ይሄው ከአገልጋዮቼ አንዱ የሆነው
ነው ።"

4 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ይህ ኤሊዔዘር
የተባለው አገልጋይ የአንተን ሀብት አይወር
ስም ፣ ከአንተ የሚወለደው ልጅ ወራሽህ ይሆ
ናል" ብሎ ሊነግረው ሰማ ። 5 ቀጥሎም እግዚአ
ብሔር አብራምን ወደ ውጭ አወጣውና "ወደ
ሰማይ ተመልከት ፣ ከዋክብትን መቁጠር
ትችል እንደሆን ሞክር ፣ እንግዲህ የአንተም
ዝርያዎች እንደዚህ ይበዛሉ" አለው ።

6 አብራም በእግዚአብሔር አመነ ፣ እምነ
ቱም ጻድቅ ሆኖ ተቈጠረለት ።

7 ደግሞም እግዚአብሔር አብራምን "ይህ
ችን አገር በውርስ ለአንተ እንድሰጥህ አር ከም
ትባለው ከከለዳውያን ምድር ያወጣሁህ እግዚአ
ብሔር እኔ ነኝ" አለው ።

8 አብራም ግን "እግዚአብሔር አምላክ
ሆይ! ይህች ምድር የእኔ እንደምትሆን እንዴት
ለማወቅ እችላለሁ?" ሲል ጠየቀ ።

9 እግዚአብሔርም "ሦስት ፥ ሦስት ዓመት
የሆናቸው አንድ ጊደር ፣ አንድ ፍየልና ፣ አንድ
በግ ፣ እንዲሁም ዋኖስና ርግብ አምጣልኝ"
አለው ። 10 አብራምም እነዚህን ሁሉ ወደ እግ
ዚአብሔር አምጥቶ እያንዳንዱን እየቈረጠ በሁ
ለት ከፈለው ፣ የተከፈሉትንም ትይዩ እያርጎ
በሁለት መስመር አስቀመጣቸው ። ወፎቹን ግን
ቈርጦ አልከፈላቸውም ። 11 አሞራዎች የተቈራ
ረጠውን ሥጋ ለመብላት ሲመጡ አብራም አባ
ረራቸው ።

12 የፀሐይ መጥለቂያ ሰዓት እየተቃረበ
ሲሄድ አብራምን ከባድ እንቅልፍ ያዘው ፣
ታላቅ ፍርሃትና ድንጋጤም መጣበት ። 13 እግዚ
አብሔር አብራምን እንዲህ አለው ፣ "ዝርያዎ
ችህ በባዕድ አገር ስደተኞች ይሆናሉ ፣ እዚያም
በባርነትና በጭቈና ለአራት መቶ ዓመት ይኖ
ራሉ ፣ 14 በባርነት የሚገዟቸውን ሕዝብ አቀጣ
ለሁ ፣ ከዚያም በኋላ ብዙ ሀብት ይዘው ከዚያ
አገር ይወጣሉ ። 15 አንተ ግን ብዙ ዘመን ኖረህ
በሰላም ትሞታለህ ፣ በሰላምም ትቀበራለህ ።
16 ዝርያዎችህ ወደዚህ ተመልሰው የሚመጡት
ከአራት መቶ ዓመት በኋላ ነው ፣ እስከዚያ የሚ
ቆዩበትም ምክንያት አሞራውያንን ከኃጢአታ
ቸው ብዛት የተነሣ ቀጥቼ ከዚህ ምድር አስነሣ
ስወጣቸው ድረስ ነው ።"

17 ፀሐይ ጠልቆ በጨለመ ጊዜ የምድጃ
እሳት ጢስና ነበልባል ታየ ፣ በተቈራረጠውም
ሥጋ መካከል አለፈ ። 18 በዚያን ዕለት እግዚአ
ብሔር ለአብራም እንዲህ በማለት ቃል ኪዳን
ገባለት ፥ "ከግብጽ ወንዝ ጀምሮ እስከ ኤፍራ
ጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን ምድር ሁሉ ለዝርያህ
ችህ እሰጣለሁ ፣ 19 እንዲሁም የቄናውያንን ፥
የቀኒዛውያንን ፥ የቃድሞናውያንን ፣ 20 የሒታው
ያንን ፥ የፈሪዛውያንን ፣ የረፋያውያንን ፥ 21 የአ
ሞራውያንን ፥ የከነዓናውያንን ፥ የጌርጌሳውያ
ንን ፥ የኢያቡሳውያንን ምድር እሰጣለሁ ።"

ምዕራፍ 16

አጋርና እስማኤል

1 የአብራም ሚስት ሣራይ ገና ልጅ አልወለ
ደችለትም ነበር ፤ ነገር ግን አጋር የምትባል
አንዲት ግብጻዊት አገልጋይ ነበረቻት ፣ 2 ስለዚህ
ሣራይ አብራምን "እነሆ እግዚአብሔር ልጅ
እንዳልወልድ ከልክሎኛል ፣ ከዚህች ከአገልጋዩ
ጋር የግዘረ ሥጋ ግንኙነት አድርግ ፣ ምናልባት
በእርስዋ በኩል ልጅ አገኝ ይሆናል" አለችው ።
አብራምም ሣራይ ባለችው ነገር ተስማማ ።
3 ስለዚህ ሣራይ ግብጻዊት የሆነች አገልጋይዋን
አጋርን ለአብራም ሚስት እንድትሆነው ሰጠ
ችው ። ይህም የሆነው አብራም በከነዓን ዐሥር

15:5 ፡- ሮም 4:18 ፣ ዕብ. 11:12 ። 15:6 ፡- ሮም 4:3 ፣ ገላ. 3:6 ፣ ያዕ. 2:23 ። 15:12 ፡- ኢዮብ 4:13-14 ።
15:13 ፡- ዘጽ. 1:1-14 ፣ ሐ.ሥ. 7:6 ። 15:14 ፡- ዘጽ. 12:40-41 ፣ ሐ.ሥ. 7:7 ። 15:18 ፡- ሐ.ሥ. 7:5 ።

ዓመት ከኖረ በኋላ ነው ። 4አብራም ከአጋር
ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እደረገ ፤ አረገዘ
ችም ፤ አጋር ማርገዝዋን ባወቀች ጊዜ በግራይ
ላይ ኮራች ፤ ናቀቻትም ።
5ግራይም አብራምን "አጋር እንድትንቀኝ
የምታደርገው እኮ አንተ ነህ ፤ እርሰዋን ለአንተ
የሰጠሁህ እኔ ራሴ ነኝ ፤ እርሰዋ ግን ማርገዝዋን
ካወቀችበት ጊዜ እንሥቶ እኔን መናቅ ጀምራ
ለች ፤ እሁንም ከእኔና ከአንተ ዋፋተኛው ማን
እንደሆነ እግዚአብሔር ይፍረድ" አለችው ።
6አብራምም "መልካም ነው ፤ እርሰዋ የአ
ንቺ እገልጋይ ስለሆነች በቍጥጥርሽ ሥር ናት ፤
የፈለግሺውን ነገር አድርጊ" አላት ። ከዚህ
በኋላ ግራይ አጋርን እጅግ ሰላሠቃየቻት አጋር
ከቤት ወጥታ ኮበለለች ።
7የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን በበረሓ
በሚገኘው በአንድ ምንጭ አጠገብ አገኛት ፤
ይህም ምንጭ ወደ ሹር በሚወስደው መንገድ
ላይ ነበር ። 8መልአኩም "የግራይ እገልጋይ
አጋር ሆይ! ከወዴት መጣሽ ፥ ወዴትስ ትሄጃ
ለሽ?" አላት ።
አርሰዋም "እኔ ከእመቤቴ ከግራይ ሸሽቼ
ነው" አለችው ።
9መልአኩም "ወደ እመቤትሽ ተመለሽና
እገልግያት" አላት ። 10ደግሞም እንዲህ
አላት ፥ "ማንም ሊቈጥረው አሰኪማይችል ድረስ
ዘርሽን አበዛዋለሁ ፤
11 እነሆ ፀንሰሻል ፥ ወንድ ልጅም
ትወልጃለሽ ፤
እግዚአብሔር የሐዘን ለቅሶሽን
ሰምቶ አሰማኤል[24*] ትይዋለሽ ።
12 ነገር ግን እንደ ሜዳ አህያ ይሆናል ፤
ሰውን ሁሉ ይቃወማል ፤
ሰዎችም እርሱን ይቃወሙታል ፤
ዘመዶቹን በመጥላት ተለይቶ
ይኖራል ።"
13አጋርም "በእርግጥ የሚያየኝን እግዚአብ
ሔርን በዐይኔ እይቼ በሕይወት ኖርሁን?" በማ
ለት ያነጋገራትን ጌታ "ኤልሮኢ" አለችው ፤
ትርጕሙም "የሚያየኝ አምላክ" ማለት ነው ።
14ስለዚህ ሰዎች በቃዴሰና በባሬድ መካከል
የሚገኘውን የውሃ ጕድጓድ "ብኤር ላሐይ
ሮኢ" ብለው ይጠሩታል ፤ ትርጕሙም
"ሕያው የሆነውና የሚያየኝ አምላኬ
ጕድጓድ" ማለት ነው ።
15አጋር ለአብራም ወንድ ልጅ ወለደች
ለት ፤ አርሰዋ የወለደችለትንም ልጅ "አሰማ
ኤል" ብሎ ሰም አወጣለት ፤ 16አብራም በዚ
ያን ጊዜ 86 ዓመት ሆኖት ነበር ።

ምዕራፍ 17

መገረዝ የቃል ኪዳን ምልክት ስለመሆኑ

1አብራም 99 ዓመት በሆነው ጊዜ እግዚአ
ብሔር ተገለጠለትና "እኔ ኤልሻዳይ - ሁሉን
የምችል አምላክ ነኝ ፤ ለእኔ በመታዘዝ ዘወትር
ትከከል የሆነውን ነገር አድርግ ፤ 2ከአንተ ጋር
ቃል ኪዳን እገባለሁ ዘርህንም እጅግ አበዛዋ
ለሁ" አለው ። 3አብራም ግንባሩ መሬት እስኪ
ነካ ድረስ ዝቅ ብሎ ሰገደ ፤ እግዚአብሔርም
እንዲህ አለው ፥ 4"ከአንተ ጋር የምገባው ቃል
ኪዳን ይህ ነው ፤ የብዙ ሕዝቦች አባት አደርግሃ
ለሁ ፤ 5የብዙ ሕዝቦች አባት ስለምደርግህም
ከአንግዲህ ወዲህ ሰምህ አብራም መሆኑ ቀርቶ
አብርሃም[25*] ይሆናል ። 6እጅግ ብዙ ሕዝቦች
አሰኪሆኑ ዝርያዎችህን አበዛቸዋለሁ ፤ ከእነር
ሱም መካከል ነገሥታት የሚሆኑ ይገኛሉ ።
7"በእንተና በዘርህ ፥ በመጪውም ትውልድ
መካከል ቃል ኪዳኔን ለዘላለም እጸናለሁ ፤ በዚ
ህም ዐይነት ለአንተና ከአንተ በኋላ ለሚመ
ጣው ዘርህ አምላክ እሆናለሁ ። 8እሁን በእንግ
ድነት የምትኖርባትን ይህችን ምድር ለአንተና
ለዘርህ እሰጣችኋለሁ ፤ መላውን የከነዓን ምድር
ለዘላለም አንዲወርሱት ለዘርህ እሰጣለሁ ፤
እኔም አምላካቸው እሆናለሁ ።"
9እንደገናም እግዚአብሔር አብርሃምን እን
ዲህ አለው ፥ "አንተና ከአንተም በኋላ የሚመ
ጣው ዘርህ ከእኔ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን
ከትውልድ እስከ ትውልድ ጠብቁ ፤ 10እንተና
ከአንተ በኋላ የሚመጣው ዘርህ የምትጠብቁት
ቃል ኪዳን ይህ ነው ፤ በመካከላችሁ ያሉት
ወንዶች ሁሉ መገረዝ አለባቸው ፤ 11የብልታች
ሁን ሽለፈት ትገረዛላችሁ ፤ ይህም በእኔና በአና
ንተ መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምልክት ይሆ
ናል ፤ 12በመጪው ዘመን የሚወለድ ወንድ
ልጅ ሁሉ በተወለደ በሰምንተኛው ቀን ይገ
ረዝ ፤ እንዲሁም በቤትህ የተወለዱና በቤትህ
ሳይወለዱ ከውጭ በገንዘብ ተገዝተው የመጡ
ባሪያዎች ሳይቀሩ በዚሁ ዐይነት ይገረዙ ።
13ቃል ኪዳኔ ለዘላለም ከእናንተ ጋር የሚኖር
መሆኑን የሚያሳይ የሥጋ ምልክት እንዲሆን
እያንዳንዱ ወንድ ይገረዝ ። 14ያልተገረዘ ወንድ
ሁሉ ቃል ኪዳኔን ስላላከበረ ከወገኖቹ እንደ
እንዱ ሆኖ እይቈጠርም ።"
15እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው ፥
"ከአንግዲህ ወዲህ ሚስትህን ግራይ ብለህ

24* 16፥11 አሰማኤል ፦ በዕብራይስጥ "እግዚአብሔር ይሰማል" ማለት ነው ። 25* 17፥5 አብርሃም ፦ በዕብራይስጥ "የብዙዎች አባት" ማለት ነው ።
16፥15 ፦ ገላ. 4፥22 ። 17፥5 ፦ ሮም 4፥17 ። 17፥7 ፦ ዘፅ. 1፥55 ። 17፥8 ፦ ሐሥ. 7፥5 ። 17፥10 ፦ ሐሥ. 7፥8 ፤ ሮም 4፥11 ።

አትጥራት ፤ ከዛሬ ጀምሮ የእርሰዋ ሰም ሣራ[26*] ነው ። [16]እርሰዋን እባርካታለሁ ፤ ከእርሰዋም ወንድ ልጅ እሰዋሃለሁ ፤ እባርካታለሁ ፤ የብዙ ሕዝቦችም እናት ትሆናለች ፥ ከዘርዋም መካከል ነገሥታት የሚሆኑ ይገኛሉ ።”

[17]አብርሃም ግንባሩ መሬት እስኪነካ ድረስ ዝቅ ብሎ ሰገደ ፤ ነገር ግን “ዕድሜው መቶ ዓመት የሆነው ሰው ልጅ መውለድ ይችላልን? ሣራስ በዘጠና ዓመትዋ ልጅ ልትወልድ ትችላለችን?” ብሎ በማሰብ ሳቀ ፤ [18]እግዚአብሔር ንም “እስማኤልንስ ብትባርከው ወራሼ ሊሆን አይችልምን?” አለው ።

[19]እግዚአብሔርም እንዲህ አለው ፥ “እንዲህ አይሆንም ፤ ነገር ግን ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ፤ ስሙንም ይስሐቅ[27*] ትለዋለህ ፤ ቃል ኪዳኔን ከእርሱና ከዘሩ ጋር ለዘላለም አጸናለሁ ፤ [20]ስለ እስማኤል ያቀረብኸው ንም ልመና ሰምቻለሁ ፤ እርሱንም እባርከዋለሁ ፤ ብዙ ልጆችን እሰጠዋለሁ ፤ ዘሩንም እጅግ አበዛዋለሁ ፤ እርሱ የዐሥራ ሁለት መሳፍንት አባት ይሆናል ፤ ዘሩንም ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ ። [21]ነገር ግን የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ከሣራ ከሚወለደው ልጅህ ከይስሐቅ ጋር ቃል ኪዳኔን አጸናለሁ ።” [22]እግዚአብሔር አብርሃምን ካነጋገረው በኋላ ከእርሱ ተሰይቶ ወደ ላይ ወጣ ።

[23]እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት አብርሃም በዚያኑ ቀን ልጁን እስማኤልን ገረዘው ፤ እንዲሁም በቤቱ ውስጥ የተወለዱና ከውጭ የተገዙ ባሪያዎች ላይቀሩ ፥ በቤቱ ያሉትን ወንዶች ሁሉ ገረዘ ፥ [24]አብርሃም ሲገረዝ ዕድሜው 99 ዓመት ነበር ። [25]ልጁ እስማኤል በተገረዘ ጊዜ 13 ዓመት ሆኖት ነበር ፤ [26]ሁለቱም የተገረዙት በአንድ ቀን ነበር ። [27]በቤቱ የተወለዱና ከውጭ የተገዙ ባሪያዎች ሳይቀሩ ወንዶች ሁሉ ከአብርሃም ጋር ተገረዙ ።

ምዕራፍ 18

የሦስቱ እንግዶች ጉብኝትና አብርሃም ወንድ ልጅ ለማግኘት የተሰጠው ተስፋ

[1]በተቀደሱት በመምሬ የወርካ ዛፎች አጠገብ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት ፤ የተገለጠለትም በዚህ ሁኔታ ነበር ፤ ከዕለታት አንድ ቀን በቀትር ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ነበር ፤ [2]ቀና ብሎም ሲመለከት ሦስት ሰዎች እዚያ ቆመው አየ ፤ እንዳያቸው መዳያ ውኑ ሊያነጋግራቸው ወደ እነርሱ ሮጠ ፥ ግንባሩም መሬት እስኪነካ ዝቅ ብሎ በመስገድ እጅ ነሣ ፤ [3]እንዲህም አለ ፥ “ጌታዬ ሆይ! በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ፥ አልፈኸኝ እንዳትሄድ አሰምንሃለሁ ፤ እነሆ እኔ ሳስተናግድህ ዝግጁ ነኝ ። [4]እግራችሁን የምትታጠቡበት ውሃ እስካ መጣሰችሁ ድረስ በዚህ ዛፍ ጥላ ሥር ዐረፍ በሉ ፤ [5]ወደ እኔ ወደ አገልጋያችሁ በመምጣታችሁ ደስ ብሎኛል ፤ ስለዚህ ለጉዞአችሁ ብርታት የሚሰጣችሁን ጥቂት ምግብ እምጥቼ እን ዳስተናግዳችሁ ፍቀዱልኝ ።”

እነርሱም “መልካም ነው ፤ እንዳልከው አድርግ” አሉት ።

[6]አብርሃም ወደ ድንኳኑ ሮጦ ሄደና ሣራን “ቶሎ ብለሽ ሦስት መስፈሪያ ዱቄት ውሰጂና አቡክተሽ እንጀራ ጋግሪ” አላት ። [7]ከዚህ በኋላ አብርሃም ወደ መንጋው ሄደና ለግሏጋውንና መልካሙን ወይፈን መርጦ ለአገልጋዩ ሰጠው ፤ አገልጋዩም በፍጥነት ወርዶ አወራርዶ አዘጋ ጀው ፤ [8]አብርሃም እርጎ ፥ ወትትና ሥጋ ይዞ ሄደና ምግቡን ለእንግዶቹ አቀረበላቸው ፤ እነ ርሱ ምግቡን በሚበሉበት ጊዜ አብርሃም ከዛፉ ሥር አጠገባቸው ቆሞ ያስተናግዳቸው ነበር ።

[9]እነርሱም “ሚስትህ ሣራ የት አለች?” አሉት ።

እርሱም “እዚያ ድንኳኑ ውስጥ ነች” አላ ቸው ።

[10]ከሦስቱም እንግዶች አንዱ አብርሃምን “የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ተመልሼ እመጣለሁ ፤ በዚያን ጊዜ ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልዳ ለች” አለው ።

እርሱም ይህን በሚናገርበት ጊዜ ፥ ሣራ በስተኋላው በድንኳኑ ደጃፍ ቆማ ታዳምጥ ነበር ፤ [11]አብርሃምና ሣራ በዕድሜአቸው መግ ፋት እርጅተው ነበር ፤ የሣራም የወር አበባ ተጽርጦ ነበር ። [12]ስለዚህ ሣራ “እኔ አሁን እን ዲህ ካረጀሁና ከደከምሁ በኋላ ከወንድ ጋር የሥጋ ፍትወት መፈጸም እችላለሁን? ከዚህም በቀር ጌታዬ አብርሃም በጣም አርጅቶአል” ብላ በማሰብ ሳቀች ።

[13]እግዚአብሔርም አብርሃምን “ሣራ ‘እንደ ዚህ ካረጀሁ በኋላ ልጅ መውለድ እችላለሁን?’ በማለት ስለምን ሳቀች? [14]ኩቶ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? እንደነገርኩህ የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ተመልሼ እመጣለሁ ፤ በዚያን ጊዜ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች” አለው ።

[15]ሣራ እጅግ ፈርታ ስለነበር “አልሳቅ ሁም” ብላ ካደች ።

እርሱ ግን “በእርግጥ ሰቀኻል” አላት ።

አብርሃም ስለ ሰዶም ያቀረበው ምልጃ

[16]ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ለመሄድ ተነሡ ፤ ሰዶ ምን ቁልቁል ወደሚያዩበት ሰፍራም ደረሱ ፤

[26*] 17፥15 ሣራ ፦ በዕብራይስጥ “ልዕልት” ማለት ነው ። [27*] 17፥19 ይስሐቅ ፦ በዕብራይስጥ “ይስቃል” ማለት ነው ።
[18፥2 ፦ ዕብ. 13፥2 ። 18፥10 ፦ ሮም 9፥9 ። 18፥12 ፦ 1ጴጥ. 3፥6 ። 18፥14 ፦ ሉቃ. 1፥37 ።

አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ፤
17 እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፥ “እኔ የማደርገውን ነገር ከአብርሃም አልሰውርም፤ 18 የአብርሃም ዘር ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናል፤ በእርሱም አማካይነት በምድር ላይ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ። 19 ቅንና ትክክል የሆነውን ነገር በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲጠብቁ ልጆቹንና ቤተሰቡን በመምከር ይመራቸው ዘንድ እኔ እርሱን መርጨዋለሁ፤ ልጆቹ ይህን ካደረጉ እኔም ለአብርሃም የሰጠሁትን ተስፋ ሁሉ እፈጽማለሁ።”

20 ቀጥሎም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፥ “የሰዶምና የገሞራ ሕዝብ የሚፈጽሙትን በደል ሰምቻለሁ፤ ኃጢአታቸውም እጅግ ከባድ ነው፤ 21 ስለ እነርሱ የሰማሁት ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ እነርሱ እወርዳለሁ።”

22 ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሰዎች ወደ ሰዶም ለመሄድ ተነሡ፤ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት እንደቆመ ቆይቶ ስለነበር፥ 23 ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ እንዲህ አለ፤ “በእርግጥ በደል የሌለባቸውን ደጋግ ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር ታጠፋለህን? 24 በከተማይቱ ውስጥ ኀምሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ከተማይቱን ይሙሉ ትደመሰሳለህን? ስለ ኀምሳው ደጋግ ሰዎች ስትል ከተማይቱ እንዳትጠፋ አታደርግ ምን? 25 በደል ያልሠሩትን ደጋግ ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር ታጠፋለህ ብዬ አላሰብም፤ ይህንን እንደማታደርገው አምናለሁ፤ ይህንንማ ካደረግህ ደጋግ ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር መቀጣታቸው ነው፤ ይህ ከቶ አይሆንም! የዓለም ሁሉ ፈራጅ በትክክል መፍረድ ይገባው የለምን?”

26 እግዚአብሔርም “በሰዶም ከተማ ውስጥ በደል ያልሠሩ ኀምሳ ደጋግ ሰዎች ባገኝ ለእነርሱ ስል ከተማይቱን ፈጽሞ አላጠፋም” አለ።

27 አብርሃም እንደገና እንዲህ አለ፥ “እኔ ትቢያና ዐመድ የሆንሁ ከንቱ ሰው፤ ከጌታዬ ጋር በድፍረት በመነጋገሬ ይቅር በለኝ፤ 28 ነገር ግን የደጋግ ሰዎች ቍጥር ኀምሳ መሆኑ ቀርቶ አርባ አምስት ቢሆን፥ አምስት ስለጐደለ ከተማይቱን በሙሉ ታጠፋለህን?”

እግዚአብሔርም “አርባ አምስት ደጋግ ሰዎች ባገኝ ከተማይቱን አላጠፋም” አለ።

29 አብርሃምም “አርባ ብቻ እዚያ ቢገኙስ?” ብሎ እንደገና ጠየቀ።

እግዚአብሔርም “አርባ ቢገኙ ለእነርሱ ስል ከተማይቱን አላጠፋም” አለ።

30 አብርሃምም “እግዚአብሔር ሆይ፤ አባክህ አትቈጣ፤ እንደገና ልናገር፤ ምናልባት ሠላሳ ብቻ ቢገኙስ?” አለ።

እግዚአብሔርም “ሠላሳ ቢገኙ ለእነርሱ ስል ከተማይቱን አላጠፋም” አለ።

31 አብርሃምም “እግዚአብሔር ሆይ! አሁንም እንደገና በመናገሬ ይቅር በለኝ፤ ምናልባት ሃያ ቢገኙስ?” አለ፤

እግዚአብሔርም “ሃያ ቢገኙ ለእነርሱ ስል ከተማይቱን አላጠፋም” አለ።

32 አብርሃምም “እግዚአብሔር ሆይ! አባክህ አትቈጣ አንድ ጊዜ ልናገር፤ ዐሥር ብቻ ቢገኙስ?” አለ።

እግዚአብሔርም “ዐሥር ቢገኙ ለእነርሱ ስል ከተማይቱን አላጠፋም” አለ። 33 እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ተነጋግሮ ካበቃ በኋላ ከዚያ ስፍራ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ምዕራፍ 19

የሰዶም ኃጢአት

1 በዚያኑ ምሽት ሁለቱ መላእክት ወደ ሰዶም መጡ፤ በዚያን ጊዜ ሎጥ በከተማይቱ በር ተቀምጦ ነበር፤ መላእክቱን ባያቸው ጊዜ ሊያነጋግራቸው ከተቀመጠበት ተነሥቶ ሄደ፤ ጐንበስ ብሎም እጅ ነሣቸውና፥ 2 “ጌቶቼ ሆይ! ተቀብዬ ላስተናግዳችሁ ዝግጁ ነኝ፤ እባካችሁ ወደ ቤቴ ግቡ፤ እግራችሁንም ታጥባችሁ እዚሁ አደሩ፤ ጠዋት በማለዳ ተነሥታችሁ ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ” አላቸው።

እነርሱ ግን “እይሆንም! እኛ እዚሁ በከተማይቱ አደባባይ እናድራለን” አሉት።

3 ነገር ግን ወደ ቤቱ እንዲገቡ አጥብቆ ስለለመናቸው፥ ከእርሱ ጋር ወደ ቤቱ ገቡ፤ ከዚህም በኋላ ሎጥ እንጀራ ጋግሮው መልካም ራት እንዲያዘጋጁ ለእነልጋዮቹ ነገራቸው፤ ራትም በተዘጋጀ ጊዜ እንጣዶቹ በሉ።

4 እንግዶቹ ከመተኛታቸው በፊት የሰዶም ሰዎች ቤቱን ከበቡት፤ ወጣቶችና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ የከተማይቱ ወንዶች ሁሉ እዐያ ተሰበሰቡ። 5 ሎጥንም ጠርተው “ከእንተ ጋር ለማደር ወደዚህ የገቡት ሰዎች የት አሉ? ከእነርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ሰለምንፈልግ ወደ እኛ አውጣቸው!” አሉት።

6 ሎጥ ግን ወደ ውጭ ወጥቶ በሩን ከበስተኋላው ዘጋው፤ 7 እንዲህም አላቸው “ወዳጆቼ ሆይ! አባከችሁ ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ! 8 እነሆ፤ ሁለት ያላገቡ ሴቶች ልጆች አሉኝ፤ እነርሱን ወደ እናንተ ላምጣላችሁና በእነርሱ ላይ የፈለጋችሁትን ነገር አድርጉ፤ በእነዚህ ሰዎች ግን ምንም ነገር አታድርጉ፤ እነርሱ የእኔ እንግዶች ስለሆኑ ልጠነቀቅላቸው ይገባኛል።”

19:5-8 ፡- ሥሳ. 19:22-24።

9ሰዎቹ ግን "አንተ ስደተኛ ፣ ሂድ ወዲያ! ለመሆኑ ልናደርገው የሚገባንን ነገር የምትነግረን አንተ ማን ነህ? ሂድ ወዲያ! አለበለዚያ በእነርሱ ላይ ልናደርግ ካሰብነው የከፋ ነገር በእንተ ላይ እናደርጋለን" አሉት ። በዚህ ብያ ኔት ሎጥን ወዲያ ገፍትረው በሩን ለመስበር ተነሣሡ ፣ 10ከዚቱ ውስጥ ያሉት ሁለቱ እንግ ዶች ግን እጆቻቸውን ወደ ውጭ አውጥተው ሎጥን ሰበው ወደ ቤቱ ውስጥ አስገቡትና በሩን ዘጉ ፣ 11ከዚያ በኋላ ውጭ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በሩን ማየት እንዳይችሉ ሀይናቸውን እሳ ወሩአቸው ።

ሎጥ ሰዶምን ለቆ ወጣ

12ሁለቱም እንግዶች ሎጥን እንዲህ አሉት ፡ "በዚህች ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ወንዶ ችና ሴቶች ልጆችህ ፡ የልጆችህ አጮኛዎችና ሌሎች ዘመዶች ቢኖሩህ ከዚህች ከተማ በፍጥ ነት እንዲወጡ አድርግ ፣ 13ምክንያቱም ይህ ችን ከተማ ልናጠፋት ነው ፤ የእነዚህ ሰዎች ኃጢአት እጅግ መብዛቱን እግዚአብሔር ሰምቶ አል ፤ ስዶምንም እንድናጠፋ ልኮናል ።"

14ከዚህ በኋላ ሎጥ ሴቶች ልጆቹን ወዳጨአ ቸው ሰዎች ቤት ሄደና "ቶሎ ብላችሁ ከዚህ ውጡ! እግዚአብሔር ይህን ስፍራ ሊደመስሰው ነው" አላቸው ፤ እነርሱ ግን የሚቀልድ መስሎ አቸው ቸል አሉ ።

15በማግሥቱ ጠዋት በማለዳ መላእክቱ ሎጥን "ፍጠን! ከተማይቱ ስትጠፋ አብሯችሁ እንዳትጠፉ ሚስትህንና ሁለቱን ሴቶች ልጆች ህን ይዘህ ከዚህ ውጣ" እያሉ አጣደፉት ። 16ሎጥ ግን አመነታ ፤ ሆኖም እግዚአብሔር ለእርሱና ለዜተለበ ለለ ራራ መላእክቱ ሎጥንና ሚስቱን ፡ ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን ፡ እጅቻቸ ውን ይዘው ከከተማዋ እንዲያወጡአቸው አደ ረገ ። 17ካወጡአቸውም በኋላ ከመላእክቱ አንዱ "ሕይወታችሁን አድኑ! ወደ ኋላ አትመ ልከቱ! በሸለቆው ውስጥ አትዘግዩ ፤ እንዳት ሞቱ ወደ ተራራው ሽሹ" አላቸው ።

18ሎጥ ግን እንዲህ አላቸው ፡ "ጌቶቼ ፡ እባ ካችሁ ወደዚያ እንድንወጣ አታደርጉ ፤ 19እኔ አገልጋያችሁ በፊታችሁ ሞገስ ስላገኘሁ ሕይወ ቴን ስማዳን ታላቅ ዕርዳታ አድርጋችሁልኛል ፤ ነገር ግን ይህ ጥፋት ደርሶብኝ እሞታለሁ ብዬ ስለምሰጋ ወደዚያ ተራራ መሸሽ አልችልም ። 20እኔ በፍጥነት ሸሽቼ ላመልጥበት የምችል እነሆ አንዲት ትንሽ ከተማ በቅርብ አለች ፤ ስለ ዚህ ሸሽቼ ወደ እርሷ እንድሄድ ፍቀዱልኝ ፤ እንደምታዩአት ትንሽ ከተማ ናት ፤ ወደ እር ስዋ ብሄድ ሕይወቴ ከጥፋት ይድናል ።"

21መልአኩም "እሺ እንተ ባልከው እስማማ ለሁ ፤ ይህችን አንተ የምትላትን ከተማ አላጠፋ ትም ፤ 22ወደዚያች ከተማ እስከምትደርስ ምንም ማድረግ ስለማልችል ፈጥነህ ወደ እር ስዋ ሽሽ" አለው ። ሎጥ ያችን ከተማ ትንሽ ብሎአት ስለነበር ጾዓር28* ተባለች ።

የሰዶምና የገሞራ መደምሰሰ

23ሎጥ ወደ ጾዓር ሲደርስ ገና ፀሐይ መው ጣትዋ ነበር ፤ 24እግዚአብሔር በሰዶምና በገ ሞራ ከተሞች ላይ እሳትና ዲን ከራሱ (ከእግዚ አብሔር ዘንደ) ከሰማይ አዘነመ ። 25በዚህ ዐይ ነት እንዚያን ከተሞችና ሸለቆዎች ፡ እዚያ የሚ ኖሩትን ሰዎች ሁሉ ፡ በምድሩም ላይ የበቀለ ውን ነገር ሁሉ ደመሰሰ ። 26የሎጥ ሚስትም ወደ ኋላዋ ስለተመለከተች የጨው ሀምድ ሆና ቀረች ።

27አብርሃም በማግሥቱ ማለዳ ተነሥቶ ከዚህ ቀደም ከእግዚአብሔር ጋር ወደተገናኘ በት ቦታ ሄደ ። 28ወደ ስዶምና ወደ ገሞራ ወደ ሸለቆውም ቁልቁል በተመለከተ ጊዜ ከታ ላቅ ምድጃ እንደሚወጣ ጢስ ከባድ የእሳት ጢስ ከዚያ ሲወጣ አየ ። 29ሎጥ ይኖርባቸው የነበሩትን ፡ በሸለቆ የሚገኙትን ከተሞች ፡ እግ ዚአብሔር ባጠፋ ጊዜ አብርሃምን አስታወሰ ፤ ስለዚህም ሎጥን ከጥፋት ወደሚድንበት ቦታ መረው ።

የሞአባውያንና የዐሞናውያን ዝርያዎች አመጣጥ

30ሎጥ በጾዓር መቀመጥ ስለፈራ እርሱና ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ወደ ተራራዎቹ ወጥተው መኖሪያቸውን በዋሻ ውስጥ አደረጉ ። 31አንድ ቀን ታላቂቱ ልጅ እኅቶዋን እንዲህ አለቻት ፡ "አባታችን ሣርጀቱ ነው ፤ ልጆች እንድንወ ልድ እኛን የሚያገቡ ወንዶች በዙሪያችን የሉም ፤ 32ከእርሱ ጋር ተኝተን ከእርሱ ልጆች እንድናገኝ አባታችንን የወይን ጠጅ አጠጥተን እናስከረው ።" 33በዚያን ምሽት አባታቸውን የወይን ጠጅ አጠጥተው አስከሩት ፤ ታላቂቱ ልጅም ከእርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደ ረገች ። ሎጥ ግን በጣም ስክሮ ስለነበር ስትተ ኛም ሆነ ስትነሣ አላወቀም ።

34በማግሥቱ ታላቂቱ ልጅ እኅቷን "ትና ንት ማታ እኔ ከእርሱ ጋር ተኝቻለሁ ፤ ዛሬም እንደገና የወይን ጠጅ አጠጥተን እናስከረውና

28* 19:22 ጾዓር ፦ በዕብራይስጥ "ትንሽ" ማለት ነው ።

19:11 ፦ 2ነገ. 6:18 ። 19:16 ፦ 2ጴጥ. 2:7 ። 19:24-25 ፦ ማቴ. 10:15 ፤ 11:23-24 ፤ ሉቃ. 10:12 ፤ 17:29 ፤ 2ጴጥ. 2:6 ፤ ይሁዳ 7 ። 19:26 ፦ ሉቃ. 17:32 ።

አንቺም አብረሽው ተኚ ፤ በዚህ ወይነት ሁለታችንም ከአባታችን ልጆች ወልደን ዘራችን እንዳ ይጠፋ አናድርግ” አለቻት ። 35 ስለዚህ በዚያን ምሽት አባታቸውን አንደገና የወይን ጠጅ አጠ ጥተው አሰከሩት ፤ ታናሽቱ ልጁም ከእርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገች ፤ አሁንም እጅግ ሰክሮ ስለነበር ስትተኛም ሆነ ስትነሣ አላወቀም ። 36 በዚህ ሁኔታ ሁለቱም የሎጥ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው አረገዙ ። 37 ታላቂቱ ወንድ ልጅ ወለደችና ስሙን ሞአብ29* አለ ችው ፤ እርሱ ዛሬ ሞአባውያን ተብለው ሰሚጠ ሩት ሕዝቦች ቅድመ አያት ነው ። 38 ታናሽ ቱም ወንድ ልጅ ወለደችና ስሙን ቤንዐሚ30* አለችው ፤ እርሱ ዛሬ ዐሞናውያን ተብለው ሰሚ ጠሩት ሕዝቦች ቅድመ አያት ነው ።

ምዕራፍ 20

አብርሃምና አቢሜሌክ

1 አብርሃም በመምሬ የነበረውን መኖሪያውን ለቆ ወደ ኔጌብ ሄደ ፤ በቃዴስና በሹር መካከ ልም ተቀመጠ ፤ በገራርም በእንግድነት በተቀ መጠበት ጊዜ ፥ 2 አብርሃም ሚስቱን ሣራን አኅቴ ናት አለ ፤ ስለዚህ የገራራ ንጉሥ አቢሜ ሌክ ሰዎች ልኮ ሣራን አንዲያመጡለት አደ ረገ ። 3 ነገር ግን አንድ ሌሊት አግዚአብሔር በሕልም ተገልጦ አቢሜሌክን “ይህች ሴት ባለ ባል ስለሆነች አርስዋን በመውሰድህ ምክንያት ትሞታለህ” አለው ።

4 ሆኖም አቢሜሌክ ገና ወደ አርስዋ አልቀረ በም ነበርና አንዲህ አለ ፥ “ጌታ ሆይ! አኔ ምንም በደል አልፈጸምኩም ፤ ታዲያ አኔንና ሕዝቤን ታጠፋለህን? 5 አኅቴ ነች ያለኝ ራሱ አብርሃም ነው ፤ እርስዋም ወንድሜ ነው ብላኛ ለች ፤ አኔ ይህን ያደረግሁት በቅንነትና በንጹሕ ኅሊና ስለሆነ ምንም በደል አልፈጸምኩም” አለ ።

6 አግዚአብሔርም በሕልም አንዲህ አለው ፥ “በንጹሕ ኅሊና አንዳደረግህ ዐውቄአለሁ ፤ ወደ አርስዋ ቀርበህ በአኔ ፊት ኃጢአት አንዳትሠራ ያደረግሁህም ስለዚህ ነው ። 7 አሁን ግን ሴቲ ቱን ስባሏ መልሰህ ስጥ ፤ አርሱ ነቢይ ስለሆነ እንዳትሞት ይጸልይልሃል ፤ አርስዋን መልሰህ ባትሰጥ ግን እንደምትሞት ዕወቅ! አንተ ብቻ ሳትሆን ሕዝብህም በሙሉ ታልቃላችሁ ።”

8 በማግሥቱ ጠዋት በማለዳ አቢሜሌክ ባለሟሎቹን ጠርቶ የሆነውን ነገር ሁሉ በተረከ ላቸው ጊዜ ደነገጡ ። 9 ከዚህ በኋላ አቢሜሌክ አብርሃምን ጠርቶ “ይህ ያደረግህብን ነገር ምን ድን ነው? በአኔና በመንግሥቴ ላይ ይህን በደል ያመጣህብኝ ምን ያስቀየምኩህ ነገር ቢኖር ነው? አንተ ያደረግህብኝን ነገር ከቶ ማንም ሰው አያደርገውም ፤ 10 ለመሆኑ ይህን አንድታ ደርግ ያስገደደህ ምንድን ነው?”

11 አብርሃምም አንዲህ ሲል መለሰ ፥ “‘አዚህ ቦታ አግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው የለም’ ብዬ በማሰብ ‘ሚስቴን ስመውሰድ በመ ፈለግ ይገድሉኛል’ ብዬ ስለ ሰጋሁ ነው ፤ 12 ደግሞም እርስዋ የአባቴ ልጅ ስለሆነች በእር ግጥ እኅቴ ናት ፤ ነገር ግን የአናቴ ልጅ ስላልሆ ነች አገዛኋት ። 13 ስለዚህ አግዚአብሔር ከአባቴ ቤት ወጥቼ ወደ ባዕድ አገር አንድሄድ ባዘዘኝ ጊዜ ‘በምንሄድበት ቦታ ሁሉ አኅቴ ነኝ ብትይ ለአኔ ታላቅ ውለታ አንዳደረግሽልኝ አቁጥሪዋ ለሁ’ ብያት ነበር ።”

14 ከዚህ በኋላ አቢሜሌክ ሣራን ለአብርሃም መልሶ ሰጠው ፤ አንዲሁም በጎችና ከብቶች ፥ አገልጋዮችም ሰጠው ። 15 አብርሃምን “እነሆ የአኔ ግዛት በፊትህ ነው ፤ በፈለግኸው ስፍራ ኑር” አለው ። 16 ሣራንም “አንቺ ምንም አስነ ዋሪ ተግባር ያልፈጸምሽ ንጹሕ መሆንሽን ከአ ንቺ ጋር ያሉት ሰዎች ሁሉ አንዲረዱት ምል ከት ይሆን ዘንድ ለወንድምሽ ለአብርሃም አንድ ሺ ብር ሰጥቼዋለሁ” አላት ።

17-18 በአብርሃም ሚስት በሣራ ላይ በሆነው ነገር ምክንያት በአቢሜሌክ ቤተ መንግሥት የሚኖሩትን ሴቶች ሁሉ አግዚአብሔር ልጅ አንዳይወልዱ አድርጎአቸው ነበር ፤ ስለዚህ አብ ርሃም ለአቢሜሌክ ጸሰየሰት ፤ አግዚአብሔርም አቢሜሌክን ፈወሰው ፤ ሚስቱንና ሴቶች አገል ጋዮቹንም ስለፈወሳቸው ልጆች ስመውሰድ ቻሉ ።

ምዕራፍ 21

የይስሐቅ መወለድ

1 ለአብርሃም በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት አግዚአብሔር ሣራን ባረካት ፤ 2 ስለዚህም አር ግዛ በአርጅናው ጊዜ ለአብርሃም ወንድ ልጅ መለደችለት ፤ ልጁም የተወለደው “በዚህ ጊዜ ይወለዳል” ብሎ አግዚአብሔር በተናገረበት ጊዜ ነው ። 3 አብርሃም ሚስቱ ሣራ የወለደችለ ትን ልጅ “ይስሐቅ” ብሎ ስም አወጣለት ፤ 4 ይስሐቅ ከተወለደ ከስምንት ቀን በኋላ አግዚአ ብሔር ባዘዘው መሠረት አብርሃም ገረዘው ። 5 ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ አብርሃም መቶ ዓመት ሆኖት ነበር ። 6 ሣራ “አግዚአብሔር ደስታና ሳቅ አመጣልኝ ፤ ስለዚህ ይህንን ነገር የሚሰማ ሁሉ ከእኔ ጋር ይስቃል” አለች ። 7 ቀጥላም ““ሣራ ለአብርሃም ልጅ ወልዳ ታጠባለች’

29* 19:37 ሞአብ ፦ በዕብራይስጥ "ከአባቱ የተወለደ" ማለት ነው ።

30* 19:38 ቤንዐሚ ፦ በዕብራይስጥ "የወገኔ ልጅ" ማለት ነው ።

20:2 ፦ ዘፍ. 12:13 ፤ 26:7 ። 21:2 ፦ ዕብ. 11:11 ። 21:4 ፦ ዘፍ. 17:12 ፤ ሐ.ሥ. 7:8 ።

ብሎ የሚናገር ከቶ ማን ነበር! አሁን ግን እነሆ በእርጅናው ዘመን ወንድ ልጅ ወለድሁለት” አለች።

8 ልጁም እድጎ ጡት መጥባት ተወ፤ ጡት ባስጣሉበትም ቀን አብርሃም ታላቅ ግብዣ አደረገ።

የአጋርና የእስማኤል መባረር

9 ግብጻዊትዋ አጋር ለአብርሃም የወለደችለት እስማኤል ከዕለታት አንድ ቀን ከሣራ ልጅ ከይስሐቅ ጋር ይጫወት ነበር፤ 10 ሣራም ልጆቹ ሲጫወቱ አየችና አብርሃምን “ይህችን አገልጋይ ከነልጅዋ ወዲያ አባርልኝ፤ የዚህች አገልጋይ ልጅ ከልጄ ከይሰሐቅ ጋር አብሮ መውረስ አይገባውም” አለችው። 11 እስማኤልም ልጁ ስለሆነ ይህ ጕዳይ አብርሃምን በብርቱ አስጨነቀው፤ 12 እግዚአብሔር ግን አብርሃምን “ስለ ልጁና ስለ አገልጋይቱ ስለ አጋር አትጨነቅ፤ ዘር የሚወጣልህ በይስሐቅ በኩል ስለሆነ ሣራ የምትልህን ሁሉ አድርግ፤ 13 የአገልጋይቱም ልጅ የአንተ ልጅ ስለሆነ ታላቅ ሕዝብ እስኪ ሆን ድረስ ዘሩን አበዛለሁ” አለው።

14 በማግሥቱ ጠዋት አብርሃም በማለዳ ተነሣ፤ ጥቂት ምግብ፥ ውሃም በአቁማዳ ሞልቶ ለአጋር ሰጣት፤ ልጁንም በጀርባዋ አሳዝሎ ከቤት አስወጣት፤ እርስዋም ከዚያ ወጥታ በቤርሳቤህ በረሓ ትንከራተት ጀመር። 15 በአቁማዳ የነበረው ውሃ ባለቀ ጊዜ ልጁን በቀሎዋቋጠ ሥር አስቀመጠችው፤ 16 እርስዋም “ልጁ ሲሞት ማየት አልፈልግም” በማለት መቶ ሜትር ያህል ርቃ ተቀመጠች፤ አዚያም ሆና ታለቅስ ጀመር።

17 እግዚአብሔርም ልጁ ምርር ብሎ ሲያለቅስ ሰማ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ከሰማይ አጋርን “አጋር ሆይ! የምትጨነቂበት ነገር ምንድን ነው? እግዚአብሔር የልጁን ለቅሶ ስምቶአልና አይዞሽ አትፍሪ፤ 18 ተነሺ! ሂጂና ልጁን አንሥተሽ አባብይው፤ የእርሱንም ዘር አበባለሁ፤ ታላቅም ሕዝብ አደርገዋለሁ” አላት። 19 በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ዐይኖች ዋን ከፈተላትና አንድ የውሃ ጕድጓድ አየች፤ ሄዳም በአቁማዳው ውሃ ሞላች፤ ለልጅዋም አጠጣችው። 20 ልጁ አያደገ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር፤ በፋራንም በረሓ ኖረ፤ ቀስት በመወርወርም የታወቀ አዳኝ ሆነ። 21 እናቱም ከእንዲት ግብጻዊት ጋር አጋባችው።

በአብርሃምና በአቢሜሌክ መካከል የተደረገ ስምምነት

22 በዚያን ጊዜ አቢሜሌክ ከሥራዊቱ አለቃ ከፊኮል ጋር ሄደና አብርሃምን “በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው፤ 23 እኔ ንም ሆነ ልጆቼን ወይም ዝርያዎቼን በማታለል እንዳትበድል እዚህ በእግዚአብሔር ስም ማል ልኝ፤ እኔ ለአንተ ታማኝነትን አሳይቻለሁ፤ አን ተም ለእኔና ለዚህች በእንግድነት ለምትኖርባት አገር ታማኝነትን እንደምታሳይ ማልልኝ” አለው።

24 አብርሃምም “እሺ እምላለሁ” አለው።

25 አብርሃም፥ የአቢሜሌክ አገልጋዮች ስለወ ስዱበት የውሃ ጕድጓድ ለአቢሜሌክ አቤቱታ አቀረበ። 26 አቢሜሌክም “ይህን ያደረገው ማን እንደሆነ አላውቅም፤ አንተም አልነገርኸኝም፤ ይህን ነገር ገና ዛሬ መስማቴ ነው” አለው፤ 27 ከዚህ በኋላ አብርሃም ብዙ በጎችና ከብቶች አምጥቶ ለአቢሜሌክ ሰጠው፤ በዚያን ቀን ሁለቱም የሰምምነት መሐላ አደረጉ። 28 በዚያን ጊዜ አብርሃም ሰባት የበግ ጥቦችን ከመንጋው ለየ፤ 29 አቢሜሌክም “እነዚህን ሰባት ጥቦች ለይተህ ያቆምሃቸው ለምንድን ነው?” አለው።

30 አብርሃምም “እነዚህን ሰባት ጥቦች ተቀበለኝ፤ እንርሱን ከተቀበልኸኝ ይህን ጕድጓድ የቈፈርሁ እኔ መሆኔን ታረጋግጣለህ” አለው። 31 ሁለቱ ተማምለው የተስማሙበት ሰፍራ በመሆኑ የዚያ ዐታ ስም ቤርሳቤህ[31*] ተባለ።

32 ይህን ስምምነት በቤርሳቤህ ካደረጉ በኋላ አቢሜሌክና የሠራዊቱ አለቃ ፊኮል ወደ ፍልስ ጥኤም ምድር ተመለሱ፤ 33 ከዚህ በኋላ አብር ሃም በቤርሳቤህ የታማሪስክ[32*] ዛፍ ተከለና የዘላ ለም አምላክ ለሆነው እግዚአብሔር ስገደ፤ 34 አብርሃም በፍልስጥኤም ምድር በእንግድነት ለረዥም ጊዜ ኖረ።

ምዕራፍ 22

ይስሐቅን እንዲሠዋለት እግዚአብሔር አብርሃምን አዘዘው

1 ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ እግዚአብሔር አብ ርሃምን ፈተነው፤ እግዚአብሔርም “አብር ሃም!” ብሎ ጠራው፤ አብርሃምም “እነሆ አለ ሁኝ” ብሎ መለሰ።

2 እግዚአብሔርም “የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ምድር

31* 21፥31 ቤርሳቤህ፦ በዕብራይስጥ “በኤር ሼባዕ” ሲሆን “የመሐላ የውሃ ጕድጓድ” ወይም “ሰባት ምንጭ” ማለት ነው።
32* 21፥33 ታማሪስክ፦ ቁመቱ እጠር ያለና ከተምር የተለየ ዛፍ ነው።

21፥10፦ ገላ. 4፥29-30። 21፥12፦ ሮም 9፥7፤ ዕብ. 11፥18። 21፥22፦ ዘፍ. 26፥26። 22፥1-13፦ ዕብ. 11፥17-19። 22፥2፦ 2ዜ.መ. 3፥1።

ሂድ ፤ እዚያ በማሳይህ እንድ ኮረብታ ላይ አር
ሱን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ” አለው ።
3በማግሥቱ ጠዋት አብርሃም በማለዳ ተነ
ሥቶ ለመሥዋዕቱ የሚሆን እንጨት ቈረጠና
በአህያው ላይ ጫነው ፤ ከአርሱ ጋር ልጁን ይስ
ሐቅንና ሁለት አገልጋዮችን ይዞ እግዚአብሔር
ወዳመለከተው ቦታ ለመሄድ ጕዞ ጀመረ ።
4በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለ
ከት ቦታውን በሩቅ አየ ። 5ከዚህ በኋላ አብር
ሃም አገልጋዮቹን “እናንተ ከአህያው ጋር
እዚህ ቆዩ ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን ለእግዚአ
ብሔር ከሰገድን በኋላ እንመለሳለን” አላቸው ።
6አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት እን
ሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው ፤ እርሱ ግን
ቢለዋውንና እሳቱን ያዘ ፤ ሁለቱም አብረው
ሲሄዱ ሳለ ፥ 7ይስሐቅ አብርሃምን “አባባ!”
አለው ፤ አብርሃምም “እነሆ አለሁ ልጄ!”
አለው ። ይስሐቅም “እነሆ እሳትና እንጨት
ይዘናል ፤ ታዲያ ለመሥዋዕት የሚሆነው በግ
የት አለ?” በማለት አብርሃምን ጠየቀው ።
8አብርሃምም “ልጄ ሆይ! ለመሥዋዕት
የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ሰራሱ ያዘጋ
ጃል” አለው ፤ ሁለቱም አብረው መንገዳቸውን
ቀጠሉ ።
9እግዚአብሔር ወዳመለከተው ቦታ በደረሱ
ጊዜ አብርሃም መሠዊያ ሠርቶ እንጨቱን በላዩ
ላይ ረበረበው ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ ከእን
ጨቱ በላይ በመሠዊያው ላይ አጋደመው ።
10ልጁን ለማረድ ቢላዋ እንሥቶ እጁን ዘረጋ ፤
11ነገር ግን የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ
“አብርሃም! አብርሃም!” ብሎ ጠራው ።
አብርሃምም “እነሆ አለሁኝ!” አለ ።
12መልአኩም “ልጁን አትንካ ፥ ምንም ዐይ
ነት ጕዳት አታድርሰበት ፤ እነሆ እግዚአብሔ
ርን የምትፈራ መሆንህን ተረድቼአለሁ ፤ ምክን
ያቱም እንድ ልጅህን አንኳ ለአኔ ከመሰጠት
አልተቈጠብህም” አለው ።
13አብርሃም ዙሪያውን በተመለከተ ጊዜ ቀን
ዶቹ በቊጥቋጦ ዛፍ የተያዙ አንድ በግ አየ ፤
ሄዶ ቦኑን አመጣና በልጁ ፋንታ መሥዋዕት
አድርጎ አቀረበው ። 14አብርሃም ያንን ቦታ
“እግዚአብሔር ያዘጋጃል”33* ብሎ ሰየመው ፤
ዛሬም ቢሆን ሰዎች “እግዚአብሔር በተራራው
ላይ ያዘጋጃል”34* ይላሉ ።
15የእግዚአብሔር መልአክ ሁለተኛ ጊዜ
አብርሃምን ጠራውና እንዲህ አለው ፤ 16“እግዚ
አብሔር ‘ብዙ ብረክት እንደምሰጥህ በራሴ ስም
እምላለሁ’ ይላል ፤ ይህን ስላደረግህና አንድ
ልጅህንም ለአኔ ለመስጠት ስላልተቈጠብህ ፥
17እኔም ብርህን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ
ባሕር ዳር እሸዋ አበዛዋለሁ ፤ ዝርያዎችህም
ጠላቶቻቸውን ድል ነሥተው ከተሞቻቸውን
ይይዛሉ ። 18ትእዛዜን ስለፈጸምህ የዓለም ሕዝ
ቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ።”
19ከዚህ በኋላ አብርሃም ወደ አገልጋዮቹ
ተመለሰና በእንድነት ሆነው ወደ ቤርሳቤህ
ሄዱ ፤ አብርሃምም በቤርሳቤህ ተቀመጠ ።

የናሖር ዝርያዎች

20ከዚህ ሁሉ በኋላ ሚልካ ለወንድሙ ለና
ኮር ልጆች እንደወለደችለት አብርሃም ሰማ ፤
እነርሱም ፥ 21የመጀመሪያው ዑፅ ፥ ወንድ
ሙም ቡዝ ፥ የአራም አባት ቀሙኤል ፤
22ኬሠድ ፥ ሐዞ ፥ ፊልዳሽ ፥ ይድላፍና በቱኤል
ናቸው ። 23በቱኤል ርብቃን ወለደ ፤ ሚልካ
እነዚህን ስምንት ልጆች ለአብርሃም ወንድም
ለናኮር ወለደችለት ። 24ረኡማ የተባለችው የና
ኮር ቊባት ደግሞ ጤባሕን ፥ ገሐምን ፥ ተሐሽ
ንና ፥ ማዕካን ወለደችለት ።

ምዕራፍ 23

ሣራ ሞተች ፥ አብርሃም የመቃብር ቦታ ገዛ

1ሣራ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት ከኖረች
በኋላ ፥ 2በከነዓን ምድር ባለችው “ቂርያት እር
ባዕ” ተብላ በምትጠራው በኬብሮን ከተማ
ሞተች ፤ አብርሃም በሣራ ሞት ምክንያት
እጅግ አዘነ ፤ አለቀሰም ።
3የሚስቱ አስከሬን ካለበት ስፍራ ተነሥቶ
ወደ ሒታውያን ሄደና ፥ 4“እኔ በመካከላችሁ
በእንግድነት የምኖር ስደተኛ ነኝ ፤ አባካችሁ
የመቃብር ቦታ ሽጡልኝ ፤ የሚስቴንም አስከ
ሬን ከዚያ ልቅበር” አላቸው ።
5ሒታውያንም አንዲህ ብለው መለሱለት ፥
6“ጌታው ፥ እስቲ ስማን ፤ እንተ እኮ በመካከላ
ችን እንደ ታላቅ መስፍን ነህ ፤ ከመቃብሮቻችን
ዋሩውን መርጠህ የሚስትህን አስከሬን እዚያ
ቅበር ፤ ሁላችንም ብንሆን የሚስትህን አስከሬን
የምትቀብርበት መቃብር ልንሰጥህ ፈቃደኞች
ነን” አሉት ።
7ከዚህ በኋላ አብርሃም በሒታውያን ፊት
እጅ ነሥቶ እንዲህ አለ ፥ 8“የሚሰቴን አስከሬን
እዚህ እንድቀብር ከፈቀዳችሁልኝ የጾሐር ልጅ
ዔፍሮን ፥ 9በእርሻው ድንበር ላይ ያለችውን
ማክጴላ የተባለችውን ድርብ ክፍል ያላትን ዋሻ
እንዲሸጥልኝ ጠይቁልኝ ፤ ይህ ሰፍራ የመቃብር

33* 22፥14 እግዚአብሔር ያዘጋጃል ፦ በዕብራይስጥ “ያህዌ ይርኤ” ሲሆን “እግዚአብሔር ያያል” ማለት ነው ።
34* 22፥14 “ያዘጋጃል” ወይም “ይታያል ”

22፥9 ፦ ያዕ. 2፥21 ። 22፥16-17 ፦ ዕብ. 6፥13-14 ። 22፥17 ፦ ዕብ. 11፥12 ። 22፥18 ፦ ሐ.ሥ. 3፥25 ።
23፥4 ፦ ዕብ. 11፥9 ፣13 ፣ ሐ.ሥ. 7፥16 ።

ቦታ እንዲሆንልኝ በእናንተ ፊት ሙሉ ዋጋ
ከፍዬ እንድገዛው አድርጉልኝ ።”
10ዔፍሮን ራሱ በከተማው በር አጠገብ ብነበ
ረው መስብሰቢያ ስፍራ ከሌሎች ሒታውያን
ጋር ተቀምጦ ነበር ፤ ስለዚህ እዚያ የነበሩት
ሰዎች ሁሉ እየሰሙ እንዲህ አለ ፦ 11 “ጌታው
ስማ ! እርሻውን በክልሉ ውስጥ ካለው ዋሻ ጋር
ሰጥቼሃለሁ ፤ ሙታንህን አንድትቀብርበት በመገ
ኖቼ በሒታውያን ፊት ሰጥቼሃለሁ ።”
12አብርሃም ግን በሒታውያን ፊት እንደገና
እጅ ነሣና ፤ 13 ሁሉም እየሰሙ ዔፍሮንን “እባ
ክህ አድምጠኝ ፤ ቦታውን ስሙሉ እገዛዋለሁ ፤
እኔም ዋጋውን ተቀበለኝና የሚሰቴን አስከሬን
እዚያ ወስጀ ልቅበር” አለው ።
14-15ዔፍሮንም “ጌታዬ የመሬቱ ዋጋ
አራት መቶ ብር ቢሆን ነው ፤ ታዲያ ይሄ በእ
ኔና በአንተ መካከል ምንድን ነው ? ይልቅስ
የሚሰትህን አስከሬን እዚያ ቅበር” አለው ።
16አብርሃምም በነገሩ ተስማምቶ ዔፍሮን በሕ
ዝቡ ፊት በተናገረው መሠረት በነጋዴዎች
ሚዛን ልክ አራት መቶ ብር መዝኖ ሰጠው ።
17በዚህ ዐይነት ከመምሬ በስተምሥራቅ
ማከጲላ የተባለው የዔፍሮን ቦታ የአብርሃም
ርስት ሆነ ፤ ይህም ቦታ እርሻውን ፣ በውስጡ
ያለውን ዋሻና በእርሻው ክልል ውስጥ ያለውን
ዛፍ ሁሉ ያጠቃልላል ። 18በዚያም ተገኝተው
የነበሩት ሒታውያን ሁሉ የአብርሃም ርስት
መሆኑን አረጋገጡ ።
19ከዚህ በኋላ አብርሃም በከነዓን ምድር ባለ
ችው በዚህችው ዋሻ የሚስቱን የሣራን አስከ
ሬን ቀበረ ፤ 20ስለዚህ የሒታውያን የነበረው
እርሻ በውስጡ ካለው ዋሻ ጋር የአብርሃም የመ
ቃብር ርስት ሆነ ።

ምዕራፍ 24

የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ

1በዚህ ጊዜ አብርሃም በጣም አርጅቶ
ነበር ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን በሁሉም
ነገር ባረከው ። 2አብርሃም የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ
በመሆን ለረዥም ዘመን የኖረውን አገልጋዩን
እንዲህ አለው ፦ “እጅህን በጕልበቴ ሳይ35*
አድርገህ ማልልኝ ፤ 3ይሄውም እኔ በመካከላ
ቸው ከምኖረው ከከነዓናውያን ሴቶች ልጆች
መካከል ለልጄ ሚስት እንዳትመርጥ የሰማይና
የምድር አምላክ በሆነው በእግዚአብሔር ስም
ማልልኝ ፤ 4ነገር ግን ወደ ትውልድ አገሬ
ሂድ ፤ እዚያም ካሉት ወገኖቼ መካከል ለልጄ
ለይስሐቅ ሚስት ምረጥለት ።”
5አገልጋዩም “ምናልባት የምመርጥለት
እጮኛ ከእኔ ጋር ወደዚህ አገር ለመምጣት
እምቢ ብትልስ ? ልጅህን ቀድሞ አንተ ወደነበ
ርክበት አገር እንዲመለስ ሳድርገውን ?” ብሎ
ጠየቀ ።
6አብርሃም ግን እንዲህ አለው ፦ “በምንም
ዐይነት ምክንያት ቢሆን ልጄን ወደዚያ አገር
መልሰህ እንዳትወሰድ ተጠንቀቅ ፤ 7የሰማይ
አምላክ እግዚአብሔር ፦ ከአባቴ ቤትና ከትው
ልድ አገሬ አውጥቶ አምጥቶኛል ፤ ይህንንም
ምድር ለዝርያዎቼ እንደሚሰጥ በመሐላ ቃል
ገብቶልኛል ፤ ከዚያ ስልጂ ሚስት ማግኘት እን
ድትችል እግዚአብሔር መልአኩን በፊትህ ይል
ካል ። 8ልጅትዋ ከእንተ ጋር ለመምጣት ፈቃ
ደኛ ባትሆን ከዚህ መሐላ ነፃ ትሆናለህ ፤
ልጄን ግን በምንም ዐይነት ሁኔታ ወደዚያ አት
መልሰው ።” 9ከዚህ በኋላ አገልጋዩ እጁን በጌ
ታው በአብርሃም ጕልበት ላይ አድርጎ አብር
ሃም ያዘዘውን ሁሉ እንደሚፈጽም በመሐላ
ቃል ገባ ።
10የአብርሃም ንብረት ኀላፊ የነበረው
መጋቢ ከጌታው ቤት ምርጥ የሆኑ የስመታ ዕቃ
ዎችን በዐሥር ግመሎች ጭኖ በስሜን መስጴጦ
ምያ ናኮር ወደሚኖርበት ከተማ ሄደ ። 11እዚያ
በደረስ ጊዜ ከከተማው ውጭ ባለ የውሃ
ጕድጓድ አጠገብ ግመሎቹ ተንበርከክው እንዲ
ያርፉ አደረገ ፤ ሰዓቱም ሊመሽ ተቃርቦ ፥
ሴቶች ውሃ ለመቅዳት የሚወጡበት ጊዜ ነበር ፤
12አገልጋዩም አንዲህ ብሎ ጸለየ ፦ “የጌታዬ
የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ! ዛሬ
የእኔን አሳብ በመፈጸም ለጌታዬ ለአብርሃም ዘላ
ለማዊ ፍቅርህን ግለጥ ። 13እነሆ ፥ እኔ በዚህ
የውሃ ጕድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ ፤ የከተማይ
ቱም ልጃገረዶች ውሃ ሊቀዱ ወደዚህ ይመ
ጣሉ ፤ 14ከእነርሱም አንድዋን ልጃገረድ ‘እንስ
ራሽን ዘንበል አድርገሽ ውሃ አጠጪኝ’ አሳታ
ለው ፤ ‘አንተም ጠጣ ፤ ግመሎችህም እንዲጠጡ
ውሃ ቀድቼ እመጣለሁ’ ካለችኝ ለአገልጋይህ
ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆን የመረጥሃት እር
ስዋ ትሁን ፤ በዚህም ሁኔታ ለጌታዬ ለአብርሃም
ዘላለማዊ ፍቅርህን እንዳሳየኸው ዐውቃለሁ ።”
15ገና ጸሎቱን ሳያጨርስ ርብቃ እንስራ
ተሸክማ መጣች ፤ የዚህችም ልጅ አባት ባቱ
ኤል ይባል ነበር ፤ እርሱም የአብርሃም ወንድም
ናኮር ከሚስቱ ከሚልካ የወለደው ነው ።
16ርብቃ ገና ወንድ ያልደረሰባት በጣም ቈንጆ
ልጃገረድ ነበረች ፤ እርሰዋ ወደ ውሃው ጕድጓድ
ወርዳ በእንስራዋ ውሃ ከቀዳች በኋላ ተመለ
ሰች ። 17አገልጋዩም ወደ እርሰዋ ሮጦ ሄደና
“እባክሽ ከእንስራሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ”
አላት ።
18እርሰዋም “እሺ ጌታዬ ጠጣ” አለችና
እንስራዋን ከትከሻዋ አውርዳ ዘንበል አድርጋ

35* 24፡2 “በጕልበቴ ሳይ” ወይም “ከሥሩ በታች” የሚለው በዕብራይስጥ ባሕል የሚያሳየው የማይለወጥ መሐላ መሆኑን ነው ።

ያዘችለት ። 19 ጠጥቶም ከረካ በኋላ "ለግመሎች ሀም ውሃ እቀዳላቸዋለሁ ፤ እስኪበቃቸውም ድረስ ይጠጡ" አለችው ። 20 ወዲያውኑ በእንስራዋ የያዘችውን ውሃ ግመሎቹ በሚጠጡበት ገንዳ ላይ ገልብጣ ግመሎቹ ሁሉ ጠጥተው እስ ከሚረኩ ድረስ እየተጣደፈች ከጉድጓድ ውሃ መቅዳት ቀጠለች ። 21 ሰውየውም እግዚአብሔር የሄደበትን ተልእኮ አቃንቶለት እንደሆን ለማረ ጋገጥ የምታደርገውን ሁሉ ዝም ብሎ ይመለ ከት ነበር ።

22 ግመሎቹ ጠጥተው ካበቁ በኋላ ሰውየው አምስት ግራም ያህል የሚመዝን የወርቅ ጕትቻ አውጥቶ በጆሮዋ ላይ አደረገላት ፤ መቶ ሀሥር ግራም ያህል የሚመዝን ሁለት የወርቅ አምባሮችንም አውጥቶ በእጆችዋ ላይ አደረገላ ትና ፥ 23 "የማን ልጅ ነሽ? እስቲ እባክሽ ንገ ሪኝ ፤ ለእኔና አብረውኝ ላሉት ሰዎች ማደሪያ የሚሆን ስፍራ በአባትሽ ቤት ይገኛልን?" ብሎ ጠየቃት ።

24 እርስዋም "የባቱኤል ልጅ ነኝ ፤ የባቱ ኤል አባት ናኮር ፥ እናቱም ሚልካ ይባላሉ ፤ 25 በቤታችን ብዙ ገለባና ድርቆሽ አለ ፤ ለእናን ተም ማደሪያ ቦታ ይገኛል" አለችው ።

26 ሰውየውም በመንበርከክ ለእግዚአብሔር ሰግዶ ፥ 27 "ለጌታዬ የገባውን ቃል ኪዳንና ዘላ ለማዊ ፍቅሩን የጠበቀ የጌታዬ የአብርሃም አም ላክ እግዚአብሔር ይመስገን ፤ በቀጥታ መርቶ ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት ያመጣኝ እርሱ ነው" አለ ።

28 ልጅትዋ ወደ ቤት ሮጣ ሄደችና የሆነ ውን ሁሉ ለእናትዋና ከእርስዋ ጋር ላሉት ሁሉ ነገረቻቸው ። 29 ርብቃ ላባ የተባለ ወንድም ነበ ራት ፤ እርሱ የአብርሃም አገልጋይ ወዳለበት ውሃ ጕድጓድ እየሮጠ ሄደ ። 30 ላባ ወደ ሰው የው የሄደው እኅቱ በጆሮዋ ላይ ያደረገችውን ጕትቻና በእጆችዋ ላይ ያደረገቻቸውን እንባ ሮች ስላየና ርብቃ ሰውየው ያላትን ስትናገር ስለሰማም ነው ። እርሱንም በውሃው ጕድጓድ አጠገብ ከግመሎቹ ጋር ቆሞ አገኘው ። 31 ስለ ዚህ ላባ "እንተ እግዚአብሔር የባረከህ ሰው! ና ወደ ቤት እንሂድ ፤ በውጭ የቆምኸው ሰምን ድን ነው? በቤታችን ለእንተ ማረፊያ ስፍራ አለ ፤ ለግመሎችህም ማደሪያ የተዘጋጀ ቦታ አለ" አሰው ።

32 ከዚህ በኋላ ሰውየው ወደ ቤት ሄደ ፤ ላባም በግመሎቹ ላይ የነበረውን ጭነት አራ ግፎ ገለባና ድርቆሽ አቀረበላቸው ፤ ቀጥሎም የአብርሃም አገልጋይና አብረውት የነበሩት ሰዎች እግራቸውን የሚታጠቡበት ውሃ አመጣ ላቸው ። 33 ገበታ በቀረበ ጊዜ ሰውየው "የተላክ ሁበትን ጕዳይ ከመናገሬ በፊት እህል አልቀም ስም" አለ ። ላባም "ይሁን ተናገር" አለው ።

34 እርሱም "እኔ የአብርሃም አገልጋይ ነኝ ፤ 35 እግዚአብሔር ጌታዬን እጅግ ባርኮታል ፤ ባሰ ጸጋም አድርጎታል ፤ ብዙ የበግ ፥ የፍየልና የከ ብት መንጋ ፥ ብርና ወርቅ ፥ ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮች ግመሎችና አህዮች ሰጥቶታል ። 36 የጌታዬ ሚስት ሣራ በእርጅናዋ ዘመን ወንድ ልጅ ወልዳለታለች ፤ ጌታዬም ያለውን ሀብት ሁሉ ለዚሁ ልጅ አውርሶታል ። 37-38 ጌታዬ አብርሃም 'እኔ በመካከላቸው ከምኖረው ከከነዓ ናውያን ሴቶች ልጆች መካከል ለልጁ ሚስት እንዳታጭለት ፤ ነገር ግን ወደ አባቴ ቤተሰብና ወደ ዘመዶቼ ሄደህ ለልጁ ሚስት እጭለት' ሲል በመሐላ ቃል ኪዳን አስገብቶኛል ። 39 እኔም ጌታዬን 'ልጅቷ ከእኔ ጋር ለመምጣት ፈቃደኛ ባትሆንስ ምን ላድርግ?' ብዬ ጠየቅ ሁት ። 40 እርሱም እንዲህ አለኝ 'ዘወትር የማገ ለግለው እግዚአብሔር መልአኩን ከአንተ ጋር ይልካል ፤ ጕዞህም የተቃና እንዲሆን ያደር ጋል ፤ በዚህ ሁኔታ አንተም ከአባቴ ቤተሰብና ከዘመዶቼ መካከል ለልጁ ሚስት ልታጭለት ትችላለህ ፤ 41 ከመሐላህ ነፃ የምትሆነው ወደ ዘመዶቼ ሄደህ እንርሱ ልጅትዋን እንሰጥም ብለው የከለከሉህ እንደሆነ ብቻ ነው ።'

42 "ከዚህም በኋላ ዛሬ ወደ ውሃው ጕድጓድ ስመጣ እንዲህ ብዬ ጸለይሁ 'የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ፤ እባክህ የመጣሁ በት ጕዳይ እንዲቃና አድርግልኝ ፥ 43 እነሆ በዚህ የውሃ ጕድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ ፤ እን ዲት ልጃገረድ ውሃ ልትቀዳ ስትመጣ ፥ 'እባክሽ ከእንስራሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ' ብዬ እጠይቃ ታለሁ ፤ 44 እርስዋም 'እሺ ጠጣ ፤ ለግመሎች ህም እቀዳላቸዋለሁ' የምትለኝ ብትሆን ፥ ለጌ ታዬ ልጅ ሚስት እንድትሆን አንተ የመረጥሃት እርስዋ ትሁን ። 45 የጎሊና ጸሎቴን ገና ሳልጨ ርስ ርብቃ እንስራ ተሸክማ ብቅ አለች ፤ ወደ ጕድጓዱም ሄዳ ውሃ ቀዳች ፤ እኔም 'እባክሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ' አልኋት ። 46 እርስዋም እንስራዋን በፍጥነት ከጀርባዋ አወረደችና ዘን በል አድርጋ 'እሺ ጠጣ ፤ ግመሎችህንም አጠጣ ልሃለሁ' አለችኝ ፤ ስለዚህ እኔም ጠጣሁ ፤ ግመ ሎቹንም አጠጣችልኝ ። 47 እኔም 'የማን ልጅ ነሽ?' ብዬ ጠየቅኋት ። እርስዋም 'የባቱኤል ልጅ ነኝ ፤ የባቱኤል አባት ናኮር እናቱም ሚልካ ይባላሉ' አለችኝ ። ከዚህ በኋላ ጕትቻ በጆሮዋ ላይ ፥ አንባሮቹንም በእጆዎችዋ ላይ አደረግሁላት ፤ 48 ከዚህ በኋላ በጕልበቴ ተንበር ከኬ ለእግዚአብሔር ሰገድሁ ፤ የጌታዬን የአብር ሃምን አምላክ እግዚአብሔርን አመሰገንሁ ፥ ምክ ንያቱም ለጌታዬ ልጅ ሚስት የምትሆነዋን ሴት ወዳገኘሁበት ወደ ጌታዬ ወንድም ቤት በቀና መንገድ የመራኝ እርሱ ነው ። 49 እንግዲህ የጌታ ዬን ሀደራ በእውነት ተቀብላችሁ እርሱን ደስ

ለማስኘት የምትፈቅዱ እንደሆን ንገሩኝ ፣ የማት
ፈቅዱም እንደሆን ቍርጡን ንገሩኝ ፣ እኔም እማ
ዚእብሔር ወደሚመራኝ እሄዳለሁ ።''
50 ላባና ባቱኤልም ''ይህ ነገር ከእግዚአብ
ሔር የመጣ ስለሆነ ፥ መከልከል አንችልም ፤
51 ርብቃ ይህችውልህ ፤ እነሆ ይዘሃት ሂድ ፤
እግዚአብሔር ራሱ እንደተናገረው ለጌታህ ልጅ
ሚስት ትሁን'' አሉት ። 52 የአብርሃም አገል
ጋይ ይህን በሰማ ጊዜ በጕልበቱ ተንበርክኮ ለእ
ግዚአብሔር ሰገደ ፥ 53 ከወርቅና ከብር የተሠሩ
ጌጣጌጦችን ፥ እንዲሁም ልብስ አውጥቶ ለር
ብቃ ሰጣት ፤ ለወንድምዋና ለእናትዋም በጣም
ውድ የሆኑ ስጦታዎችን አውጥቶ ሰጣቸው ።
54 ከዚህ በኋላ የአብርሃም አገልጋይና አብረ
ውት የነበሩ ሰዎች በልተው ጠጥተው እዚያው
አደሩ ፤ ጠዋት በተነሡ ጊዜ የአብርሃም አገል
ጋይ ''እንግዲህ ወደ ጌታዬ እንድመለስ ፍቀዱ
ልኝ'' አለ ።
55 ነገር ግን የርብቃ ወንድምና እናትዋ
''ልጅትዋ ዐሥር ቀን ያህል ከእኛ ጋር ትቀይ ፤
ከዚያ በኋላ ከአንተ ጋር ልትሄድ ትችላለች''
አሉት ።
56 እርሱ ግን ''እባካችሁ አታቆዩኝ ፤ እግዚ
አብሔር የመጣሁበትን ጉዳይ ስላቃናልኝ ቶሎ
ብዬ ወደ ጌታዬ ልመለስ'' አላቸው ።
57 እነርሱም ''እስቲ ልጅቷን እንጥራና እር
ስዋ የምትለውን እንስማ'' አሉ ። 58 ስለዚህ ርብ
ቃን ጠሩና ''ከዚህ ሰው ጋር መሄድ ትፈልጊያ
ለሽን ?'' ብለው ጠየቅዋት ።
እርስዋም ''አዎ አሄዳለሁ'' አለች ።
59 ስለዚህ ርብቃ ሞግዚትዋን አስከትላ ፥ ከአ
ብርሃም አገልጋይና ከእርሱ ሰዎች ጋር አንድት
ሄደ ፈቀዱላት ። 60 ''አንቺ እኅታችን የብዙ ሺ
ሕዝብ እናት ሁኚ ፤ ዝርያዎችሽም የጠላቶች
ሽን ከተሞች ይውረሱ'' ብለው ርብቃን መረቁ
አት ። 61 ከዚህ በኋላ ርብቃ ከተከታዮችዋ ጋር
ለመሄድ ተነሣች ፤ በግመሎቹ ላይ ተቀምጠው
ከአብርሃም አገልጋይ ጋር ለመሄድ ተዘጋጁ ።
በዚህ ዐይነት የአብርሃም አገልጋይ ርብቃን ይዞ
ሄደ ።
62 በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ''ብኤር ላሐይ ሮኢ
ወይም የሚያየኝ ሕያው አምላክ'' የተባለው
ኵሬ ወዳለበት ሸረሓ መጥቶ በኔጌብ ተቀምጦ
ነበር ። 63 ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ማታ ጊዜ
እያሰላሰለ በመስክ ውስጥ ሲዘዋወር ሳለ ግመ
ሎች ሲመጡ በሩቅ አየ ። 64 ርብቃ ይስሐቅን
ባያት ጊዜ ከግመሏ ወረደችና ፥ 65 ''ያ በመስክ
ውስጥ ወደ እኛ የሚመጣው ሰው ማን ነው ?''
ስትል የአብርሃምን አገልጋይ ጠየቀችው ። አገል
ጋዩም ''እርሱ ጌታዬ ነው !'' አላት ። ስለዚህ
በፍጥነት በሻሽ ፊትዋን ሸፈነች ።

66 አገልጋዩም ያደረገውን ነገር ሁሉ ለይስ
ሐቅ ነገረው ። 67 ከዚህ በኋላ ይስሐቅ እናቱ
ሣራ ትኖርበት ወደነበረው ድንኳን ርብቃን ይዞ
አት ገባ ፤ ሚስትም ሆነችው ፤ ይስሐቅ ርብቃን
ወደዳት ፤ በእናቱ ሞት ምክንያት ከደረሰበትም
ሐዘን በዚህ ሁኔታ ተጽናና ።

ምዕራፍ 25

ሌሎች የአብርሃም ዝርያዎች
(1 ዜ.መ. 1፡32-33)

1 አብርሃም ቀጡራ የምትባል ሌላ ሚስት
አገባ ፤ 2 እርስዋም ዚምራንን ፥ ዮቅሻንን ፥ መዳ
ንን ፥ ምድያምን ፥ ዩሽባቅንና ሹሐን ወለደች
ለት ። 3 ዮቅሻንም ሳባንና ደዳንን ወለደ ፤ የደዳ
ንም ዝርያዎች አሹራውያን ፥ ሌጡሻውያንና
ሌኡማውያን ናቸው ። 4 የምድያምም ልጆች
ዔፋ ፥ ዔፌር ፥ ሐኖክ ፥ አቢዳዕና ኤልዳዓ
ናቸው ፤ እነዚህ ሁሉ የቀጡራ ዝርያዎች
ናቸው ።
5 አብርሃም ያለውን ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ
አወረሰው ፤ 6 ከሌሎች ሴቶች ለተወለዱትም
ልጆች ገና በሕይወት ሳለ ስጦታ ሰጣቸው ፤
ከዚህ በኋላ እነዚህ ሌሎች ልጆች ከይስሐቅ
ርቀው ወደ ምሥራቅ አገር እንዲሄዱ አደረጋ
ቸው ።

የአብርሃም መሞት

7 የአብርሃም ዕድሜ ለአጠቃላይ መቶ ሰባ
አምስት ዓመት ነበር ፤ 8 በዚህም ዐይነት አብር
ሃም በቂ ዕድሜ አግኝቶ ካረጀ በኋላ ሞተ ፤
9 ልጆቹ ይስሐቅና እስማኤል ማክፌላ በተባለ
ዋሻ ቀበሩት ፤ ይህም ዋሻ ከመምሬ በስተምሥ
ራቅ በሒታዊው በጾሐር ልጅ በዔፍሮን እርሻ
ውስጥ የሚገኘው ነው ፤ 10 እርሱም አብርሃም
ከሒታውያን ላይ የገዛው የመቃብር ቦታ ነው ፤
በዚህ ዐይነት አብርሃም ሚስቱ ሣራ በተቀበረች
በት ዋሻ ተቀበረ ። 11 አብርሃም ከሞተ በኋላ
ልጁን ይስሐቅን እግዚአብሔር ባረከው ፤ ይስሐ
ቅም ''ብኤርላሐይ ሮኢ ወይም የሚያየኝ
ሕያው አምላክ'' ተብሎ በሚጠራው ኵሬ አጠ
ገብ ይኖር ነበር ።

የእስማኤል ዝርያዎች
(1 ዜ.መ. 1፡28-31)

12 የሣራ አገልጋይ ግብጻዊትዋ አጋር ለአብር
ሃም የወለደችለት እስማኤል ፥ 13 ከዚህ በታች
በዕድሜአቸው ቅደም ተከተል ቍራ የተዘረዘሩ
ትን ልጆች ወለደ ፤ እነርሱም ፦ ነባዮት ፥
ቄዳር ፥ አደብኤል ፥ ሚብሣም ፥ 14 ሚሽማዕ ፥
ዱማ ፥ ማሣ ፥ 15 ሐዳድ ፥ ቴማ ፥ ይጡር ፥ ናፌ
ሽና ቄድማ ናቸው ። 16 እነዚህ የእስማኤል

25፡10 ፦ ዘፍ. 23፡3-16 ።

ልጆች ለወሥራ ሁለት ነገዶች ቅድመ አያቶች ነበሩ ፤ ስማቸውም በኖሩባቸው ከተሞችና ሰፍራዎች ሲጠራ ይኖራል ። 17 አስማኤል መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ሲሆነው ሞተ ፤ 18 የአስማኤል ዝርያዎች ከግብጽ በስተምሥራቅ ወደ አሦር በምትወስደው መንገድ በሐዊላና በሹር መካከል ይኖሩ ነበር ፤ የኖሩትም ከሌሎቹ የአብርሃም ዝርያዎች ጋር በጥላቻ ተራርቀው ነበር ።

የዔሳውና የያዕቆብ መወለድ

19 የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ታሪክ ይህ ነው ፤ አብርሃም ይስሐቅን ወለደ ። 20 ይስሐቅ የባቱኤልን ልጅ ርብቃን ሲያገባ አርባ ዓመት ሆኖት ነበር ፤ የርብቃ አባት ባቱኤልና ወንድ ምዋ ላባ በመስጴጦምያ የሚኖሩ ሶርያውያን ነበሩ ፤ 21 ርብቃ መኻን ስለነበረች ይስሐቅ ሰለ እርስዋ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰለ ሰማ ርብቃ ፀነሰች ፤ 22 የተፀነሱትም መንትያዎች ስለነበሩ እርስ በርሳቸው በማሕፀንዋ ውሰጥ ይጋፉ ነበር ፤ እርስዋም “ይህን ዐይነት ነገር ለምን ደረሰብኝ?” በማለት ወደ እግዚአብሔር ለመጸለይ ተነሣሣች ። 23 እግዚአብሔርም ፦

“በማሕፀንሽ ያሉት ሁለት ሕዝቦች
ናቸው ፤
እርስበርሳቸው የማይስማሙ ሁለት
ወገኖች ትወልጃለሽ ፤
አንዱም ከሌላው የበረታ ይሆናል ፤
ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል”
አሉት ።

24 የመውለጃዋም ሰዓት በደረሰ ጊዜ ሁለት ወንዶች ልጆች መለደች ። 25 የመጀመሪያው ልጅ መልኩ ቀይ ፥ ሰውነቱ ጠጕራም ነበር ፤ ስለዚህ ዔሳው[36*] ተባለ ። 26 ሁለተኛው ልጅ ሲወለድ የዔሳውን ተረከዝ ይዞ በመውጣቱ ያዕቆብ[37*] ተባለ ፤ ልጆቹ ቡተወለዱ ጊዜ ይስሐቅ ሰልሳ ዓመት ሆኖት ነበር ።

ዔሳው ብኵርናውን ሸጠ

27 ሁለቱም ልጆች አደጉ ፤ ዔሳው በዱር መዋል የሚወድ ብልኅ አዳኝ ሆነ ፥ ያዕቆብ ግን በቤት መዋል የሚወድ ጭምት ሰው ነበር ። 28 ይስሐቅ ዔሳውን ይወድ ነበር ፤ ምክንያቱም ዔሳው እያደነ ሥጋ ያበላው ነበር ። ርብቃ ግን ያዕቆብን ትወድ ነበር ።

29 ከሰለታት አንድ ቀን ያዕቆብ ቀይ የምስር ወጥ በመሥራት ላይ እንዳለ ዔሳው ከአደን መጣ ፤ በጣም እርቦት ነበር ፤ 30 ስለዚህም ያዕቆብን “ከዚህ ከቀይ ወጥ ስጠኝ” አለው ። ኤዶም[38*] የተባለውም በዚህ ምክንያት ነበር ።

31 ያዕቆብም “መጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥ ልኝ” አለው ።

32 ዔሳውም “እኔ በረሀብ መሞቴ ነው ፤ ታዲያ ብኵርና ምን ያደርግልኛል?” አለው ።

33 ያዕቆብም “እንግዲያውስ ብኵርናህን እን ደምትሸጥልኝ መጀመሪያ ማልልኝ” አለው ። ስለዚህ ዔሳው ምሎ ብኵርናውን ለያዕቆብ ሸጠ ።

34 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ የምስሩን ወጥ በእን ጀራ አድርጎ ሰጠው ፤ ዔሳውም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነሥቶ ሄደ ፤ በዚህ ዐይነት ዔሳው ብኵ ርናውን በመናቅ አቃለሳት ።

ምዕራፍ 26

ይስሐቅ በገራር ኖረ

1 በአብርሃም ዘመን ከደረሰው ረሀብ ሌላ ዳግ መኛ ረሀብ በምድር ላይ መጣ ፤ በዚህ ምክንያት ይስሐቅ የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ አቢሜሌክ ወዳለበት ወደ ገራር ሄደ ፤ 2 በዚያም እግዚአብ ሔር ለይስሐቅ ተገለጠለትና እንዲህ አለው ፥ “ወደ ግብጽ አገር አትሂድ ፤ እንድትኖርበት በምነግርህ በዚህ ምድር ተቀመጥ ፤ 3 እዚህ ኑር ፤ አንም ከአንተ ጋር አሆናለሁ ፤ አባርክሃለ ሁም ፤ ይህን ምድር ለአንተና ለዝርያዎችህ እሰ ጣለሁ ፤ በዚህ ዐይነት ለአባትህ ለአብርሃም የገባ ሁትን ቃል ኪዳን እፈጽማለሁ ፤ 4 ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ ፤ ይህንንም ሁሉ ምድር አወርሳቸዋለሁ ፤ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ። 5 እንተን የምባርክበትም ምክ ንያት አባትህ አብርሃም ለእኔ ታዛዥ በመሆን የሰ ጠሁትን ሕግና ሥርዓት ሁሉ ስለ ጠበቀ ነው ።”

6 ስለዚህ ይስሐቅ መኖሪያውን በገራር አደ ረገ ፤ 7 የዚያ አገር ሰዎችም ስለ ርብቃ “ምንህ ናት” ብለው በጠየቁት ጊዜ “እኅቴ ናት” አላ ቸው ፤ ይህንንም ያለበት ምክንያት ርብቃ በጣም ቈንጆ ስለነበረች የዚያ አገር ሰዎች በእ ርስዋ ሰበብ እንዳይገድሉት በመፍራት ነው ። 8 ይስሐቅ እዚያ አገር ብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ የፍ ልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ በመስኮት ወደ ውጪ ሲመለከት ይስሐቅና ርብቃ እንደባልና ሚስት በመዳራት ሲጫወቱ አየ ፤ 9 ስለዚህ አቢ ሜሌክ ይስሐቅን አስጠርቶ “ለካስ ርብቃ ሚስ ትህ ናት ፤ ታዲያ ‘እኅቴ ናት’ ያልከው ለምን ድን ነው?” ሲል ጠየቀው ።

እርሱም “ሚስቴ ነች ያልኩ እንደሆን ሰዎች ይገድሉኛል ብዬ ስለፈራሁ ነው” ብሎ መለሰ ።

36* 25፡25 ዔሳው ፡- በዕብራይስጥ “ጠጕራም” ማለት ነው ። 37* 25፡26 ያዕቆብ ፡- በዕብራይስጥ “ተረከዝ የሚይዝ አሰናካይ” ማለት ነው ። 38* 25፡30 ኤዶም ፡- “ቀይ” ማለት ሲሆን ዔሳው የተለየመበት ስም ነው ።

25፡23 ፡- ሮም 9፡12 ። 25፡33 ፡- ዕብ. 12፡16 ። 26፡3-4 ፡- ዘፍ. 22፡16-18 ። 26፡7 ፡- ዘፍ. 12፡13 ፤ 20፡23 ።

10 አቢሜሌክም “ይህ በእኛ ላይ ያደረግ
ኸው ነገር ምንድን ነው? ከእኛ ስዎች አንዱ
በቀላሉ ሚስትህን ስመይፈር በቻለ ነበር ፣ አኛ
ንም ጋጢአተኞች ልታደርገን ነበር ፡፡” 11 ቀጥ
ሎም አቢሜሌክ “ይህን ሰው ወይም ሚስቱን
የሚነካ ሰው በሞት ይቀጣል” የሚል ማስጠን
ቀቂያ ለሕዝቡ ሰጠ ።
12 ይስሐቅ በዚያች ምድር ዘርን ዘራ ፣ አግዚ
አብሔር ስለባረከውም በዚያኑ ዓመት መቶ
እጥፍ አመረተ ፣ 13 ሀብት በሀብት ላይ እየተጨ
መረስት ስለሄደ እጅግ ባለጸጋ ሆነ ። 14 ብዙ የበ
ግና የከብት መንጋ ፣ አንዲሁም ብዙ አገልጋ
ዮች ስለ ነበሩት ፍልስዮኤማውያን ቀኑበት ።
15 ስለዚህ የይስሐቅ አባት አብርሃም በሕይወት
በነበረበት ዘመን የአርሱ አገልጋዮች ቁፍረዋ
ቸው የነበሩትን የውሃ ጕድጓዶች ሁሉ ሀፈር
ሞልተው ደፈኑአቸው ።
16 በዚያን ጊዜ አቢሜሌክ ይስሐቅን “ኅይ
ልህ ከእኛ ይልቅ እየበረታ ስለሄደ ፣ አገራችንን
ለቀህ ውጣ” አለው ። 17 በዚህ ምክንያት ይስ
ሐቅ ያንን ቦታ ለቆ በገራር ሸለቆ ውስጥ
ሰፈረ ፣ አቢያም ተቀመጠ ። 18 አብርሃም በሕይ
ወት ሳለ አስቄፍሮአቸው የነበሩትንና አብርሃም
ከሞተ በኋላ ግን ፍልስዮኤማውያን የደፈኑአቸ
ውን የውሃ ጕድጓዶች ይስሐቅ እንደገና እንዲቄ
ፈሩ አደረገ ፣ አባቱ ባወጣሳቸው ስሞችም ጠራ
ቸው ።
19 የይስሐቅ አገልጋዮች በሸለቆው ውስጥ
የውሃ ጕድጓድ ቁፈሩና ጥሩ የምንጭ ውሃ
አገኙ ፤ 20 የገራር አረኞች ግን “ይህ ውሃ የአኛ
ነው” በማለት ከይስሐቅ እረኞች ጋር ተጣሉ ።
በዚህ ምክንያት ይስሐቅ ጕድጓዱን
“ዔሚቅ”39* ብሎ ሰየመው ።
21 የይስሐቅ አገልጋዮች ሌላ የውሃ ጕድጓድ
ቁፈሩ ፣ በዚህኛውም ጕድጓድ ምክንያት ሌላ
ጠብ ተነሣ ፤ ስለዚህ ይስሐቅ ይህን ጕድጓድ
“ስጥና”40* ብሎ ሰየመው ። 22 ከዚያም አልፍ
ብሎ ሌላ የውሃ ጕድጓድ ቁፈረ ፤ በዚህኛው
የውሃ ጕድጓድ ምክንያት ምንም ጠብ ስላልተ
ነሣ “እነሆ አሁን አግዚአብሔር ሰፊ ቦታ
ሰጠን ፣ በምድር ላይም እንበዛለን ሲል ያንን
ቦታ ‘ረሐቦት’41* ብሎ ሰየመው ።
23 ከዚህ በኋላ ይስሐቅ ወደ ቤርሳቤህ ወጣ ፤
24 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር ተገለጠለትና
“እኔ የአባትህ የአብርሃም አምላክ ነኝ ፤ እኔ
ከእንተ ጋር ስለሆንኩ አትፍራ ! ለአገልጋዬ ለአ
ብርሃም በገባሁት ቃል ኪዳን መሠረት አባርክህ
ለሁ ፣ ዘርህንም አበዛዋለሁ” አለው ። 25 ይስሐቅ
በዚያ መሠዊያ ሠራና ለእግዚአብሔር ሰገደ ፤
መኖሪያውንም አዚያ አደረገ ፤ አገልጋዮቹም
ሌላ ጕድጓድ ቆፈሩ ።

በይስሐቅና በአቢሜሌክ መካከል የተደረገ ስምምነት

26 አቢሜሌክ ከአማካሪው ከአሔዘትና ከሥራ
ዊቱ አዛዥ ከፊኮል ጋር ይስሐቅን ስመጐብኘት
ከገራር መጣ ፤ 27 ስለዚህ ይስሐቅ “ከዚህ በፊት
ጠልታችሁኝ ከአገራችሁ እንድወጣ አድርጋች
ሁኛል ፣ ታዲያ አሁን ልትጐበኙኝ የመጣች
ሁት ለምንድን ነው ?” አላቸው ።
28 እነርሱም አንዲህ ሲሉ መለሱለት ፥ “እግ
ዚአብሔር ከአንተ ጋር መሆኑን በግልጥ ዐውቀ
ናል ፤ ስለዚህ በእኛና በአንተ መካከል በሰላም
ለመኖር የሚያስችል ስምምነት በመሐላ ለመፈ
ጸም አስበናል ፤ በዚህም መሠረት ቃል ኪዳን
እንድትገባልን የምንፈልገው ፥ 29 በእኛ ላይ
ምንም ዐይነት በደል እንዳታደርስብን ነው ፤
ምክንያቱም እኛ በአንተ ላይ ምንም ግፍ አል
ሠራንም ፤ ዘወትር መልካም ነገር አደረግንልህ
እንጂ ክፉ አላደረግንብህም ፤ ከአገራችንም የመ
ጣኸው በሰላም ነው ፤ አሁንም አግዚአብሔር
ባርኮሃል ።” 30 ከዚህ በኋላ ፥ ይስሐቅ ግብዣ
አደረገላቸው ፤ አነርሱም በሉ ፤ ጠጡ ። 31 በማ
ግሥቱ ጠዋት በማለዳ ተነሡና ተማማሉ ፤ ይስ
ሐቅ ካሰናበታቸው በኋላም በሰላም ሄዱ ።
32 በዚያኑ ቀን የይስሐቅ አገልጋዮች መጥ
ተው ስለ ቆፈሩት ጕድጓድ ለይስሐቅ ነገሩት ፤
“ውሃ አገኘን” ብለውም አዘሩት ። 33 እር
ሱም የውሃውን ጕድጓድ “ሳቢህ” ብሎ
ጠራው ፤ ስለዚህም የከተማይቱ ስም እስከ ዛሬ
“ቤርሳቤህ” እየተባለ ይጠራል ።

ዔሳው ከወገኖቹ ውጭ ያደረገው ጋብቻ

34 ዔሳው አርባ ዓመት ሲሆነው የብኤሪን
ልጅ ዮዲትንና የኤሎንን ልጅ ባሴማትን አገባ ፤
ሁለቱም ሒታውያን ነበሩ ። 35 ይህም ጋብቻ
ይስሐቅንና ርብቃን ሲያሳዝናቸው ይኖር ነበር ።

ምዕራፍ 27

ይስሐቅ ያዕቆብን መረቀው

1 ይስሐቅ አርጅቶ ሀይናቸም ታውረው
ነበር ፤ ታላቁን ልጁን ዔሳውን “ልጄ ሆይ!”
ብሎ ጠራው ፤ ልጁም “እነሆ አለሁ” አለ ።
2 ይስሐቅም አንዲህ አለው ፥ “እንደምታየኝ
አርጅቻለሁ ፤ የምሞትበትንም ቀን አላውቅም ፤
3 ስለዚህ የምታድንበትን ቀስትና ፍላጻ ያዝ ፤
ወደ ዱር ሂድና አውሬ አድነህ ሥጋ አምጣ
ልኝ ፤ 4 ልክ እንደምወደው አድርገህ የጣፈጠ

39* 26:20 ዔሚቅ ፦ በዕብራይስጥ "ጠብ" ማለት ነው ። 40* 26:21 ስጥና ፦ በዕብራይስጥ "ተጣቻ" ማለት ነው ።
41* 26:22 ረሐቦት ፦ በዕብራይስጥ "ሰፊ ቦታ" ማለት ነው ።
26:26 ፦ ዘፍ. 21:22 ።

ምግብ ሥራልኝ፤ ከበላሁም በኋላ ከመሞቴ በፊት የመጨረሻ ምርቃቴን እሰጥሃለሁ።”

5 ይስሐቅ ለልጁ ለዔሳው የሚሰውን ሁሉ ርብቃ ትሰማ ነበር፤ ስለዚህ ዔሳው ወደ አደን ከሄደ በኋላ፥ 6 ርብቃ ልጅዋን ያዕቆብን “አባ ትህ ዔሳውን እንዲህ ቢሉው ሰማሁ፥ 7 ‘አውሬ አድነህ ሥጋ አምጣልኝ፤ ልክ እንደምወደው አድርገህ የጣፈጠ ምግብ ሥራልኝ፤ ሳልሞትም በእግዚአብሔር ፊት እመርቅሃለሁ።’ 8 አሁንም ልጄ ሆይ! የምነግርህን አድምጥ፤ የማዝህንም አድርግ፤ 9 አባትህ እንደሚወደው አጣፍጬ ጥሩ ምግብ እንድሠራለት፥ ወደ መንጋዎች ሂደና ሁለት የሰቡ የፍየል ጥቦቶች አምጣ ልኝ፥ 10 አንተም ያዘጋጀሁትን ምግብ እንዲበላ ለአባትህ ወስደህ ታቀርብለታለህ፤ በዚህ ወይነት አባትህ ከመሞቱ በፊት ይመርቅሃል።”

11 ያዕቆብ ግን እናቱን ርብቃን “የወንድሜ የዔሳው ገላ ጠጕራም ነው፤ የእኔ ገላ ግን ምንም ጠጕር የሌለው ለስላሳ ነው፤ 12 ምናል ባት አባቴ ቢዳስሰኝና እንዳታለልኩት ቢያውቅ በምርቃት ፈንታ እርግማን እንደማተርፍ ታውቂ የለምን?” አላት።

13 እናቱም “ልጄ ሆይ! የአንተ እርግማን በእኔ ላይ ይሁን፤ አሁንም እንደነገርሁህ አድ ርግ፤ ሂደህ ጥቦቶቹን አምጣልኝ” አለችው።

14 ለስዚህ ሄዶ ጥቦቶቹን አመጣላት፤ እርስ ዋም ልክ አባቱ እንደሚወደው አድርጋ ጥሩ ወጥ ሠራች፤ 15 የታላቁ ልጅዋን የዔሳውን የክት ልብስ ከተቀመጠበት ቦታ አውጥታ ለያዕ ቆብ አለበሰችው። 16 የፍየሎቹንም ቆዳ በክን ዶቹ ላይና ጠጕር በሌለበት በአንገቱ ላይ አለበ ሰችው። 17 ያዘጋጀችውንም ጥሩ ወጥ ከጋገረ ችው እንጀራ ጋር ለልጅዋ ለያዕቆብ ሰጠችው።

18 ያዕቆብም ወደ አባቱ ሄደና “አባባ!” አለው፤

እርሱም “እነሆ አለሁ! ለመሆኑ አንተ የት ኛው ልጄ ነህ!” አለ።

19 ያዕቆብም “የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ፤ እነሆ እንዳዘዝከኝ አድርጌአለሁ፤ እንድትመር ቀኝ እስቲ ቀና በልና ያመጣሁልህን የአደን ሥጋ ተመገብ” አለው።

20 ይስሐቅም “ልጄ ሆይ! እንዴት በቶሎ ልታገኝ ቻልህ?” አለው።

ያዕቆብም “አምላክህ እግዚአብሔር ስለረ ዳኝ በቶሎ ስማግኘት ቻልሁ” አለው።

21 ይስሐቅም “አስቲ ወደ እኔ ቀረብ በልና ልዳብስህ፤ በእርግጥ አንተ ዔሳው ነህን?” አለው። 22 ያዕቆብም ወደ አባቱ ተጠጋ፤ አባ ቱም ዳሰሰውና “ድምፅ የያዕቆብን ድምፅ ይመስላል፤ ክንድህ ግን የዔሳውን ክንድ ይመስ ላል” አለው። 23 ከንዶቹ እንደ ዔሳው ክንዶች ጠጕራም ስለነበሩ ይስሐቅ ያዕቆብን ሰይቶ ማወቅ አልቻለም፤ ሊመርቀው ከተዘጋጀ በኋላ፥ 24 “በእርግጥ አንተ ልጄ ዔሳው ነህን?” ቢል እንደገና ጠየቀው፤ እርሱም “እም ነኝ” አለ።

25 ይስሐቅም “ልጄ! በል ከአደንህው ሥጋ አቅርብልኝ፤ ከበላሁም በኋላ እመርቅሃለሁ” አለው።

ያዕቆብም ምግቡን አቀረበለት፤ የወይን ጠጅም እንዲጠጣ አመጣለት። 26 ከዚህ በኋላ አባቱ ይስሐቅ “ልጄ ሆይ! ቀረብ በልና ሳመኝ” አለው፤ 27 ያዕቆብም ቀርቦ ሳመው። ይስሐቅ የያዕቆብን ልብስ ባሸተተ ጊዜ እንዲህ ሲል መረቀው፥

“እነሆ የልጄ መልካም ሽታ
እግዚአብሔር እንደባረከው የእርሻ
ሽታ ነው፤
28 እግዚአብሔር ከሰማይ የሚያረስርስ ጠል
ይስጥህ፤
ምድርህን ያሰምልምልህ፤
እህልህንና የወይን ጠጅህን ያብዛልህ፤
29 መንግሥታት ይገዙልህ፤ ሕዝቦችም
ያገልግሉህ፤
በወንድሞችህ ሁሉ ላይ አስቻ ሁን፤
የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ፤
የሚረግሙህ የተረገሙ ይሁኑ፤
የሚመርቁህም የተመረቁ ይሁኑ።”

ዔሳው የይስሐቅን በረከት ለመነ

30 ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ እንዳበቃና ያዕቆ ብም ከአባቱ ፊት እንደወጣ ወዲያው ዔሳው ከአደን ተመልሶ መጣ። 31 እርሱም በበኩሉ የጣፈጠ ወጥ ሠርቶ ለአባቱ አቀረበለትና “አባቴ ሆይ! እንድትመርቀኝ፥ እስቲ ቀና ብለህ ካመጣሁልህ የአደን ሥጋ ብላ” አለው።

32 ይስሐቅም “እንተ ማን ነህ?” አለው።

እርሱም “እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ” አለ።

33 ይስሐቅም እጅግ ደንግጦ እየተንቀጠቀጠ “ታዲያ አውሬ አድኖ ያመጣልኝ ማን ነበር? ልክ አንተ ከመምጣትህ በፊት ተመገብሁ፤ የመጨረሻ ምርቃቴንም ሰጠሁት፤ ምርቃቱም የእርሱ ሆኖ ይኖራል” አለው።

34 ዔሳው ይህን በሰማ ጊዜ ድምፁን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ እያለቀሰ “አባቴ ሆይ! እኔንም መርቀኝ!” አለ።

35 ይስሐቅም “ወንድምህ መጥቶ እኔን በማ ታለል የእንተን ምርቃት ወስዶብሃል” አለው።

36 ዔሳውም “እርሱ እኔን ሲያሰናክለኝ ይህ ሁለተኛው ነው፤ ያዕቆብ መባሉ ተገቢ ነው፤

27፥27-29 ፡- ዘፍ. 11፥20። 27፥29 ፡- ዘኍ. 12፥3። 27፥36 ፡- ዘፍ. 25፥29-34።

ከዚህ በፊት ብኵርናዬን ወሰደብኝ ፥ አሁን ደግሞ ምርቃቴን ቀማኝ ፥ ታዲያ ለእኔ ያስቀረ ኹው ምንም ምርቃት የለምን?" አለው ።

37 ይስሐቅም "ቀደም ብዬ እርሱን የአንተ ጌታ አድርጌዋለሁ ፥ ወንድሞቹ ሁሉ የእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ አድርጌአለሁ ፥ እህልና የወይን ጠጅ እንዲበላለት አድርጌአለሁ ፥ ልጄ ሆይ! እንግዲህ ለአንተ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?" አለው ።

38 ዔሳውም "አባቴ ሆይ! ምርቃትህ አን ዲት ብቻ ናትን? አባክህ እኔንም መርቀኝ" እያለ በማልቀስ አባቱን ነዘነዘው ።

39 ይስሐቅም እንዲህ አለው ፥

"በረከት ከሞላበት ሰምለም ምድር
ርቀህ ትኖራለህ ፥
የሰማይ ጠልም አታገኝም ፥
40 በሰይፍህ ኀይል ትኖራለህ ፥
የወንድምህም አገልጋይ ትሆናለህ ፥
በተቃወምከው ጊዜ ግን ከእርሱ
ጭቈና ትላቀቃለህ ።"

41 አባቱ ስለመረቀው ዔሳው ያዕቆብን አጥ ብቆ ጠላው ፥ በልቡም "አባቴ በቅርብ ቀን ይሞታል ፥ ከዚያ በኋላ ወንድሜን ያዕቆብን እገ ድለዋለሁ" ብሎ አሰበ ።

42 ነገር ግን ርብቃ የዔሳውን ዕቅድ ስለሰ ማች ፥ ያዕቆብን ጠርታ እንዲህ አለችው ፥ "እድምጠኝ ፥ ወንድምህ ዔሳው አንተን በመግ ደል ሊበቀልህ አሰቦአል ፤ 43 አሁንም ልጄ ሆይ! የምልህን አድርግ ፥ ተነሥተህ በካራን ወደሚኖረው ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሽሽ ፥ 44 የወንድምህ ቊጣ እስኪብርድ ድረስ ለጥቂት ጊዜ እዚያው ቆይ ፥ 45 ቊጣውም ሲበርድ ያደ ረግህበትን ነገር ይረሳል ፥ ከዚያ በኋላ በው ልኬ አስመጣሃለሁ ፥ ሁለታችሁንም በአንድ ቀን ማጣት አልፈልግም ።"

ይስሐቅ ያዕቆብን ወደ ላባ ላከው

46 ርብቃ ይስሐቅን "ዔሳው ባገባቸው በእነ ዚህ በሒታውያን ሴቶች ምክንያት መኖሬን ጠላሁት ፤ ያዕቆብ ደግሞ ከነዚህ ከሒታውያን ሴቶች አንዲቱን ካገባ ከመኖር ይልቅ ሞቴን እመርጣለሁ" አለችው ።

ምዕራፍ 28

1 ይሰሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ መረቀው ፥ እንዲ ህም ሲል እዘዘው ፥ "ከነዓናዊት ሴት እንዳታ ገባ ፤ 2 ይልቅስ ተነሥተህ በመስጴጦምያ ወዳ ለው ወደ እናትህ አባት ወደ ባቱኤል ቤት ሂድ ፤ እዚያም ከእኰትህ ከላባ ሴቶች ልጆች አንዲ ን አግባ ፤ 3 ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ይባርክህ ፥ ብዙ ልጆችም ይስጥህ ፥ የብዙ ሕዝ ቦችም አባት ያድርግህ ፤ 4 አብርሃምን እንደባረከ አንተንና ዘርህን ይባርክ ፥ ይህንንም ለአብርሃም ሰጥቶት የነበረውንና አንተም ስደተኛ ሆነህ የኖ ርከበትን ምድር ርስት አድርጎ ይስጥህ ።"

5 በዚህ ሁኔታ ይስሐቅ ያዕቆብን አሰናበ ተው ፥ ያዕቆብም በመስጴጦምያ ወደሚኖረው ወደ ላባ ሄደ ፥ ላባ የያዕቆብና የዔሳው እናት የርብቃ ወንድም ነበረ ፥ እባቱም ሶርያዊው ባቱ ኤል ነበር ።

ዔሳው ሌላ ሚስት አገባ

6 ይስሐቅ ያዕቆብን እንደመረቀውና ሚስት እንዲፈልግ ወደ መስጴጦምያ እንደላከው ዔሳው ተረዳ ፥ ይስሐቅ ያዕቆብን ሲመርቀው "ከነዓናዊት ሴት እንዳታገባ" ብሎ ያዘዘው መሆኑንም ሰማ ፤ 7 ያዕቆብ ለእባቱና ለእናቱ በመታዘዝ ወደ መስጴጦምያ መሄዱንም ተረዳ ፤ 8 በዚህም አባቱ ይስሐቅ የከነዓናውያንን ሴቶች እንደማይወድ ዔሳው ተገንዘበ ፤ 9 ስለዚህ ከዚህ በፊት ካገባቸው ሌላ በተጨማሪ ወደ አብርሃም ልጅ ወደ እሰማኤል ሄዶ ልጁን ማሕላትን አገባ ፥ እርስዋም የነባዮት እኅት ናት ።

ያዕቆብ በቤትኤል ያየው ሕልም

10 ያዕቆብ ቤርሳቤህን ትቶ ወደ ካራን ለመ ሄድ ተነሣ ፤ 11 ፀሐይ በጠለቀች ጊዜ ወደ አንድ ስፍራ መጥቶ በረፈ ፤ በዚያም አንድ ድን ጋይ ተንተርሶ ተኛ ፤ 12 በሕልሙም ከመሬት እስከ ሰማይ የሚደርስ መሰላል አየ ፥ በመሰላ ሉም የእግዚአብሔር መላእክት ወደ ላይ ይወ ጡና ወደ ታች ይወርዱ ነበር ። 13 እግዚአብሔ ርም በአጠገቡ ቆሞ እንዲህ አለው ፥ "እኔ የአባ ትህ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ እግዚአብ ሔር ነኝ ፥ ለአንተና ለዝርያዎችህ እንዲሆን ይህን የተኛህበትን ምድር እሰጥሃለሁ ፤ 14 ዘር ህን እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ ፤ እነርሱ በሁሉ አቅጣጫ ይዘታቸውን ያሰፋፋሉ ፤ በእን ተና በዘርህ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ ። 15 እይዘህ! እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ፤ በምትሄድበ ትም ስፍራ ሁሉ እጠብቅሃለሁ ፤ ወደዚህም ምድር በደህና እመልስሃለሁ ፤ የገባሁልህን ቃል ኪዳን ሁሉ እፈጽምልሃለሁ ፤ ከቶም አልተው ህም ።"

16 ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቃና "በእርግጥ እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ አለ ፤ እኔ ግን ይህን አላወቅሁም ነበር" አለ ። 17 በጣም ፈርቶም ስለነበር "ይህ እንዴት የሚያስፈራ ቦታ ነው ፥ ይህ የእግዚአብሔር ቤት መሆን አለበት ፤ ወደ ሰማይ የሚያስገባው በር ይህ ነው" አለ ።

27:38 ፡- ዕብ. 12:17 ። 27:39-40 ፡- ዕብ. 11:20 ። 27:40 ፡- ዘፍ. 36:8 ፤ 2ነገ. 8:20 ። 28:4 ፡- ዘፍ. 17:4-8 ። 28:12 ፡- ዮሐ. 1:51 ። 28:13 ፡- ዘፍ. 13:14-15 ። 28:14 ፡- ዘፍ. 12:3 ፤ 22:18 ።

18 ያዕቆብ በማግሥቱ ጠዋት በማለዳ ተነሣ፥
ተንተርሶት የነበረውንም ድንጋይ መታሰቢያ
እንዲሆን እንደ ሐውልት አቆመው፥ በላዩ
ላይም የወይራ ዘይት አፈሰሰበት። 19 ያንንም
ሰፍራ "ቤትኤል"[42*] ብሎ ሰየመው፥ ይህ
ሰፍራ ከዚያ በፊት ሎዛ እየተባለ ይጠራ ነበር።
20 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ለእግዚ
አብሔር ተሳለ "ከእኔ ጋር ሆነህ በምትሄድበት
መንገድ ብትጠብቀኝ፥ የሚያስፈልገኝን ምግ
ብና ልብስ ብትሰጠኝ፥ 21 ወደ አባቴም ቤት
በሰላም ብትመልሰኝ፥ አንተ እምላኬ ትሆና
ለህ፥ 22 ይህ ለመታሰቢያነት ያቆምሁት ድንጋይ
ወደ ፊት የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፥ ከምት
ሰጠኝም ሁሉ ከዐሥር አንዱን እጅ ለእንተ እሰ
ጣለሁ።"

ምዕራፍ 29

ያዕቆብ ወደ ላባ ቤት ደረሰ

1 ያዕቆብ ጕዞውን ቀጥሎ በስተምሥራቅ
ወዳለው አገር ደረሰ፥ 2 እዚያም በሜዳ ላይ
አንድ የውሃ ጕድጓድ አየ፥ በሦስት የተከፈሉ
የበግ መንጋዎች በጕድጓዱ ዙሪያ ነበሩ፥ መንጋ
ዎቹ ውሃ የሚጠጡት ከዚሁ ጕድጓድ ነበር፥
ጕድጓዱም የሚዘጋበት ድንጋይ ትልቅ ነበር፥
3 መንጋዎቹ ሁሉ እዚያ ከተሰበሰቡ በኋላ እረ
ኞቹ ድንጋዩን አንከባለው ከጕድጓዱ ውሃ ያጠ
ጡአቸው ነበር፥ መንጋዎቻቸውን ካጠጡ በኋላ
ግን ድንጋዩን መልሰው በጕድጓዱ አፍ ላይ ያስ
ድኑታል።

4 ያዕቆብም እረኞቹን "ወዳጆቼ ሆይ! ከየት
ነው የመጣችሁት?" ብሎ ጠየቃቸው።

እነርሱም "እኛ የመጣነው ከካራን ነው"
አሉት።

5 እርሱም "የናኮርን የልጅ ልጅ ላባን ታው
ቁታላችሁን?" ብሎ ጠየቃቸው።

እነርሱም "አዎ፥ እናውቀዋለን" አሉት።

6 እርሱም "ለመሆኑ እርሱ ደኅና ነውን?"
አላቸው።

እነርሱም "አዎ፥ ደኅና ነው፥ እንዲያውም
ልጁ ራሔል ያችውልህ! በጎች እየነዳች በመም
ጣት ላይ ነች" አሉት።

7 ያዕቆብም "ጊዜው ገና ቀን ነው፥ መንጋ
ዎቻችሁንም ወደ ቤት የምታስገቡበት ሰዓት
ገና አልደረሰም፥ ታዲያ ለምን ውሃ አጠጥታ
ችሁ አታሰማሩአቸውም?" አለ።

8 እነርሱም "እረኞች ሁሉ መንጋዎቻቸውን
ይዘው እዚህ ከመሰብሰባቸው በፊት ምንም
ማድረግ እንችልም፥ ሁሉም እዚህ ከመጡ
በኋላ ግን ድንጋዩን በጎብረት አንከባለን በጎቹን
እናጠጣቸዋለን" አሉት።

9 ያዕቆብም ከእረኞቹ ጋር በመነጋገር ላይ
ሳለ ራሔል የአባትዋን ብጎች ይዛ ወደዚያ
መጣች፥ ምክንያቱም እርሰዋ የበጎች እረኛ ነበ
ረች። 10 ያዕቆብ ያጐቱን የላባን በጎች እየነዳች
ስትመጣ ራሔልን አይቶ ወደ ጕድጓዱ ሄደ፥
ጕድጓዱ የተከደነበትንም ድንጋይ አንከባሎ በጎ
ቹን አጠጣቸው። 11 ከዚህ በኋላ ራሔልን
ሳማት፥ ከደስታውም ብዛት የተነሣ አለቀሰ፥
12 "እኔ የአባትሽ እኅት የሆነችው የርብቃ ልጅ
ነኝ" አላት። እርሰዋም ለአባቷ ልትነግር ሮጣ
ሄደች። 13 ላባም የእኅቱ ልጅ ያዕቆብ መምጣ
ቱን በሰማ ጊዜ ሊቀበለው ፈጥኖ ሄደ፥ አቅፎ
ከሳመውም በኋላ ወደ ቤት አመጣው፥ ያዕቆብ
የሆነውን ሁሉ ለላባ ነገረው፥ 14 ላባም "ዘአር
ግጥ አንተ ቅርብ የሥጋ ዘመዴ ነህ" አለው፥
ያዕቆብም አንድ ወር ያህል ከእርሱ ጋር ተቀ
መጠ።

ያዕቆብ ስለ ራሔልና ስለ ልያ ላባን አገለገለው

15 ላባ ያዕቆብን "ዘመዴ በመሆንህ ብቻ
በነፃ ልታገለግለኝ አይገባህም፥ ሰለዚህ ምን
ያህል ደመወዝ ላስብልህ?" አለው። 16 ላባ
ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት፥ ታላቂቱ ልያ፥
ታናሽቱ ራሔል ይባሉ ነበር። 17 ልያ ዐይነ
ልም ስትሆን፥ ራሔል ግን ቁመናዋ የሚያምር
የደሰ ደሰ ያላት ነበረች።

18 ያዕቆብ ራሔልን እጅግ ሰለወደዳት
"ራሔልን ብትድርልኝ ሰባት ዓመት እገለግልሃ
ለሁ" አለ።

19 ላባም "ለሌላ ሰው ከምሰጣት ይልቅ ሰአ
ንተ ብሰጥህ ይሻለኛል፥ እሺ ተሰማምቼአለሁ፥
አዚህ ከእኔ ጋር ኑር" አለው። 20 ያዕቆብ ራሔ
ልን ለማግባት ሰባት ዓመት አገለገለ፥ ይሁን
እንጂ ራሔልን በጣም ይወዳት ሰለነበር የቆየ
በት ጊዜ ጥቂት ቀን ብቻ መሰሎ ታየው።

21 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ላባን "አኔሆ የአገልግ
ሎት ዘመኔ ተፈጽሞአል፥ ሚስት እንድትሆነኝ
ልጅህን ስጠኝ" አለው። 22 ላባም የሠርግ
ድግስ አዘጋጅቶ በአቅራቢያው የሚገኙትን
ሰዎች ሁሉ ጠራ። 23 ነገር ግን ላባ በራሔል
ምትክ ልያን ለያዕቆብ ሰጠው፥ ያዕቆብም
ከልያ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ።
24 ላባ ሴት አገልጋዩን ዚልፋን አገልጋይዋ እን
ድትሆን ለልጁ ለልያ ሰጣት። 25 በማግሥቱ
ጠዋት ያዕቆብ አብራው ያደረችው ልያ መሆን
ዋን ባወቀ ጊዜ ወደ ላባ ሄዶ "ይህ ያደረግህ
ብኝ ነገር ምንድን ነው? ያገለገልሁህ ራሔልን
ለማግኘት አልነበረምን? ታዲያ ለምን አታለል
ከኝ?" አለው።

26 ላባም "ታላቂቱ ሳትዳር፥ ታናሺቱን
መዳር የአገራችን ልማድ አይደለም፥ 27 የልያ

[42*] 28፡19 ቤትኤል፦ በዕብራይስጥ "የእግዚአብሔር ቤት" ማለት ነው።

ሠርግ ሰባት ቀን አስከ.ሞላው ድረስ ጠብቅ ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰባት ዓመት የምታገለግለኝ ከሆነ ራሔልን እሰጥሃለሁ" አለው ።

28 ያዕቆብም በነገሩ ተስማማ ፤ ከልያ ጋር ሰባት ቀን ተሞሽሮ ከቆየ በኋላ ፥ ላባ ልጁን ራሔልን ለያዕቆብ ዳረለት ። 29 ላባ ሴት አገልጋዩን ባላን አገልጋይዋ እንድትሆን ለልጁ ለራሔል ሰጣት ። 30 ያዕቆብ ከራሔልም ጋር የግ ብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ ፤ ከልያም አብልጦ ወደዳት ፤ ከዚያ በኋላ ላባን ሰባት ዓመት አገለገ ለው ።

ለያዕቆብ ልጆች ተወለዱለት

31 ልያ የራሔልን ያህል እንዳልተወደደች እግዚአብሔር ባየ ጊዜ ልጅ መውለድ እንድት ችል ማሕፀንዋን ከፈተላት ፤ ራሔል ግን መኻን ሆነች ፤ 32 ልያ አርግዛ ወንድ ልጅ ወለደች ፤ "እግዚአብሔር መከራዬን ተመለከተ ፤ ከእንግዲ ህስ ወዲያ ባሌ ይወደኛል" ስትል ስሙን ሮቤል43* አለችው ። 33 እንደገና አረገዘችና ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች ፤ "እግዚአብሔር እንዳልተ ወደደው ሰማ ፤ ይሆንንም ልጅ ደግሞ ሰጠኝ" ስትል ስሙን ስምዖን44* አለችው ። 34 እንደገና አረገዘችና ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች ፤ "እንግ ዲህ ሦስት ወንዶች ልጆች ስለ ወለድሁለት ባሌ ከእኔ ጋር በፍቅር ይጠመዳል" ስትል ስሙን ሌዊ45* አለችው ፤ 35 እንደገና አረገዘችና ወንድ ልጅ ወለደች ፤ "አሁንስ እግዚአብሔርን አመሰ ግናለሁ" ስትል ስሙን ይሁዳ46* አለችው ፤ ከዚህ በኋላ መውለድ አቁረጠች ።

ምዕራፍ 30

1 ራሔል ለያዕቆብ አንድም ልጅ ለመውለድ አለመቻሏን ባወቀች ጊዜ በእኅቷ ቀናችባት ፤ ስለዚህ ያዕቆብን "ልጅ ስጠኝ ፥ አለበለዚያ እሞታለሁ" አለችው ።

2 ያዕቆብም ራሔልን ተቈጥቶ "ልጅ ልሰጥ ሽና ልከለክልሽ የምችል እግዚአብሔር መሰል ኩሽን?" አላት ።

3 እርስዋም "እነሆ አገልጋዬ ባላ እዚህ አለች ፤ በእኔ ምትክ ልጅ እንድትወልድልኝ ከእርስዋ ጋር ተኛ ፤ በዚህ ዐይነት በእርስዋ አማካይነት የልጆች እናት እሆናለሁ" አለ ችው ። 4 ስለዚህ ባላን እንደ ሚስት አድርጋ ሰጠችው ፤ ያዕቆብም ከእርስዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ ። 5 ባላም አረገዘችና ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት ። 6 ራሔልም "እግዚአ ብሔር ፈረደልኝ ፤ ጸሎቴንም ሰምቶ ወንድ ልጅ ሰጠኝ" አለች ፤ በዚህም ምክንያት ሰሙን ዳን47* ብላ ጠራችው ። 7 የራሔል አገልጋይ ባላ ዳግመኛ አረገዘችና ለያዕቆብ ሌላ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤ 8 ራሔልም "ከእኅቴ ጋር ብርቱ ትግል ታግዬ አሸንፋኋት" አለች ፤ ስለዚህ ስሙን ንፍታሌም48* ብላ ጠራችው ።

9 ልያም መውለድ እንዳቆመች በተገነዘበች ጊዜ አገልጋይዋን ዚልፋን አንደ ሚስት አድ ርጋ ለያዕቆብ ሰጠችው ፤ 10 የልያ አገልጋይ ዚልፋ ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት ። 11 ልያም "አንዲት የታደልሁ ነኝ!" ስትል ስሙን ጋድ49* ብላ ጠራችው 12 የልያ አገልጋይ ዚልፋ ለያዕቆብ ሌላ ወንድ ልጅ ወለደችለት ። 13 ልያም "አድማ ደስ ብሎኛል ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ሴቶች ሁሉ 'ደስተኛዋ ሴት!' ይሉ ኛል" ስትል ስሙን አሴር50* ብላ ጠራችው ።

14 በስንዴ መከር ወራት ሮቤል ወደ ዱር ሄዶ እንኮይ አገኘ ፤ ለእናቱ ለልያም አመጣ ላት ፤ ራሔል ልያን "አባክሽ ልጅሽ ካመጣልሽ እንኮይ ስጪኝ" አለቻት ።

15 ልያም "ባሌን የነጠቅሽኝ አንሶሽ ፥ አሁን ደግሞ ልጄ ያመጣልኝን እንኮይ መቀማት ትፈ ልጊያለሽን?" አለቻት ።

ራሔልም "ከልጅሽ እንኮይ ስጪኝና ዛሬ ሌሊት ያዕቆብ ካንቺ ጋር ይደር" አለቻት ።

16 በዚያን ምሽት ያዕቆብ ከዱር ሲመለስ ፥ ልያ ከቤት ወደ እርሱ ወጥታ "በልጄ እንኮይ ስለገዛሁህ ዛሬ ሌሊት የምታድረው ከእኔ ጋር ነው" አለችው ፤ ስለዚህ በዚያን ሌሊት ከእር ስዋ ጋር አደረ ።

17 እግዚአብሔር የልያን ጸሎት ሰማ ፤ ስለ ዚህ አረገዘችና ለያዕቆብ አምስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደችለት ። 18 ልያም "አገልጋዬን ሰባሴ በመስጠቴ እግዚአብሔር ደመወዜን ከፈለኝ" ስትል ይሳኮር51* ብላ ጠራችው ፤ 19 ልያ ዳግ መኛ አረገዘችና ለያዕቆብ ስድስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤ 20 እርስዋም "እግዚአብሔር መልካም ስጦታ ሰጠኝ ፤ ስድስት ወንዶች ልጆች ስለመለድሁለት አሁን ባሌ ያከብረኛል" ስትል ስሙን ዛብሎን52* ብላ ጠራችው ። 21 ከዚህ በኋላ ሴት ልጅ ወለደች ፤ ሰሚንም ዲና53* ብላ ጠራቻት ።

22 እግዚአብሔርም ራሔልን አሰበ ፥ ጸሎትዋ ንም ሰምቶ ልጅ እንድትወልድ አደረጋት ፤

43* 29፡32 ሮቤል ፦ በዕብራይስጥ "ረኤቢን" ሲሆን "እሱ፤ ወንድ ልጅ!" ወይም "መከራዬን አየልኝ" ማለት ነው ።
44* 29፡33 ስምዖን ፦ በዕብራይስጥ "ሰማ" ማለት ነው ። 45* 29፡34 ሌዊ ፦ በዕብራይስጥ "ይጠመዳል" ማለት ነው ።
46* 29፡35 ይሁዳ ፦ በዕብራይስጥ "ምስጋና" ማለት ነው ። 47* 30፡6 ዳን ፦ በዕብራይስጥ "ፈረደልኝ" ማለት ነው ።
48* 30፡8 ንፍታሌም ፦ በዕብራይስጥ "ናፍታሊ" ሲሆን "ትግል" ማለት ነው ። 49* 30፡11 ጋድ ፦ በዕብራይስጥ "መልካም ዕድል" ማለት ነው ። 50* 30፡13 አሴር ፦ በዕብራይስጥ "አሸር" ሲሆን "ደስታ" ማለት ነው ። 51* 30፡18 ይሳኮር ፦ በዕብራይስጥ "ደመወዝ" ማለት ነው ። 52* 30፡20 ዛብሎን ፦ በዕብራይስጥ "ማኦር" ማለት ነው ። 53* 30፡21 ዲና ፦ በዕብራይስጥ "ፈረደ" ማለት ነው ።

23 እርሷም ወንድ ልጅ ወለደች ፤ “እግዚአብ
ሔር ወንድ ልጅ ሰጠኝ ፤ ስድቤንም አስወገደ
ልኝ ፤ 24 ደግሞም ሌላ ወንድ ልጅ ይስጠኛል”
ስትል ስሙን ዮሴፍ[54*] ብላ ጠራችው ።

ያዕቆብ ለለ ደመወዝ ከላባ ጋር ተከራከረ

25 ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ
ላባን እንዲህ አለው ፥ “ወደ ተወለድሁበት
አገር እንድመለስ አሰናብተኝ ፤ 26 እንቲን በማገ
ልገል ያገኘኋቸውን ሚስቶቼንና ልጆቼን ስጠ
ኝና ልሂድ ፤ ምን ያህል አገልግሎት እንዳበረከ
ትኩልህ ታውቃለህ ።”
27 ላባም “በእንተ ምክንያት እግዚአብሔር
እንደባረከኝ በልዩ መገለጥ መረዳቴን ልነግርህ
እወዳለሁ ፤ 28 የምትፈልገውን ደመወዝ ልከ
ንገረኝና እከፍልሃለሁ” አለው ።
29 ያዕቆብም እንዲህ አለው “እንዴት እንዳገ
ለገልሁህና የከብትህም መንጋ በእኔ ጠባቂነት
እንዴት እንደረባልህ አንተ ታውቃለህ ፤ 30 እኔ
ከመምጣቱ በፊት ጥቂት የነበሩት መንጋዎችህ
አሁን እጅግ በዝተዋል ፤ እኔ ዘደረስሁበት
ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔር በረከትን ሰጥቶሃል ፥
ከእንግዲህ ወዲህስ ለቤተሰቤ የሚጠቅም ነገር
ማግኘት አለብኝ” አለው ።
31 ላባም “ታዲያ ምን ያህል ልከፈልህ?”
ብሎ ጠየቀው ።
ያዕቆብም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “እኔ የምል
ህን አንድ ነገር ብቻ ብታደርግልኝ መንጋህን
ማሠማራቴንና መጠበቁን እቀጥላለሁ ፤ 32 ዛሬ
በመንጋዎችህ መካከል ልለፍና ዝንጕርጕርና
ነቁጣ ጥቁርም የሆኑትን በጎች ሁሉ ልለይ ፤
እንዲሁም ነቁጣና ዝንጕርጕር የሆኑትን ፍየ
ሎች እመርጣለሁ ፤ እነርሱም ደመወዜ ይሆ
ናሉ ፤ 33 በዚህ ዐይነት ታማኝነቴ ወደ ፊት
ይታያል ፤ ደመወዜን ለመቈጣጠር ስትመጣ
ዝንጕርጕር ያልሆነ ወይም ነቁጣ የሌለበት
ፍየል ብታገኝ ፥ እንዲሁም ጥቁር ያልሆነ በግ
ብታገኝ የተሰረቀ መሆኑን መረዳት ትችላ
ለህ ።”
34 ላባም “እሺ አንተ ባልከው አሰማማለሁ”
አለ ። 35 ነገር ግን በዚያኑ ቀን ላባ ሽመልመሌ
የሆኑትን ወይም ነቁጣ ያለባቸውን ወንዶች ፍየ
ሎችና ዝንጕርጕር የሆኑትን ነጭ ነጠብጣብ
ያለባቸውን ሴቶች ፍየሎች መረጠ ፤ እንዲሁም
ጥቁር የሆኑትን በጎች ለየና ልጆቹ እንዲጠብቁ
አቸው አደረገ ። 36 ከዚህ በኋላ ላባ መንጋውን
ነድቶ የሦስት ቀን መንገድ ያህል ከያዕቆብ ርቆ
ሄደ ፤ ያዕቆብም የቀሩትን የላባን መንጋዎች
መጠበቁን ቀጠለ ።
37 ያዕቆብም ልብን ፥ ለውዝና ኤርሞን ከሚ
ባሉ እንጨቶች እርጥብ በትሮችን ወሰደ ፤ በዘት
ሮቹ ውስጥ ያለው ነጭ እንዲታይ ሽመልመሌ
አድርጎ ላጣቸው ፤ 38 መንጋዎቹ ውሃ ሰመጠ
ጣት ሲመጡ ከፊት ለፊት እንዲያዩአቸው የተ
ላጡትን በትሮች በውሃ ማጠጫዎቹ ውስጥ አደ
ረጋቸው ፤ መንጋዎቹ ውሃ ለመጠጣት በሚመ
ጡበት ጊዜ ፥ 39 በዱላዎቹ ፊት ለፊት ፍትወት
እየተሰማቸው ይኰመዠ ነበር ፤ ስለዚህ ሽመል
መሌ ፥ ዝንጕርጕርና ነቁጣ የሆኑ ግልገሎችን
ወለዱ ። 40 ያዕቆብ እነዚህን ግልገሎች ለብቻ
ለየ ፤ የቀሩትን ግን ዝንጕርጕርና ጥቁር በሆኑት
በላባ መንጋዎች ፊት ለፊት እቆማቸው ፤ በዚህ
ዐይነት የራሱን መንጋ ወደ ላባ መንጋ ሳይቀላ
ቅል ለብቻ አቆማቸው ።
41 ጤናማና ብርቱ የሆኑት መንጋዎች ፍት
ወት እየተሰማቸው ሲጕመዠ ያዕቆብ በትሮቹን
በፊታቸው ባሉት ውሃ መጠጫዎች ውስጥ ያኖ
ራቸው ነበር ፤ በዚህ ዐይነት በትሮቹን እያዩ
ይፀንሱ ነበር ። 42 ነገር ግን በትሮቹን ዘደካሞቹ
መንጋዎች ፊት ለፊት እያስቀምጣቸውም
ነበር ፤ በዚህ ዐይነት ደካሞቹ መንጋዎች ለላባ
ሲሆኑ ብርቱዎቹ ግን የያዕቆብ ሆኑ ። 43 በዚህ
አኳኋን ያዕቆብ እጅግ ባለ ጸጋ ሆነ ፤ ብዙ መን
ጋዎች ፤ ሴቶችና ወንዶች እገልጋዮች ፥ ብዙ
ግመሎችና አህዮችም ነበሩት ።

ምዕራፍ 31

ያዕቆብ ከላባ ተሰውሮ ሄደ

1 የላባ ወንዶች ልጆች “ያዕቆብ የአባታችንን
ሀብት ወስዶ ፤ ይህን ሁሉ ሀብት ያገኘው ከአባ
ታችን ነው” እያሉ መናገራቸውን ያዕቆብ
ሰማ ። 2 በላባም ዘንድ እንደ ቀድሞው ተወዳጅ
አለመሆኑን ተረዳ ። 3 በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር
ያዕቆብን “ወደ አባቶችህና ወደ ዘመዶችህ
አገር ተመለስ ፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ”
አለው ።
4 ስለዚህ ያዕቆብ መንጋዎቹ ወደ ተሠማሩ
በት መስክ እንዲመጡ ራሔልንና ልያን አስጠ
ራቸው ፤ 5 እንዲህም አላቸው ፥ “አባታችሁ እን
ደቀድሞው ጊዜ እንደማይወደኝ ተረድቻለሁ ፤
ነገር ግን የአባቴ አምላክ ከእኔ ጋር አለ ፤ 6 ኵል
ቤቴን ሳልቈጥብ በትጋት አባታችሁን እንዳገለገ
ልሁ እናንተም ታውቃላችሁ ፤ 7 እርሱ ግን
ዐሥር ጊዜ ደመወዜን በመለዋወጥ አታለለኝ ፤
ሆኖም እኔን ለመጕዳት እግዚአብሔር አልፈቀ
ደለትም ፤ 8 ላባ ‘ዝንጕርጕሮቹ ሁሉ ለእንተ
ደመወዝ ይሁኑ’ ባለኝ ጊዜ ፥ መንጋዎቹ ሁሉ
ዝንጕርጕር ወለዱ ፤ ደግሞም ‘ሽመልመሌ መሳ
ዮቹ ሁሉ ለእንተ ደመወዝ ይሁኑ’ ባለኝ ጊዜ ፥
መንጋዎቹ ሁሉ ሽመልመሌ መሳዮች ወለዱ ።
9 እግዚአብሔር የአባታችሁን የላባን መንጋዎች
ወስዶ ለእኔ የሰጠኝ በዚህ ዐይነት ነው ።

54* 30፡24 ዮሴፍ ፦ በዕብራይስጥ “ይጨምርልኝ” ወይም “እስወገደልኝ” ማለት ነው ።

10 “እንሰሳቱ ለመፅነስ ፍትወት በሚያድርባቸው ወራት የሚያጠቁአቸው አውራ ፍየሎች ሽመልመሌ ፥ ዝንጕርጕርና ነቁጣ መሆናቸውን በሕልም አየሁ ። 11 በዚያው ሕልም የእግዚአብሔር መልአክ ‘ያዕቆብ’ ብሎ ጠራኝ ፤ እኔም ‘እነሆ አለሁ’ አልሁ ። 12 እርሱም እንዲህ አለኝ ፥ ‘መንጋዎቹን የሚያጠቁአቸው አውራ ፍየሎች ሽመልመሌ ፥ ዝንጕርጕርና ነቁጣ ያለባቸው መሆናቸውን ተመልከት ፤ ላባ የፈጸመብህን በደል ሰላየሁ ይህን ያደረግሁት እኔ ነኝ ፤ 13 የመታሰቢያ ድንጋይ አቁመህ ዘይት በመቀባት በተሳልክበት ቦታ በቤትኤል የተገለጥሁልህ አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ፤ አሁንም ከዚህ አገር በፍጥነት ወጥተህ ወደ ተወለድህበት አገር ተመለስ ።’ ”

14 ራሔልና ልያ ለያዕቆብ እንዲህ ሲሉ መለሱለት ፥ “ከአባታችን የምንወርሰው ምንም የለን ፤ 15 እርሱ እኛን የሚያየን እንደ ባዕድ ነው ፤ አስቀድሞ ሸጦን ነበር ፤ አሁን ደግሞ ለእኛ ዋጋ የተከፈለውን ሁሉ አጥፍቶታል ፤ 16 አሁንም እግዚአብሔር ከአባታችን ወስዶ ለእኛ የሰጠህ ሀብት ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ያዘዘህን ሁሉ አድርግ ።”

17-18 ስለዚህ ያዕቆብ በከነዓን ወደሚኖረው ወደ አባቱ ለመሄድ ተዘጋጀ ፤ ልጆቹንና ሚስቶቹን በግመል ላይ አሰቀመጠ ፤ በመለጴጥምያ ሳለ ያገኘውን ሀብትና መንጋዎች አየነዳ ተጓዘ ። 19 ላባ በጎች ሊሸልት ሄዶ ስለነበር ፥ እርሱ ዘሌለበት ራሔል በቤት የነበሩትን የአባቷን ጣዖቶች ሰርቃ ሄደች ። 20 ያዕቆብ መሄዱን ለላባ ሳይገልጥለት አታሎት ሄደ ፤ 21 የራሱ የሆነውን ሀብት ይዞ በፍጥነት ተጓዘ ፤ የኤፍራጥስንም ወንዝ ተሻግሮ ወደ ኮረብታማው አገር ወደ ገለዓድ ሄደ ።

ያዕቆብ በጉዞ ላይ ሳለ ላባ ተከታተለው

22 ያዕቆብ በሰውር መሄዱን ላባ ከሦስት ቀን በኋላ ሰማ ፤ 23 ከዘመዶቹ ጋር ሆኖ ያዕቆብን ተከታተለው ፤ ሰባት ቀን ከተጓዘ በኋላ ገለዓድ በተባለው ተራራማ አገር ላይ ሊደርሰበት ተቃረበ ። 24 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር ለላባ በሕልም ተገለጠለትና “ያዕቆብን ፥ ክፉም ሆነ ደግ አንዳትናገረው ተጠንቀቅ” አለው ። 25 ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኮረብታማ ስፍራ ድንኳኑን በመትከል ሰፍሮ ሳለ ላባ ደረሰበት ፤ ላባና ዘመዶቹም እዘያው ድንኳናቸውን ተክለው ሰፈሩ ።

26 ከዚህ በኋላ ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው ፥ “ለምን እንዲህ አድርገህ አታለልከኝ ፤ ሴቶች ልጆቼንስ በጦርነት እንደተማረኩ ያህል ይዘሃቸው ለምን ሄድህ? 27 ሳትነግረኝ ተሰውረህ በመሄድ ለምን አታለልከኝ? ነግረኸኝ ቢሆን በክብርና ዘመሰንቆ እየተዘፈነ በደስታ በሸኘሁህ ነበር ። 28 ልጆቼንና የልጅ ልጆቼን በመላም እንድሰናበታቸው አላደረግህም ፤ ይህ ያደረግኸው ነገር ስሕተት ነው ። 29 ጕዳት ላደርስብህ አችል ነበር ፤ ነገር ግን ባለፈው ሌሊት የአባትህ አምላክ ‘ያዕቆብን ፥ ክፉም ሆነ ደግ አንድ ቃል እንዳትናገረው’ ብሎ አስጠነቀቀኝ ፤ 30 ወደ ትውልድ አገርህ ለመመለስ ባለህ ብርቱ ፍላጎት እንደተለየኸኝ ሀውቃለሁ ፤ ታዲያ የቤቴን ጣዖቶች የሰረቅህብኝ ለምንድን ነው?”

31 ያዕቆብም “ሴቶች ልጆችህን ነጥቀህ ትወስድብኛለህ ብዬ ስለፈራሁ ነው ፤ 32 ከእኛ መካከል የአንተ ጣዖቶች የተገኙበት ሰው ቢኖር ግን ይሙት ፤ እነሆ አሁን ዘመዶቻችንን ምስክር በማድረግ የአንተ የሆነውን ነገር ሁሉ ፈልገህ ውሰድ” አለው ፤ ያዕቆብ ይህን ያለው ራሔል የአባቷን ጣዖቶች ሰርቃ እንደወሰደች ስላላወቀ ነው ።

33 ከዚህ በኋላ ላባ ወደ ያዕቆብ ወደ ልያና ወደ ሁለቱ አገልጋዮች ድንኳን ተራ በተራ ገብቶ በረበረ ፤ ነገር ግን ምንም አላገኘም ፤ በመጨረሻ ወደ ራሔል ድንኳን ገባ ፤ 34 ራሔል ግን ጣዖቶቹን ወስዳ ብግመሱ ኮርቻ ሥር በመሰወር በላያቸው ላይ ተቀምጣባቸው ነበር ፤ ላባ በድንኳኑ ውስጥ ያለውን ንዝ ሁሉ በርብሮ ምንም ነገር አላገኘም ። 35 ራሔልም አባቷን “ጌታዬ! በወር አበባዬ ምክንያት መነሣት ስላ ልቻልሁ ቅር አትሰኝብኝም” አለችው ። ላባ በሁሉ ስፍራ ፈልጎ ጣዖቶቹን ማግኘት አልቻ ለም ።

36 በዚህ ጊዜ ያዕቆብ እንዲህ ሲል ላባን በቊጣ ቃል ተናገረው ፥ “ታዲያ የፈጸምኩት በደል ምንድን ነው? እስቲ ምን አጥፍቼ ነው እንዲህ የምታሳድደኝ? 37 ዕቃዬን ሁሉ ከበረበርክ በኋላ የአንተ የሆነ ነገር ምን አግኝተሃል? አንዳች ነገር አግኝተህ ቢሆን በአንተና በእኔ ዘመዶች ፊት እዚህ አቅርበው ፤ እነርሱም ከአንተና ከእኔ አጥፊው ማን እንደሆነ ይፍረዱ ። 38 ከአንተ ጋር መኖር ከጀመርኩ ሃያ ዓመት ሆነኝ ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ በጎችህና ፍየሎችህ የጨነገፉብት ጊዜ የለም ፤ ከመንጋህም አንድ ጥቦት እንኳ በልቼ አላውቅም ፤ 39 ከበጎችህ አንዱን አውሬ ሲበላው ወዲያው አከፍልህ ነበር አንጂ የእኔ ስሕተት ያለመሆኑን ለማስረዳት ወደ አንተ አምጥቼው አላውቅም ፤ በቀንም ቢሆን በሌሊት የተሰረቀ እንሰሳ ቢኖር ታለከፋ ሰኝ ነበር ። 40 ብዙ ጊዜ በቀን ሐሩርና በሌሊት ቊር እሠቃይ ነበር ፤ በቂ እንቅልፍ ያገኘሁበት ጊዜ አልነበረም ። 41 ከአንተ ጋር የነበርኩበትን ሃያ ዓመት ያሳለፍሁት በዚህ ሁኔታ ነበር ፤

ከዚህም ዐሥራ አራቱን ዓመት ያገለገልሁህ ሁለቱን ሴቶች ልጆችህን ለማግኘት ብዬ ነው ፤ የቀሩትን ሰድስት ዓመታት ያገለገልሁህ መንጋ ዎችህን ለማግኘት ብዬ ነው ። ይህም ሆኖ ደመ ወዜን ዐሥር ጊዜ ሰዋወጥክብኝ ። 42 አባቴ ይስ ሐቅ የሚያመልከው የአብርሃም አምላክ ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ ባዶ እጄን በሰደድከኝ ነበር ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር መከራዬንና ልፋቴን አይቶ ባለፈው ሌሊት ገሥጾሃል ።”

በያዕቆብና በላባ መካከል የተደረገ ሰምምነት

43 ላባም ያዕቆብን እንዲህ አለው ፥ “እነዚህ ሴቶች የእኔ ልጆች ናቸው ፤ ልጆቻቸውም የእ ኔው ናቸው ፤ እነዚህም መንጋዎች የእኔ ናቸው ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የምታየው ሁሉ የራሴ ነው ፤ ነገር ግን ልጆቼንም ሆነ ልጆቻቸውን ስማሰቀረት ምንም ማድረግ አልቻ ልኩም ፤ 44 ስለዚህ እኔና አንተ በመሐላ የስም ምነት ውል እናድርግ ፤ ስምናደርገው ውል ምስክር ሆኖ እንዲኖር ድንጋይ ሰብስበን በመካ መር ሐውልት እናቁም ።”

45 ስለዚህ ያዕቆብ ትልቅ ድንጋይ አንሥቶ የመታሰቢያ ሐውልት እንዲሆን አቆመው ። 46 ቤተሰቡንም ሁሉ “ድንጋይ ሰብስቡ” አላ ቸው ፤ ድንጋይ ሰብስበው ከቁሰሉ በኋላም በአ ጠገቡ ተቀም"ጠው ምግብ ተመገቡ ። 47 ላባም ይጋርሃዱታ[55*] ብሎ ጠራት ፤ ያዕቆብም ጋል ዔድ ብሎ ሰየማት ። 48 ላባም “እነሆ ዛሬ ይህ የድንጋይ ክብ በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ነው” አለ ፤ ጋልዔድ[56*] ተብላ የተጠራችበት ምክንያት ስዚህ ነው ። 49 ላባም “እንግዲህ ከዚህ በምንለያይበት ጊዜ እግዚአብሔር እኔንና አንተን ይጠብቀን” በማለት ያንኑ ስፍራ ምጽጳ[57*] ብሎ ጠራው ። 50 ላባም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ ፥ “ልጆቼን ብታጉላላ ችው ወይም ሌሎችን ሴቶች በላያቸው ብታገባ ምንም እንኳ እኔ ላውቅ ባልችል እግዚአብሔር ምስክራችን መሆኑን አትርሳ ። 51 በመካከላችን የቈለልሁት ድንጋይና ያቆምሁት ሐውልት እነሆ ፤ 52 እኔ አንተን ስማጥቃት ይህን የድን ጋይ ቍልል እንደማላልፍ ፥ አንተም እኔን ስማ ጥቃት ይህን የድንጋይ ቍልልና ይህን የመታሰ ቢያ ሐውልት እንደማታልፍ ፥ ይህ የድንጋይ ቍልልና ይህ የመታሰቢያ ሐውልት ምስክሮች ናቸው ። 53 ይሆንን ሳናደርግ ብንቀር ግን ከአብ ርሃም አምላክ ፥ ከናኮር አምላኮና ከአባታቸ ውም አምላክ ትጣት ይድረሰብን ።” ከዚህ በኋላ ያዕቆብ አባቱ ይስሐቅ በሚያመልከው አምላክ ስም ይህን ቃል ስመጠበቅ ማለ ። 54 ዘተራራውም ላይ ያዕቆብ መሥዋዕት አቀ ረበ ፤ በዎቹን ሁሉ ጠርቶም ምግብ እንዲመገቡ አደረገ ፤ ከበሉም በኋላ ሌሊቱን በዚያ አሳለፉ ። 55 በማግሥቱ ላባ ጥዋት በማለዳ ተነሥቶ ልጆ ቹንና የልጅ ልጆቹን በመሳምና በመመረቅ ተሰ ናበታቸው ፤ ከዚያም ተነሥቶ ወደ ቤቱ ተመ ለሰ ።

ምዕራፍ 32

ከኤሳው ጋር ስመገናኘት የያዕቆብ ዝግጅት

1 ያዕቆብ በጉዞ ላይ ሳለ የእግዚአብሔር መላ እክት በመንገድ ተገናኙት ። 2 ባያቸውም ጊዜ “እግዚአብሔር ከሠራዊቱ ጋር የሚሠፍርበት ቦታ ነው” አለ ፤ ስለዚህ ያንኑ ቦታ ማሕና ይም[58*] ብሎ ጠራው ።

3 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ በኤዶም አገር ሚዓር ተብላ በምትጠራው ምድር ወደሚኖረው ወደ ወንድሙ ወደ ዔሳው መልእክተኞች አስተድሞ ላከ ። 4 እንዲህም በማለት አዘዛቸው ፥ “ሰጌታዬ ስዔሳው እንዲህ ብላችሁ ንገሩት ፥ ‘ታማኝ አገ ልጋይህ እኔ ያዕቆብ እስከ አሁን የቆየሁት ከላባ ጋር አንደነበር ልንግርህ እወዳለሁ ፤ 5 እነሆ አሁን ብዙ ከብቶች ፥ አህዮች ፥ በጎችና ፍየ ሎች እንዲሁም አሽከሮችና ገረዶች አሉኝ ፤ ይህን መልእክት የላኩብህ በእንተ ዘንድ ሞገስ አገኛሰሁ ዘሚል ተስፋ ነው ።’”

6 መልእክተኞቹም ወደ ያዕቆብ ተመልሰው መጡና “ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሄደን ነበር ፤ እርሱም ከአንተ ጋር ስመገናኘት በመም ጣት ላይ ነው ፤ ከእርሱም ጋር አራት መቶ ሰዎች አሉ” አሉት ። 7 በዚህ ጊዜ ያዕቆብ እጅግ በመፍራት ተጨነቀ ፤ አብረውት የነበሩ ትንም ሰዎች በሁለት ክፍል መደባቸው ፤ እን ዲሁም በጎቹን ፥ ፍየሎቹን ፥ ከብቶቹንና ግመ ሎቹን በሁለት በሁለት መደባቸው ። 8 ይህንንም ያደረገው “ዔሳው መጥቶ በድንገተኛ አደጋ የመጀመሪያውን ክፍል ቢያጠቃ ፥ ሌላው ክፍል ሊያመልጥ ይችላል” ብሎ በማሰብ ነው ።

9 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ጸለየ ፥ “የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ ሆይ ! ልመናዬን እድምጥ ፤ እግዚአብሔር ሆይ ! ‘ወደ ትውልድ አገርህና ወደ ዘመዶችህ ተመለስ ፤ እዚያም መልካም ነገር እንዲሆንልህ እደርጋለሁ’ ብለኸኝ ነበር ። 10 እኔ ባሪያህ ይህን ያህል ቸርነትና ታማኝነት ልታሳየኝ የሚገባኝ

55* 31፡47 ይጋርሃዱታ ፡- በሶርያ ቋንቋ “የምስክር ካብ ወይም ሐውልት” ማለት ነው ። 56* 31፡48 ጋልዔድ ፡- በዕብራይስጥ “የምስክር ካብ ወይም ሐውልት” ማለት ነው ። 57* 31፡49 ምጽጳ ፡- በዕብራይስጥ “መጠበቂያ” ማለት ነው ።
58* 32፡2 ማሕናይም ፡- በዕብራይስጥ “ሰፈሮች” ማለት ነው ።

አልነበርሁም ፤ ዮርዳኖስን ተሻግሬ ስመጣ ከም መረኮዘው በትር በቀር ምንም አልነበረኝም ፤ አሁን ግን እነዚህን በውለት ቡድን የተከፈሉ ወገኖች ይዤ ተመልሻለሁ ። 11 በእኔ ላይ አደጋ በመጣል ቤቶችና ሕፃናት እንኳ ሳይቀሩ ያጠፉ ናል ብዬ ስለፈራሁ ከወንድሜ ከዔሳው እጅ እንድታድነኝ እለምንሃለሁ ፤ 12 ‘መልካም ነገር አደርጋለሁ ፤ ዘርህንም ሲቈጠር እንደማይቻል አንደ ባሕር ዳር አሸዋ አበዛልሃለሁ’ ያልከውን አስታውስ ።”

13 እዚያም አደረ ፤ በማግሥቱም ካለው ነገር ሁሉ ለወንድሙ ለዔሳው ስጦታ የሚሆን ነገር መርጦ አዘጋጀ ፤ 14 በዚህ ዐይነት ሁለት መቶ እንስት ፍየሎች ፥ ሃያ ሰባት ተባዕት ፍየሎች ፥ ሁለት መቶ እንስት በጎች ፥ ሃያ ተባዕት በጎች ፤ 15 ሠላሳ የሚያጠቡ ግመሎች ከነግልገሎቻቸው ፥ አርባ ላሞች ፥ ሀሥር በሬዎች ፥ ሃያ እን ስት አዞዮችና ዐሥር ተባዕት አህዮች መረጠ ፤ 16 እነዚህንም በየመንጋው ከፈለና ለእያንዳንዳ ቸው እረኞች መደበላቸው ፤ እረኞቹንም “ከእኔ ቀድማችሁ ሂዱ ፤ በየመንጋው መካከል ርቀት እንዲኖር አድርጋችሁ ፥ በመካተተል ሂዱ” አላቸው ። 17 የመጀመሪያዎቹንም እረ ኞች እንዲህ በማለት አዘዛቸው ፥ “ወንድሜ ዔሳው በመንገድ አግኝቶ ‘የማን ሰዎች ናችሁ? ወዴትስ ትሄዳላችሁ? እነዚህ የምትነዱአቸው ከብቶች የማን ናቸው?’ ብሎ የጠየቃችሁ እንደ ሆነ ፥ 18 ‘እነዚህ ከብቶች የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው ፤ እርሱ እነዚህን የላከው ለጌታዬ ለዔ ሳው ስጦታ የሚሆን ነው ፤ አነሆ ያዕቆብ ከኋላ ችን ነው’ ብላችሁ ንገሩት ።” 19 ለሁለተኛ ውም ለሦስተኛውም ከፍል እረኞችና ለቀሩ ትም የመንጋ ጠባቂዎች “እናንተም ዔሳውን ስታገኙት እንደዚሁ ንገሩት ፤ 20 ‘ባተለያይም አገ ልጋይህ ያዕቆብ ከበለስተኋላ እየመጣ ነው’ ብላ ችሁ ንገሩት” አላቸው ። ይህንንም ያለበት ምክ ንያት “እኔ ከመድረሱ በፊት በሚደርስለት ስጦታ ቊጣውን አበርድ ይሆናል ፥ በኋላም በማገኘው ጊዜ በደስታ ይቀበለኛል” በማለ አሳብ ነው ። 21 በዚህ ዐይነት ስጦታውን አስቀ ድሞ ከላከ በኋላ እዘያው በሰፈሩበት ቦታ አደረ ።

ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ

22 በዚያኑ ሌሊት ያዕቆብ ተነሣ ሁለቱን ሚስቶቹን ፥ ሁለቱን ሴቶች አገልጋዮቹንና ፥ ዐሥራ አንዱን ልጆቹን ይዞ የያቦቅን መንገ ድ ተሻገረ ። 23 እነርሱን ካሻገረም በኋላ ያለውን ንዝ ሁሉ አሻገረ ። 24 እርሱ ግን ብቻውን ቀረ ፤

ከዚህ በኋላ ሌሊቱ እስኪነጋ ድረስ አንድ ሰው ሲታገለው አደረ ። 25 ያ ሰው ያዕቆብን በት ግል ማሸነፍ እንዳቃተው ዛሮ ጒዜ የጭኑን ሹልዳ መታው ፤ ያዕቆብም በሚታገልበት ጊዜ ጭኑ ከመነጣጠሚያው ላይ ተለያየ ፤ 26 ከዚህ በኋላ ሰውየው “ሌሊቱ ሊነጋ ስለሆነ ልቀቀኝ” አለ ።

ያዕቆብም “ካልባረክኸኝ አልለቅህም” አለው ።

27 ሰውየውም “ስምህ ማን ነው?” አለው ።

“ስሜ ያዕቆብ ነው” አለው ።

28 ሰውየውም ፥ “ከአንግዲህ ወዲህ ስምህ ያዕቆብ አይባልም ፤ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃል ፤ ስለዚህ ለምህ ‘እስራ ኤል’59* ይባላል” አለው ።

29 ያዕቆብም “እንተስ ስምህ ማን ነው” አለው ።

ሰውየውም “ስሜን ለማወቅ የምትፈልገው ለምንድን ነው?” አለውና ያዕቆብን ባረከው ።

30 ያዕቆብም “አኔ አግዚአብሔርን ፊት ለፊት አይቼ እነሆ ፥ በሕይወት አገኛለሁ” አለ ፤ በዚህም ምክንያት ያንን ቦታ “ጵን ኤል”60* ብሎ ጠራው ። 31 ያዕቆብ ከጵንኤል ተነሥቶ ሲሄድ ፀሐይ ወጥቶ ነበር ፤ በጭኑም ሕመም ምክንያት ያነከስ ነበር ። 32 ስለዚህ እስ ራኤላውያን እስከ ዛሬ ድረስ በጭን መጋጠሚያ ላይ ያለውን የሹልዳ ሥጋ አይበሉም ፤ ምክንያ ቱም ያዕቆብ ከሰውየው ጋር ሲታገል ሰውየው ሹልዳውን መትቶት ስለነበር ነው ።

ምዕራፍ 33

ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ተገናኘ

1 ያዕቆብ ቀና ብሎ ሲመለከት ፥ ዔሳው እራት መቶ ሰዎች አስከትሎ ሲመጣ አየ ፤ ያዕ ቆብም ልጆቹን ከልያ ፥ ከራሔልና ከሁለቱ ሴቶች አገልጋዮቹ ጋር ከፋፈላቸው ። 2 በመጀ መሪያ ሁለቱን ሴቶች አገልጋዮቹንና ልጆቻቸ ውን አስቀደመ ፤ ቀጥሎ ልያንና ልጆችዋን አስ ከተለ ፤ በመጨረሻም ራሔልንና ዮሴፍን ከሁሉ በኋላ አደረገ ። 3 ያዕቆብ ከሁሉ ቀድሞ ተጓዘ ፤ ወደ ወንድሙ ወደ ዔሳው ሲቀርብ ወደ መሬት በመጐንበስ ሰባት ጊዜ እጅ ነሣ ፤ 4 ዔሳው ግን ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጠ ፤ በአንገቱም ላይ ተጠምጥሞ እቅፍ አድርጎ ሳመው ፤ ሁለቱም በደስታ ተሳቀሱ ። 5 ዔሳው በዙሪያው ተመል ከቶ ሴቶቹንና ልጆቹን ባየ ጊዜ “እነዚህ ሁሉ ከአንተ ጋር ያሉ ሰዎች የማን ናቸው?” አለ ።

59* 32፡28 እስራኤል ፡- በዕብራይስጥ “ከእግዚአብሔር ጋር ይታገላል” ማለት ነው ። 60* 32፡30 ጵንኤል ፡- በዕብራይስጥ “የእግዚአብሔር ፊት” ማለት ነው ።

32፡12 ፡- ዘፍ. 22፡17 ። 32፡24-26 ፡- ሆሴዕ 12፡3-4 ። 32፡28 ፡- ዘፍ. 35፡10 ። 32፡29 ፡- መሳ. 13፡17-18 ።

ያዕቆብም “ጌታዬ ሆይ! እነዚህ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠኝ ልጆች ናቸው” ሲል መለሰ። 6ከዚህ በኋላ ሴቶች አገልጋዮቹ ከልጆቻቸው ጋር መጥተው እጅ ነሡ። 7ቀጥሎም ልያና ልጆችዋ ቀርበው እጅ ነሡ፤ በመጨረሻም ዮሴፍና ራሔል ቀርበው እጅ ነሡ።

8ዔሳውም “እፈት እፈትስ እየተነዳ ሲሄድ ያየሁት የእንስሳት መንጋ ምንድን ነው?” አለ።

ያዕቆብም “ጌታዬ ሆይ! እርሱ በእንተ ፊት ሞገስ እንዳገኝ የላክሁልህ ነው” አለ።

9ዔሳውም “ወንድሜ ሆይ! እኔ በቂ ሀብት አለኝ፤ የአንተ ለራስህ ይሁን” አለው።

10ያዕቆብ ግን “እንዲህስ እይሁን፤ በእርግጥ የምትወድደኝ ከሆነ እባክህ ስጦታዬን ተቀበል፤ ፍቅር ስላላየሽኝ፥ የእንተን ፊት ማየት የእግዚአብሔርን ፊት እንደማየት ያህል እቈጥረዋለሁ። 11ስለዚህ እባክህ ይህን ያቀረብኩልህን ስጦታ ተቀበለኝ፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ሰጥቶኛል” አለ። ስጦታውን እንዲቀበለው ያዕቆብ ዔሳውን አጥብቆ ለመነው።

12ዔሳውም “እንግዲህ እንሂድ፤ እኔም ከአንተ ቀድሜ እሄዳለሁ” አለ።

13ያዕቆብም እንዲህ አለ፥ “ልጆቹ ደክሞች እንደሆኑ ጌታዬ ታውቃለህ፤ ለሚያጠቡት እንስሳት፥ ለግልገሎቻቸውና ለእንቦሳዎቻቸው መጠንቀቅ ይኖርብኛል፤ ለአንድ ቀን እንኳ በጥድፊያ ቢነዱ እንስሳቱ በሙሉ ያልቃሉ። 14ስለዚህ እባክህ ጌታዬ አንተ ቀድመህ ሂድ፤ እኔም በዝግታ እከተልሃለሁ፤ በእንስሳቱና በልጆቹ ዐቅም ልከ እየተራመድሁ በሴዔር እደርስብሃለሁ።”

15ዔሳውም “እንግዲያውስ ከእኔ ሰዎች ጥቂ ቶቹን ከእንተ ጋር ላስቀርልህ” አለው።

ያዕቆብ ግን “በጌታዬ ፊት ሞገስ ካገኘሁ ሌላ ምንም ነገር አያስፈልገኝም” አለው። 16ስለዚህ ዔሳው በዚያኑ ቀን ጕዞውን በመጀ መር ወደ ሴዔር ተመለሰ። 17ያዕቆብ ግን ወደ ሱኮት[61*] አመራ፤ እዚያም ለራሱ ቤትና ለከብ ቶቹም መጠለያ ሠራ፤ ስለዚህ ያ ስፍራ ሱኮት ተባለ።

18ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ በከነዓን ምድር ወዳለችው ወደ ሴኬም በሰላም ደረሰ፤ እዚያም በከተማይቱ ፊት ለፊት በሚገኘው ሜዳ ላይ ሠፈረ። 19ድንኳኑን የተከለበትን የሴ ኬም አባት ከነበረው ከሐሞር ዝርያዎች ላይ በመቶ ብር ገዛው፤ 20እዚያም መሠዊያ ሠራና “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር” ብሎ ጠራው።

ምዕራፍ 34

የያዕቆብ ሴት ልጅ የዲና መደፈር

1ከዕለታት አንድ ቀን ልያ ለያዕቆብ የወለደች ለት ዲና በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ከነዓናውያን ሴቶች ለማየት ወጣች፤ 2የአገሩ ገዥ የሒዋዊው የሐሞር ልጅ ሴኬም ባያት ጊዜ ያዛት፤ በማስገ ደድም ከብረ ንጽሕናዋን ደፈረ። 3በውሳኔ ተማርኮ እጅግ ወደዳት፤ እርስዋም እንድትወ ደው ለማድረግ በፍቅር ቃል አነጋገራት። 4አባ ቱንም “ከዚህች ልጅ ጋር እጋባኝ” አለው።

5ያዕቆብ ልጁ ዲና ከብረ ንጽሕናዋ እንደተ ደፈረ ሰማ፤ ነገር ግን ወንዶች ልጆቹ የከብት መንጋ ይዘው ተመግርተው ስለነበር፥ እነርሱ እስኪመለሱ ዝም ብሎ ቆየ፤ 6ከዚህ በኋላ የሴኬም አባት ሐሞር፥ ያዕቆብን ለማነጋገር ወጣ፤ 7ልክ በዚያኑ ጊዜ የያዕቆብ ልጆች ከተ ሠማሩበት መጡ፤ ስለተፈጸመው ድርጊት በሰሙ ጊዜ እጅግ ደነገጡ፤ ሴኬም የያዕቆብን ልጅ በመድፈር የእስራኤልን ሕዝብ በማዋረ ዱም እጅግ ተቈጡ፤ ምክንያቱም ይህ ነገር መደረግ አልነበረበትም። 8ሐሞር ግን እንዲህ አላቸው፥ “ልጄ ሴኬም ልጃችሁን በጣም ወዶ አታል፤ ስለዚህ እንዲያገባት ፍቀዱለት፤ 9እን ዲያውም በመካከላችን የጋብቻ ውል እናድ ርግ፤ እኛ የእናንተን ሴቶች ልጆች እናግባ፤ እናንተም የእኛን ሴቶች ልጆች አግቡ። 10በዚህ ወይነት በአገራችን ላይ ከእኛ ጋር መኖር ትችላላችሁ፤ በፈለጋችሁበት ስፍራ በመዘዋወር እየሠራችሁና እየነገዳችሁ በብልጽ ግና መኖር ትችላላችሁ።”

11ሴኬምም፥ በበኩሉ የዲናን አባትና ወን ድሞችዋን እንዲህ አላቸው፥ “አሳቤን ብትፈጽ ሙልኝ የምትፈልጉትን ሁሉ አደርጋለሁ፤ 12ለሙሽራዋም ጥሎሽ የፈለጋችሁትን ያህል ጠይቁኝ፤ እርሰዋን እንዳገባ ፍቀዱልኝ እንጂ፥ የፈለጋችሁትን ሁሉ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ።”

13ሴኬም እኅታቸውን ዲናን አስነውሮ ስለነ በር የያዕቆብ ልጆች ለእርሱና ለአባቱ ለሐሞር በተንኰል እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፥ 14“እኅ ታችንን ያልተገረዘ ሰው እንዲያገባት አንፈቅ ድም፤ ይህ ለእኛ ታላቅ ውርደት ነው፤ 15እር ስዋን ለመስጠት የሚያስችለን አንድ መንገድ ብቻ አለ፤ ይኼውም አንተና የአገርህ ወንዶች ሁሉ እንደኛ የተገረዛችሁ እንደሆነ ነው። 16እንዲህ ከሆነ እናንተ የእኛን ሴቶች ልጆች ታገባላችሁ፤ እኛም የእናንተን ሴቶች ልጆች እናገባለን፥ እንድ ሕዝብ ሆነንም አብረን እንኖ ራለን። 17አላባችንን ባትቀበሉና ባትገረዙ ግን እኅታችንን ይዘን እንሄዳለን።”

61* 33፡17 ሱኮት ፡- በዕብራይስጥ “መጠለያ ወይም ጸዳ” ማለት ነው ፥
33፡19 ፡- ኢያሱ 24፡32 ፣ ዮሐ. 4፡5 ።

18 ይህም የውል ድርድር ለሐሞርና ለልጁ
ለሼኬም መልካም መስሎ ታያቸው ፤
19 ሼኬም ፥ የያዕቆብን ልጅ እጅግ ወዶአት ስለ
ነበር የተነገረውን ሁሉ ለማድረግ ምንም ጊዜ
አልወሰደበትም ፤ ከዚህም በላይ በቤተሰቡ
ውስጥ እጅግ የተከበረ በመሆኑ የፈለገውን ለማ
ድረግ መብት ነበረው ።
20 ስለዚህ ሐሞርና ልጁ ሼኬም በከተማው
በር እጠገብ ወዳለው መሰብሰቢያ ቦታ ሄዱ ፤
ለከተማይቱ ነዋሪዎች እንዲህ በማለት ንግግር
አደረጉ ፤ 21 “እነዚህ ሰዎች ከእኛ ጋር የሚኖ
ሩት በሰላም ነው ፤ በምድሪቱ ላይ አብረውን
ይቀመጡ ፤ በነፃም ይዘዋወሩባት ፤ እነሆ ! ምድ
ሪቱ ለእኛም ለእነርሱም ትበቃናለች ፤ የእነር
ሱን ሴቶች ልጆች እናግባ ፤ የእኛንም ሴቶች
ልጆች እንዳርላቸው ። 22 ሆኖም እነዚህ ሰዎች
አብረውን ለመኖርና ከእኛም ጋር አንድ ሕዝብ
ለመሆን ፈቃደኞች የሚሆኑት ወንዶች የሆንን
ሁሉ እንደነርሱ ለመገረዝ የተስማማን እንደሆነ
ነው ። 23 እንዲህ ብናደርግ እኮ መንጋዎቻቸ
ውና ከብቶቻቸው ፥ ሌላውም ንብረታቸው ሁሉ
የእኛ ይሆናል ፤ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ስምም
ነት እናድርግ ፤ እነርሱም ከእኛ ጋር ይኑሩ ።”
24 የከተማይቱ ነዋሪዎች ሁሉ ሐሞርና ሼኬም
ባቀረቡት እሳብ ተስማምተው ወንዶች ሁሉ
ተገረዙ ።
25 በሦስተኛው ቀን ሰዎቹ ገና ከመገረዝ
ቍስል ሳይድኑ ከያዕቆብ ልጆች መካከል ሁለቱ
የዲና ወንድሞች ስምዖንና ሌዊ ሰይፍ ፥ ሰይፋ
ቸውን ይዘው ማንም ሳያውቅባቸው ወደ ከተማ
ገቡና ወንዶቹን ሁሉ ገደሉ ። 26 ሐሞርንና
ልጁን ሼኬምን ሳይቀር በሰይፍ ከገደሉ በኋላ ፥
ዲናን ከሼኬም ቤት መሰደው ሄዱ ። 27 የቀሩ
ትም የያዕቆብ ልጆች ወደ ሞቱት ሰዎች ቤት
እየገቡ እጎታቸው የተደፈረችበትን ከተማ
በሙሉ ዘረፉ ። 28 የበግና የፍየል መንጋዎቻቸ
ውን ፥ ከብቶቻቸውን ፥ አህዮቻቸውንና በከተ
ማና ከከተማ ውጭ የነበራቸውን ንብረት ሁሉ
ዘርፈው ወሰዱ ። 29 ሴቶችንና ሕፃናትን ማረኩ ፤
በየቤቱ ያገኙትን ሀብት ሁሉ ዘረፉ ።
30 ያዕቆብ ስምዖንና ሌዊን እንዲህ አላቸው ፥
“በእኔ ላይ ክባድ ችግር አመጣችሁብኝ ፤ እኔሆ
በዚህ ድርጊት የተነሣ በዚህች ምድር የሚኖሩ
ከነዓናውያንና ፈሪዛውያን ይጠሉኛል ፤ እኛ
በቍጥር እንስተኞች ነን ፤ እነርሱ ተባብረው
ቢያጠቁን እኔና ቤተሰቤ እንጠፋለን ።”
31 እነርሱ ግን “የፈለገው ቢሆን እኅታችን
እንደ አመንዝራ ሴት ስትደፈር አይተን መታ
ገሥ አንችልም ” አሉ ።

ምዕራፍ 35

እግዚአብሔር ያዕቆብን በቤትኤል ባረከው

1 እግዚአብሔር ያዕቆብን “አሁን ተነሥተህ
ወደ ቤትኤል ሂድና እዘያ ኑር ፤ በዚያም ከወን
ድምህ ከዔሳው ሸሽተህ በሄድህ ጊዜ ልትገለጥሁ
ልህ እምላክ ለእኔ መሠዊያ ሥራልኝ” አለው ።
2 ስለዚህ ያዕቆብ ለቤተሰቡና አብረውት ለነ
በሩት ሰዎች ሁሉ እንዲህ አላቸው ፥ “በእናንተ
ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልክት አስወግዱ ፤
ሰውነታችሁን እንጹ ፥ ንጹሕ ልብስም ልበሱ ፤
3 ከዚህ ተነሥተን ወደ ቤትኤል እንሄዳለን ፤
በዚያም ከዚህ በፊት በተቸገርሁ ጊዜ ለረዳኝና
በሄድኹበት ስፍራ ሁሉ ከእኔ ላልተለየኝ አም
ላክ መሠዊያ እሠራለሁ ።” 4 ስለዚህም በእርሱ
ዘንድ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት ሁሉ እምተ
ተው ለያዕቆብ ሰጡት ፤ እንዲሁም በየጆሮእ
ቸው አድርገውት የነበረውን ጕትቻ ሁሉ አው
ልቀው ሰጡት ፤ እርሱም ሁሉንም ወሰደና በሴ
ኬም አጠገብ በነበረው የወርካ ዛፍ ሥር ቀበ
ረው ።
5 ያዕቆብና ልጆቹ ያንን ስፍራ ትተው ለመ
ሄድ ተነሡ ፤ እግዚአብሔር በዙሪያቸው በነበ
ሩት ሰዎች ላይ ፍርሃትና ድንጋጤ ስላሳደረባ
ቸው ሊያሳድዱአቸው አልደፈሩም ። 6 ያዕቆብ
አብረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር ሆኖ ወደ ሎዛ
ደረሰ ፤ ሎዛ ቤትኤል ተብላ የምትጠራው በከነ
ዓን ምድር የምትገኝ ስፍራ ናት ። 7 ያዕቆብ
እዚያ መሠዊያ ሠርቶ “ኤል ቤትኤል”62* ብሎ
ሰየመው ፤ ምክንያቱም ከወንድሙ ፊት ሸሽቶ
በሄደበት ጊዜ እግዚአብሔር የተገለጠለት በዚህ
ስፍራ ነበር ። 8 እዚያም የርብቃ ሞግዚት
ዲቦራ ሞተች ፤ ከቤትኤል በስተደቡብ ባለውም
ወርካ ሥር ተቀብረች ፤ ስለዚህም ያ ዛፍ አሎን
ባኩት63* ተባለ ።
9 ያዕቆብ ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ እግ
ዚአብሔር ዳግመኛ ተገለጠለትና ባረከው ።
10 ደግሞም “ስምህ ያዕቆብ ነው ፤ ከእንግዲህ
ወዲህ ግን እስራኤል ትባላለህ እንጂ ያዕቆብ
ተብለህ አትጠራም ” አለው ። ስለዚህም እግዚአ
ብሔር ያዕቆብን “እስራኤል” ብሎ ጠራው ።
11 ደግሞም እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ
አለው “ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ ፤ ብዙ
ልጆች ይኑርህ ፤ ዘርህም ይብዛ ፤ የብዙ ሕዝብ
አባት ሁን ፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወለዱ ።
12 ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠሁትን ምድር
ለአንተም እሰጥሃለሁ ፤ ይህንኑ ምድር ከአንተም
በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ ።” 13 እግዚአብሔር ከእ
ርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ከዚያ ስፍራ ወደ ላይ

62* 35፥7 ኤል ቤትኤል ፦ በዕብራይስጥ “የቤትኤል አምላክ” ማለት ነው ። 63* 35፥8 አሎን ባኩት ፦ በዕብራይስጥ “የለቅሶ ወርካ” ማለት ነው ።

35፥1 ፦ ዘፍ. 28፥11-17 ። 35፥10 ፦ ዘፍ. 32፥28 ። 35፥11-12 ፦ ዘፍ. 17፥4-8 ።

ወጣ ። 14 ያዕቆብ ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
በተነጋገረበት ስፍራ መታሰቢያ የሚሆን የድን
ጋይ ሐውልት አቆመ ፤ የመጠጥ ቍርባንና ዘይት
በላዩ አፍስሶም ቀደሰው ፤ 15 ያዕቆብ ፥ እግዚአ
ብሔር ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን ይህንኑ
ስፍራ "ቤትኤል" ብሎ ጠራው ።

የራሔል ሞት

16 ያዕቆብና ቤተሰቡ ከቤትኤል ሰቀው
ሄዱ ፤ ገና ከኤፍራታ ብዙ ርቀው ሳይሄዱ የራ
ሔል መውለጃ ጊዜ ደረሰና በከባድ ምጥ ተያ
ዘች ። 17 ምጥ እየበረታ በሄደ ጊዜ አዋላጅዋ
"ራሔል ሆይ ! ሌላ ወንድ ልጅ መውለድሽ ስለ
ሆነ አይዞሽ እትፍሪ !" አለቻት ። 18 እርስዋ ግን
ልትሞት ታጣዋር ስለነበር ከመሞቷ በፊት
ልጅዋን "ቤንኢ"64* አለችው ፤ አባቱ ግን
"ብንያም"65* አለው ።

19 ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ ራሔል ሞተች ፤
እሁን ቤተ ልሔም ተብሎ በሚጠራው መደ
ኤፍራታ በሚወስደው መንገድ ዳር ተቀበረች ።
20 ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ ለመታሰቢ
ያዋ የሚሆን የድንጋይ ሐውልት አቆመ ። ይህም
ሐውልት እስከ ዛሬ ድረስ የራሔልን መቃብር
ያመለክታል ። 21 ያዕቆብ ጕዞውን ቀጥሎ በዔ
ያ፫ር ግንብ ባሻገር ድንኳን ተክሎ ሠፈረ ።

የያዕቆብ ልጆች
(1 ዜ.መ. 2፡1-2)

22 ያዕቆብ በዚያ ምድር ሲኖር ሳለ ፥ ሮቤል
ከእባቱ ቍባት ከባላ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት
እደረገ ፤ ያዕቆብም ይህን ነገር ሰማ ። የያዕቆብ
ወንዶች ልጆች ዐሥራ ሁለት ናቸው ።

23 የልያ ልጆች ፥ የያዕቆብ የመጀመሪያ
ልጅ ሮቤል ፥ ስምዖን ፥
ሌዊ ፥ይሁዳ ፥ ይሳኮርና ዛብሎን
ናቸው ።
24 የራሔል ልጆች ፥ ዮሴፍና ብንያም
ናቸው ።
25 የራሔል አገልጋይ የነበረችው የባላ
ልጆች ፥ ዳንና ንፍታሌም ናቸው ።
26 የልያ አገልጋይ የነበረችው የዚልፋ
ልጆች ጋድና አሴር ናቸው ።
እነዚህ ወንዶች ልጆች ያዕቆብ በመስጴጦ
ምያ ባለ የተወለዱለት ናቸው ።

የይስሐቅ ሞት

27 ያዕቆብ በኬብሮን አጠገብ መምሬ ወይም
ትባል ስፍራ ወደሚኖረው አባቱ ወደ ይስሐቅ
ሄደ ፤ ይህም ስፍራ አብርሃምና ይስሐቅ የኖሩ
በት ነው ። 28 ይስሐቅ መቶ ሰማንያ ዓመት
ኖረ ፤ 29 ዕድሜ ጠግቦ ካረጀ በኋላ ሞተ ፤ ልጆ
ቹም ዔሳውና ያዕቆብ ቀበሩት ።

ምዕራፍ 36

የዔሳው ዝርያዎች
(1 ዜ.መ. 1፡34-37)

1 ኤዶም የተባለው የዔሳው የትውልድ ታሪክ
የሚከተለው ነው ፤ 2 ዔሳው ከነዓናውያን ሴቶ
ችን አገባ ፤ እነርሱም የሒታዊው የኤሎን ልጅ
ዓዳ ፥ የሒዋዊው የጺባዖን ልጅ ዐና የመለዳት
እሆሊባማና ፥ 3 የነባዮት እኅት የነበረችው የእሰ
ማኤል ልጅ ባሴማት ናቸው ። 4 ዓዳ ለዔሳው
ኤሊፋዝን መለደችለት ፤ ባሴማትም ረዑኤልን
መለደችለት ፤ 5 እሆሊባማም የዑሻን ፥ ያዕላም
ንና ቆራሕን መለደችለት ። እነዚህ ሁሉ ለዔሳው
በከነዓን ምድር የተወለዱለት ልጆች ናቸው ።

6 ከዚህ በኋላ ዔሳው ሚስቶቹን ወንዶችና
ሴቶች ልጆቹን ፥ በቤቱ የሚገኙትን ሰዎች
ሁሉ መንጎቹንና ሌሎቹንም ከብቶች ሁሉ ፥
በከነዓን ሳለ ያፈራውን ንብረት ሁሉ ይዞ ከወን
ድሙ ከያዕቆብ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደ ። 7 ይህን
ንም ያደረገበት ምክንያት እርሱና ያዕቆብ ብዙ
ንብረት ስለነበራቸው ፥ የሚስፍሩበት ምድር
ለሁለት ስላልበቃ ነው ፤ ሁለቱም ብው እንስ
ሳት ስለነበሩአቸው አብረው ለመኖር አልቻ
ሉም ። 8 ስለዚህ ኤዶም የተባለው ዔሳው በተራ
ራማው አገር በዔዓር ተቀመጠ ።

9 በተራራማው አገር በዔዓር ይኖሩ የነበ
ሩት ኤዶማውያን ቅድመ አያት የነበረው የዔ
ሳው ዝርያዎች የሚከተሉት ናቸው ፤ 10 ዔሳው
ከሚስቱ ከዓዳ ኤሊፋዝን ፥ ከሚስቱ ከባሴማት
ረዑኤልን መለደ ።

11 የኤልፋዝ ልጆች ፦ ቴማን ፥ አማር ፥
ጸፎ ፥ ጋዕታምና ቀናዝ ናቸው ።

12 የዔሳው ልጅ ኤሊፋዝ ቲመናዕ የምትባል
የጭን ገረድ ነበረችው ፤ እርስዋ ለኤሊፋዝ ዘማ
ሌቅን መለደችለት ፤ እነዚህም የዔሳው ሚስት
የዓዳ የልጅ ልጆች ናቸው ። 13 የረዑኤል
ልጆች ፦ ናሐት ፥ ዘራሕ ፥ ሻማና ሚዛ ናቸው ፤
እነዚህም ዔሳው ባሴማት ከምትባለው ሚስቱ
የወለዳቸው የልጅ ልጆች ናቸው ።

14 የዐና ልጅና የጺባዖን የልጅ ልጅ የነበረ
ችው አሆሊባማ ለዔሳው የወለደቻቸው ልጆች ፥
የዑሽ ፥ ያዕላምና ቆራሕ ናቸው ።

15 የዔሳው መጀመሪያ ልጅ የኤልፋዝ ነገድ
አለቆች ፦ ቴማን ፥ አማር ፥ ጸፎ ፥ ቀናዝ ፥

64* 35፡18 ቤንኢ ፦ በዕብራይስጥ "የሐዘኔ ልጅ" ማለት ነው ። 65* 35፡18 ብንያም ፦ በዕብራይስጥ "ቤንያሚን" "ቀኝ እጅ" ሲሆን "የመልካም ዕድል ልጅ" ማለት ነው ።
35፡14-15 ፦ ዘፍ. 28፡18-19 ። 35፡22 ፦ ዘፍ. 49፡4 ። 35፡27 ፦ ዘፍ. 13፡18 ። 36፡2 ፦ ዘፍ. 26፡34 ።
36፡3 ፦ ዘፍ. 28፡9 ።

16 ቆራሕ ፥ ገዕታምና ዐማሌቅ ፤ እነዚህ በኤ
ዶም የኤልፋዝ ነገድ አለቆች ሲሆኑ ፥ እነር
ሱም ዔሳው ከሚስቱ ከዓዳ የወለዳቸው
ናቸው ።
17 የዔሳው ልጅ የረዑኤል ነገድ አለቆች ፦
ናሐት ፥ ዘራሕ ፥ ሻማና ሚዛ ሲሆኑ እነዚህ በኤ
ዶም የረዑኤል ነገድ አለቆች ናቸው ፤ እነር
ሱም ዔሳው ከሚስቱ ከባሴማት የወለዳቸው
ናቸው ።
18 ከዔሳው ሚስት ከአሆሊባማ የተወለዱት
የነገድ አለቆች ፦ የዑሽ ፥ ያዕላምና ቆራሕ
ናቸው ፤ እነዚህ የዐና ልጅ ከሆነችው ከአሆሊ
ባማ የተወለዱ የዔሳው ዝርያዎች የነገድ አለ
ቆች ናቸው ። 19 እነዚህ ሁሉ ኤዶም የተባለው
የዔሳው ልጆችና የነገድ አለቆች ናቸው ።

የሴዒር ዝርያዎች
(1 ዜ.መ. 1፡38-42)

20 በኤዶም ምድር ነዋሪዎች የነበሩት የሴ
ዒር ልጆች የሆኑ የሐሪውያን አለቆች ፦
ሎጣን ፥ ሾባል ፥ ጺብዖን ፥ ዐና ፥ 21 ዲሾን ፥
ኤጼርና ፥ ዲሻን ናቸው ።
22 ሎጣን የሐሪና የሄማም ጉሳዎች ቅድመ
አያት ነበረ ። ሎጣን ቲምናዕ የተባለች እኅት
ነበረችው ።
23 የሾባል ልጆችም ዓልዋን ፥ ማናሐት ፥
ዔባል ፥ ሰፎና ፥ አናም ናቸው ።
24 የጺብዖን ልጆችም አያና ዐና ናቸው ።
ይህም ዐና የአባቱን አህዮች ሲጠብቅ በበረሓ
ውስጥ የፍል ውሃ ምንጮችን ያገኘ ሰው ነው ።
25 የዐናም ልጅ ዲሾን የተባለው ነው ፤ ሴት
ልጁም አሆሊባማ ትባላለች ።
26 የዲሾን ልጆች ሔምዳን ፥ ኤሽባን ፥ ይት
ራንና ፥ ከራን ናቸው ።
27 የኤጼር ልጆች ቢልሃን ፥ ዛዕዋንና ፥ ዓቃን
ናቸው ።
28 የዲሻን ልጆች ዑጽና አራን ናቸው ።
29 የሐረው አለቆች የሚከተሉት ናቸው ፤
ሎጣን ፥ ሾባል ፥ ጺብዖን ፥ ዐና ፥ 30 ዲሾን ፥
ኤጼር ፥ ዲሻን ፤ እነዚህ ሁሉ በሴዒር ምድር
አለቆች የሆኑ የሐረው ዝርያዎች ናቸው ።

የኤዶም ነገሥታት
(1 ዜ.መ. 1፡43-54)

31 በእስራኤል ንጉሥ መንግሥት ከመጀመሩ
በፊት በኤዶም ምድር የነገሡት ነገሥታት የሚ
ከተሉት ናቸው ፤
32 የበዖር ልጅ ቤላዕ በኤዶም ነገሠ ፤ የነገሠ
ባትም ከተማ ዲንሃባ ትባል ነበር ።
33 ቤላዕ በሞተ ጊዜ የቦጽራ አገር ተወላጅ
የዘራሕ ልጅ ዮባብ በእርሱ እግር ተተክቶ
ነገሠ ።
34 ዮባብም በሞተ ጊዜ የቴማን አገር ተወ
ላጅ ሑሻም በእርሱ እግር ተተክቶ ነገሠ ።
35 ሑሻምም በሞተ ጊዜ የምድያምን ሰዎች
በሞአብ ሜዳ ድል የመታው የበዳድ ልጅ
ሀዳድ በእርሱ ተተክቶ ነገሠ ፤ የነገሠባትም
ከተማ ዐዊት ትባል ነበር ።
36 ሀዳድ በሞተ ጊዜ የማሥሬቃ ተወላጅ
ሣምላ በእርሱ እግር ተተክቶ ነገሠ ።
37 ሣምላ በሞተ ጊዜ በወንዝ አጠገብ ያለ
ችው የረሖቦት ተወላጅ የነበረው ሻኡል በእ
ርሱ ተተክቶ ነገሠ ። 38 ሻኡል በሞተ ጊዜ የዐክ
ቦር ልጅ በዐል ሐናን በእርሱ እግር ተተክቶ
ነገሠ ።
39 የዐከቦር ልጅ ባዓል ሐናንም በሞተ ጊዜ
ሀዳር በእርሱ እግር ተተክቶ ነገሠ ፤ የነገሠባ
ትም ከተማ ፋው ትባል ነበር ፤ ሚስቱም የሜዛ
ሃብ ልጅ ማጥሬድ የወለደቻት መሄጣብኤል
ትባል ነበር ።
40 የሚከተሉትም የዔሳው ዝርያ የነገድ አለ
ቆች በየጐሳቸው ስምና በየሚኖሩበት ቦታ ስም
ይጠራሉ ፤ ቲምናዕ ፥ ዐልዋ ፥ ዬቴት ፥ 41 አሆሊ
ባማ ፥ ኤላ ፥ ፊኖን ፥ 42 ቀናዝ ፥ ቴማን ፥ ሚብ
ጻር ፥ 43 ማግዲኤልና ዒራም ። በየመኖሪያ ሰፍ
ራቸው ስም የሚጠሩት የኤዶም አለቆች እነ
ዚህ ናቸው ። ይህም ዔሳው የኤዶማውያን አባት
ነው ።

ምዕራፍ 37
ዮሴፍና ወንድሞቹ

1 ያዕቆብ ተቀማጭነቱን እባቱ በኖረበት በከ
ነዓን ምድር አደረገ ። 2 የያዕቆብ ዝርያዎች
ታሪክ እንደሚከተለው ነው ፤
ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነበረ
በት ጊዜ ከአባቱ ሚስቶች ከባሳና ኤዘልፋ ከተ
ወለዱት ወንድሞቹ ጋር በጎችና ፍየሎች ይጠ
ብቅ ነበር ፤ ወንድሞቹ የሚፈጽሙትንም ዘደል
እያመጣ ለአባቱ ይነግር ነበር ።
3 ያዕቆብ ዮሴፍን ከሌሎች ልጆች ሁሉ አብ
ልጦ ይወደው ነበር ፤ ምክንያቱም በሸተር፟ጅና
የወለደው ስለሆነ ነው ፤ ስለዚህም ጌጠኛ የሆነ
እጀ ሙሉ ልብስ ሰፋለት ። 4 ወንድሞቹም አባ
ታቸው ከእነርሱ ይልቅ ዮሴፍን እንደሚወድ
ባዩ ጊዜ በመቅናት ጠሉት ፤ መልካም ቃልም
ሊናገሩት አልወደዱም ።
5 አንድ ሌሊት ዮሴፍ ሕልም አየ ፤ ሕል
ሙን ለወንድሞቹ በነገራቸውም ጊዜ ከቀድ
ሞው ይበልጥ ጠሉት ። 6 እርሱም እንዲህ አላ
ቸው “ያየሁትን ሕልም ልንገራችሁ ፤ 7 እኛ
ሁላችን በእርሻ ውስጥ የስንዴ ነዶ እናስር
ነበር ፤ የእኔ ነዶ ተነሣና ቀጥ ብሎ ቆመ ፤ የእና
ንተ ነዶዎች ዙሪያውን ተሰብስበው ለእኔ ነዶ
ሰገዱለት ።”

8 ወንድሞቹም “ታዲያ በእኛ ላይ ንጉሥ
ሆነህ ልትገዛን ታስባለህን?” ብለው ጠየቁት።
ስላየው ሕልምና የአነርሱንም በደል ለአባቱ
በመናገሩ ይብልጥ እየጠሉት ሄዱ።
9 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ሌላ ሕልም አይቶ ወን
ድሞቹን “እነሆ፥ ሌላ ሕልም አየሁ፤ በሕል
ሜም ፀሐይ፥ ጨረቃና ዐሥራ አንድ ከዋክብት
ሰገዱልኝ” አላቸው።
10 ይህንኑ ለወንድሞቹ የነገራቸውን ሕልም
ለአባቱም በነገረው ጊዜ፥ አባቱ “ይህ ምን ዐይ
ነት ሕልም ነው? እኔና እናትህ ወንድሞችህም
የምንሰግድልህ ይመስልሃልን?” ብሎት ገሠ
ጸው። 11 የዮሴፍ ወንድሞች እጅግ ቀኑበት፤
አባቱ ግን ይህን ነገር በልቡ እያሰላሰለ ይጠብ
ቀው ነበር።

ወንድሞቹ ዮሴፍን ሸጡት

12 አንድ ቀን የዮሴፍ ወንድሞች የአባታቸ
ውን መንጋዎች ይዘው ወደ ሴኬም ተሠማሩ፤
13 እስራኤልም ዮሴፍን “እነሆ ወንድሞችህ
መንጋውን ይዘው ወደ ሴኬም መሰማራታቸውን
ታውቃለህ፤ ስለዚህ ወደ እነርሱ ልልክህ እፈል
ጋለሁ” አለው።
ዮሴፍም “እሺ እሄዳለሁ” አለ።
14 አባቱም “በል እንግዲህ ሂድና የወንድሞ
ችህንና የመንጋዎቹን ደኅንነት አይተህ ንገረኝ”
አለው። በዚህ ዐይነት እስራኤል ዮሴፍን ከኬብ
ሮን ሸለቆ ላከው። ዮሴፍ ሴኬም ደረሰ።
15 አዚያም በየዱሩ ሲባዝን ሳለ አንድ ሰው
አገኘውና “ምን እየፈለግህ ነው?” ብሎ ጠየ
ቀው።
16 ዮሴፍም “ወንድሞቼን እየፈለግሁ ነው፤
መንጋዎቻቸውን ይዘው ወዴት እንደተሠማሩ
ልትነግረኝ ትችላለህን?” አለው።
17 ሰውየውም “እነርሱ ከዚህ ሄደዋል፤
‘ወደ ዶታን እንሂድ’ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ”
አለው። ስለዚህ የወንድሞቹን ዱካ ተከትሎ
ሄደና በዶታን አገኛቸው።
18 እነርሱም በሩቅ አዩት፤ ወደ እነርሱም
ከመድረሱ በፊት ሊገድሉት ተማከሩ። 19 እርስ
በርሳቸውም “እነሆ፥ ያ ሕልም አላሚ መጣ፤
20 እንግዲህውና ከእነዚህ ከደረቁት ጕድጓ
ዶች በአንዳኛው ውስጥ እንጣለው፤ ከዚህ
በኋላ ‘ክፉ አውሬ በላው’ ብለን ማመካኘት
እንችላለን፤ በዚህ ዐይነት የሕልሙን መጨረሻ
እናያለን” አሉ።
21 ሮቤል ይህንን የአድማ ምክር በሰማ ጊዜ
ከእጃቸው ለማዳን በመፈለግ “ተዉ፥ እይዞ
ንም፥ ባንገድለው ይሻላል፤ 22 ከምትገድሉት
ይልቅ በዚህ በበረሓ ባለው ጕድጓድ ውስጥ
ጣሉት” አላቸው። ሮቤል ይህንን ያለው ከእጃ
ቸው እድኖ ወደ አባቱ ሊመልሰው ፈልጎ
ነው። 23 ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ በደረሰ ጊዜ
ጌጠኛ የሆነውን እጀ ሙሉ ልብሱን እወሰቁ
በት፤ 24 ዮሴፍንም ወስደው ውሃ በሌለው
ደረቅ ጕድጓድ ውስጥ ጣሉት።
25 ከዚህ በኋላ ምግብ ሰመብላት ተቀመጡ፤
በሚመገቡበትም ጊዜ አስማኤላውያን ነጋዴዎ
ችን በሩቅ አዩ፤ እነርሱም በግመሎቻቸው
ቅመማ ቅመም፥ በለሳን፥ ከርቤም ጭነው ከገለ
ዓድ ወደ ግብጽ የሚጓዙ ነበሩ።
26 በዚህ ጊዜ ይሁዳ ወንድሞቹን እንዲህ አላ
ቸው “ወንድማችንን ገድሰን የእሚሚቱን
ሁኔታ ብንደብቅ ምን ይጠቅመናል? 27 በእርሱ
ላይ ጕዳት ከምናደርሰበት ይልቅ ለእነዚህ አስ
ማኤላውያን ነጋዴዎች ብንሸጠው ይሻላል፤
ምክንያቱም እርሱ የሥጋ ወንድማችን ነው።”
ወንድሞቹም በዚህ አሳብ ተስማሙ። 28 የምድ
ያም ነጋዴዎች የሆኑ አስማኤላውያን በዚያ
በኩል ያልፉ ነበር፤ ስለዚህ ወንድሞቹ ዮሴፍን
ከጕድጓድ ጕትተው በማውጣት ለእነዚህ አስማ
ኤላውያን በሃያ ብር ሸጡላቸው፤ እነርሱም
ወደ ግብጽ ይዘውት ሄዱ።
29 ሮቤል ወደ ጕድጓዱ መመለቱ ዮሴፍ በዚያ
አለመኖሩን ባወቀ ጊዜ በሐዘን ልብሱን ቀደደ፤
30 ወደ ወንድሞቹም ሄደና “እነሆ ልጁ እዚያ
የለም! እንግዲህ እኔ ወዴት ብሄድ ይሻለ
ኛል?” አለ።
31 ከዚህ በኋላ አንድ ፍየል ወሪዱና የዮሴፍን
ልብስ በደም ነከሩት። 32 ብዙ ሕብር ያለበት
ንም ልብሱን ወደ አባታቸው ወስደው “እነሆ፥
ይህን አገኘን የልጅህ ልብስ እንደሆነ ወይም
እንዳልሆነ እይ” አሉት።
33 እርሱም የልጁ ልብስ መሆኑን ተረድቶ
“በእርግጥ የእርሱ ልብስ ነው፤ አንድ ክፉ
አውሬ ገድሎታል፤ ልጄን ዮሴፍን አውሬ ቦጫ
ጭቆ በልቶታል” አለ። 34 ከዚህ በኋላ ልብሱን
በሐዘን ቀደደ፤ የሐዘን ልብስ ሰብሶም ለልጁ
ብዙ ቀናት አለቀሰ። 35 ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ
ሁሉ ሊያጽናኑት ወደ እርሱ መጡ፤ እርሱ ግን
“ስልጁ እያለቀሰሁ ወደ ሙታን ዓለም እወርዳ
ለሁ” በማለት መጽናናትን እምቢ አለ። ስለዚህ
ስለ ልጁ ማዘኑን ቀጠለ።
36 በዚያን ጊዜ የምድያም ሰዎች የሆኑ አስ
ማኤላውያን ዮሴፍን በግብጽ አገር ለጰጢፋር
ሸጡት፤ ጰጢፋር ከፈርዖን ባለሥልጣኖች
አንዱ የሆነ የዘበኞቹ አለቃ ነበር።

ምዕራፍ 38

ይሁዳና ትዕማር

1 በዚያም ወራት ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለ
ይቶ ሒራ ወደሚሉት ዐዲላማዊ ሰው ዘንድ

ሄዶ ፥ መኖሪያውን እዚያ አደረገ ። 2እዚያም
ይሁዳ የከነዓናዊውን የሹዓን ሴት ልጅ አየ ፤
እርስዋንም አግብቶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት
ፈጸመ ። 3እርስዋም እርግዝ ወንድ ልጅ ወለደ
ችለት ፤ ስሙንም ዔር ብላ ጠራችው ። 4እንደገ
ናም አረገዘችና ወንድ ልጅ ወለደችለት ፥ ስሙ
ንም እናን ብላ ጠራችው ፤ 5እንደገናም ወንድ
ልጅ ወለደች ስሙንም ሼላ ብላ ጠራችው ፤
እርሱንም የወለደችው ይሁዳ አክዚብ በሚባል
ቦታ በሚኖርበት ጊዜ ነው ።

6ይሁዳ የመጀመሪያ ልጁን ዔርን ትዕማር
ከምትባል ልጃገረድ ጋር አጋባው ። 7ዔር በእ
ግዚአብሔር ፊት ክፉ ስው ስለነበረ ፥ እግዚአ
ብሔር በሞት ቀሠፈው ። 8ይሁዳ የዔርን ወን
ድም እናንን "ሂድና ከወንድምህ ሚስት ጋር
የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ በደንቡ
መሠረት ለወንድምህ መጠሪያ የሚሆን ዘር
አስቀርለት" አለው ። 9እናን የሚወለዱት
ልጆች የእርሱ ያለመሆናቸውን በማወቁ ከወን
ድሙ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባደ
ረገ ቍጥር አባስ ዘሩን ወደ ምድር ያፈሰው
ነበር ፤ በዚህ ዐይነት በወንድሙ ስም ልጆች
እንዳይወለዱ እደረገ ። 10ይህን በማድረጉ እግ
ዚአብሔርን ስላሳዘነ እግዚአብሔር እርሱንም
በሞት ቀሠፈው ። 11ከዚህ በኋላ ይሁዳ ምራ
ቱን ትዕማርን "ልጄ ሼላ እስከሚያድግበት
ጊዜ ድረስ ሂጂና በአባትሽ ቤት መበለት
ሆነሽ ኑሪ" አላት ። ይህንንም ያስው እንደ
ወንድምቹ ይሞትብኛል ብሎ ስለ ስጋ ነበር ፤
ስለዚህ ትዕማር ሄዳ በአባቷ ቤት ተቀመ
ጠች ።

12በርከት ካሉ ዓመታት በኋላ የሹዓ ልጅ
የሆነችው የይሁዳ ሚስት ሞተች ፤ ይሁዳ ከሐ
ዙኡ ከተጽናና በኋላ ከወዳጁ ከዐዱላማዊው
ከሐራ ጋር በጎቹን ለማሸለት ወደ ቲምና ሄደ ።
13ሰዎቹም ለትዕማር "አማትሽ በጎቹን ለማሸ
ለት ወደ ቲምና ይሄዳል" ብለው ነገሩአት ።
14ስለዚህ ትዕማር የመበለትነት ልብሷን ለውጣ
ፊቷን በሻሽ ሸፈነች ፤ ወደ ቲምና በሚወስደው
መንገድ ዳር በዔናይም ደጅ ተቀመጠች ፤ ይህን
ንም ያደረገችው ሼላ አድጎ ሳለ ስእርሱ በሚስ
ትነት እንድትሰጥ አለመፈቀዱን ስለተረዳች
ነው ።

15ፊቷን በሻሽ ሸፍና ስለነበር ይሁዳ ባያት
ጊዜ አመንዝራ ሴት መሰለችው ። 16ምራቱ እን
ደሆነች ሳያውቅ እርስዋ ወደተቀመጠችበት
ወደ መንገድ ዳር ወጣ አለና "እባክሽ ከእንቺ
ጋር እንድተኛ ፍቀጂልኝ" ብሎ ጠየቃት ።
እርስዋ "ፈቃድህን ብፈጽም ምን ትሰጠኛ
ስህ?" አለችው ።

17እርሱም "ከመንጋዎቼ መካከል አንድ
የፍየል ጥቦት እልክልሻለሁ" አላት ።
እርስዋም "እሺ እንግዲያውስ ጥቦቱን እስክ
ትልክልኝ ድረስ መያዣህ የሚሆን ነገር
ስጠኝ" አለችው ።

18እርሱም "ታዲያ መያዣህ የሚሆን ነገር
ምን ልስጥሽ?" አላት ።
እርስዋም "የማኅተም ቀለበትህን ከነማሰሪያ
ውና ይህን የያዝከውን በትር ስጠኝ" አለችው ።
ስለዚህ የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣትና ከእርስዋ
ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ ፤ እርስዋም
አረገዘችለት ። 19ከዚያ በኋላ ሻሽዋን ከፊቷ ላይ
እንሥታ የመበስትነት ልብሷን እንደገና ለበ
ሰች ።

20ይሁዳ በመያዣያ መልክ የሰጣትን ነገሮች
ለማስመለስ የፍየል ጥቦት በዐዱላማዊው ሰው
እጅ ወደ ሴትዮዋ ላከ ፤ ሰውየው ግን ሊያገኛት
አልቻለም ። 21ሰውየውም እዚያ የሚኖሩትን
ሰዎች "በዔናይም ደጅ በመንገድ ዳር የነበረ
ችው አመንዝራ ሴት ወዴት ሄደች?" ብሎ
ጠየቀ ።

ሰዎቹም "በዚህ አካባቢ እንደዚህ ያለች
አመንዝራ ሴት የለችም" አሉት ።
22ስለዚህ ሰውየው ወደ ይሁዳ ተመልሶ
ሄደና "ላገኛት አልቻልኩም ፤ በዚያ የሚኖሩ
ትም ሰዎች 'እንደዚህ ያለች አመንዝራ ሴት
እዚህ የለችም' አሉኝ" ብሎ ነገረው ።
23ይሁዳም "እንግዲህ ጥቦቱን ልኬላት
ነበር ፤ ነገር ግን ልታገኛት አልቻልክም ፤ ስለ
ዚህ ሰዎች መሳቂያ እንዳያደርጉን የወሰደች
ውን መያዣያ እዚያው ታስቀረው" አለ ።
24በሦስተኛው ወር ገደማ ሰዎች "ምራትህ
ትዕማር የዝሙት ሥራ ፈጸመች ፤ ከዚህም የተ
ነሣ አርግዛለች" ብለው ለይሁዳ ነገሩት ።
ይሁዳም "ወደ ውጪ አውጥታችሁ በእሳት
አቃጥላችሁ ግደሉአት" አለ ።
25እርስዋም ተይዛ ውጪ በምትወጣበት
ጊዜ "እኔ ያረገዝሁት የእነዚህ ዕቃዎች ባለቤት
ከሆነ ሰው ነው ፤ ይህን የማኅተም ቀለበት ከነማ
ሰሪያውና ይህንንም በትር ተመልከተህ የማን
እንደሆኑ ዕወቅ" ብላ ለወግቷ ለይሁዳ ላከች
ሰት ።

26ይሁዳም ዕቃዎቹ የማን እንደሆኑ ዐውቆ
"ከልጄ ከሼላ ጋር ስላላጋባኋት እርስዋ ከእኔ
ይልቅ ትክክለኛ ሆና ተገኘች" አለ ፤ ከእርስ
ዋም ጋር ዳግመኛ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አላደ
ረገም ።

27የመውለጃዋ ቀን በተቃረበ ጊዜ በማሕፀ
ንዋ ውስዋ መንታ ልጆች መኖራቸው ታወቀ ።
28በምትወልድበትም ጊዜ ከመንትያዎቹ አንዱ
እጁን አወጣ ፤ አዋላጂቱም ሴት ቀይ ከር በእጁ
ላይ አሰረችለትና "ይህ በመጀመሪያ ወጣ"
አለች ። 29ነገር ግን እጁን በመለሰው ጊዜ ወን
ድሙ ቀድሞት ተወለደ ፤ አዋላጂቱም ሴት

"እንዴት ጥሰህ ወጣህ?" አለች ፤ ስለዚህ የመ
ጀመሪያው ልጅ ስም "ፋሬስ" ተባለ ።66* 30 ከዚህ በኋላ በእጁ ላይ ቀይ ክር የነበረው
ወንድሙ ተወለደ ፤ ስሙም ዛራሕ ተባለ ።

ምዕራፍ 39

ዮሴፍና የጰጢፋር ሚስት

1 እስማኤላውያን ነጋዴዎች ዮሴፍን ወደ
ግብጽ ወሰዱት ፤ እዚያም ከግብጽ ንጉሥ ፈር
ዖን ባለሥልጣኖች አንዱ ለሆነው ለጰጢፋር
ሸጡት ፤ ጰጢፋር የተባለው ግብጻዊ ፥ የፈርዖን
የዘበኞች አለቃ ነበር ። 2 እግዚአብሔር ከዮሴፍ
ጋር ነበር ፤ ስለዚህም በግብጻዊው አሳዳሪው
ቤት ሲኖር ሁሉ ነገር ተቃናለት ። 3 እግዚአብ
ሔር ከዮሴፍ ጋር እንደነበረና ሥራውንም ሁሉ
እንዳቃናለት በየ ጊዜ ፥ 4 ጰጢፋር ዮሴፍን ወደ
ደው ፤ የቅርብ አገልጋዩም አደረገው ፤ በቤቱ
ላይ አዛዥነትን ፥ በንብረቱም ሁሉ ላይ ጎላፊነ
ትን ሰጠው ። 5 ይህም ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እግ
ዚአብሔር ዘዮሴፍ ምክንያት የግብጻዊውን ሰው
ቤት ንብረትና በውጭም በእርሻ ያለውን ሀብት
ሁሉ ባረከለት ። 6 ስለዚህ ጰጢፋር ያለውን ንብ
ረት ሁሉ ዘዮሴፍ ቊጥጥር ሥር አደረገ ፤ ስለ
ዚህ ጰጢፋር ከሚመገበው ምግብ በስተቀር
የሚያውቀው ምንም ነገር አልነበረም ። ዮሴፍ
ቁመናው የተስተካከለ መልከ መልካም ሰው
ነበር ። 7 ከጊዜ በኋላ የጌታው ሚስት ዮሴፍን
ተመልክታ ስለ አፈቀረችው ፥ "ና ከእኔ ጋር
አብረን እንተኛ" አለችው ። 8 እርሱ ግን ይሆን
ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆነም ፤ ስለዚህም እን
ዲህ አለ "ጌታዬ ሁሉንም ነገር በእኔ ጎላፊነት
ሥር ስላደረገ ፥ በቤቱ ውስጥ ስላለው ንብረት
ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም ፤ ያለውን
ንብረት ሁሉ እንዳስተዳድርለት በወደራ ሰእኔ
ሰጥቶኛል ። 9 ጌታዬ በዚህ ቤት ባለው ንብረት
ሁሉ ላይ ከእኔ የበለጠ ጎላፊነት የለውም ፤ ከአ
ንቺ በቀር በእኔ ቊጥጥር ሥር ያላደረገው
ምንም ነገር የለም ፤ ይሄውም ሚስቱ ስለሆንሽ
ነው ፤ ታዲያ ይህን አስከፊ ኃጢአት በመፈጸም
እግዚአብሔርን እንዴት እሳዝናለሁ?" 10 እርስ
ዋም ይህንኑ ጕዳይ በየቀኑ ትነግረው ነበር ፤
ዮሴፍ ግን እብሮአት መተኛት ይቅርና በአ
ጠገቢ ለመገኘት አልፈለገም ።

11 ከአንታት አንድ ቀን ዮሴፍ ለሥራ ጕዳይ
ወደ ቤት ሲገባ በቤት ውስጥ አንድም ሠራተኛ
አልነበረም ። 12 በዚያን ጊዜ የጌታው ሚስት
ልብሱን ይዛ "ከእኔ ጋር ተኛ" አለችው ፤
እርሱ ግን ልብሱን እጅዋ ላይ ትቶላት ከቤት
ሸሽቶ ወጣ ። 13 እርስዋም ልብሱን በእጅዋ ላይ
ትቶ ከቤት ሸሽቶ መውጣቱን በተመለከተች
ጊዜ ፥ 14 አገልጋዮችዋን ጠርታ እንዲህ አለቻ
ችው ፥ "እነሆ ፥ ባለቤቴ ያመጣው ይህ ዕብራዊ
ሊያዋርደን ነበር ፤ ወዳለሁበት ክፍል ገብቶ
ሊደፍረኝ ሞከረ ፤ እኔ ግን ድምፄን ከፍ አድ
ርጌ ጮኽሁ ። 15 ዕርዳታ ለማግኘትም መጮ
ኼን በሰማ ጊዜ ልብሱን አጠገቤ ትቶ ከቤት
ሸሽቶ ወጣ ።"

16 የዮሴፍ አሳዳሪ እስኪመጣ ድረስ ልብሱን
በእርስዋ ዘንድ አቆየችው ። 17 በመጣም ጊዜ
የሆነውን ታሪክ እንዲህ ሰትል ዘርዝራ ነገረ
ችው ፥ "እንተ ወደዚህ ያመጣኸው ዕብራዊ
አገልጋይ ወዳለሁበት ክፍል ገብቶ ሊያዋርደኝ
ነበር ። 18 ነገር ግን ዕርዳታ ለማግኘት ድምፄን
ከፍ አድርጌ ዘመኽሁ ጊዜ ልብሱን እጠገቤ
ትቶ ከቤት ሸሽቶ ወጣ ።"

19 ሚስቱ "የእንተ አገልጋይ እንዲህ አደረ
ገኝ" ብላ የነገረችውን ታሪክ በሰማ ጊዜ የዮ
ሴፍ አሳዳሪ እጅግ ተቈጣ ። 20 ስለዚህ ዮሴፍን
ወስዶ የንጉሡ እስረኞች ወዳሉበት እስር ቤት
አስገባው ። ነገር ግን ዮሴፍ በእስር ቤት በነበረ
በት ጊዜ ፥ 21 እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ
ዘላለማዊ ፍቅሩን አሳየው ፤ በእስር ቤቱ አዛዥ
ዘንድ ባለሟልነትን እንዲያገኝ አደረገው ።
22 በዚህ ዐይነት በእስረኞቹ ሁሉ ላይና በእስር
ቤቱ ውስጥ በሚደረገው ነገር ሁሉ ላይ ጎላፊ
አደረገው ። 23 እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ሆኖ
የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንዲቃናለት ስላደረገ
የእስር ቤቱ አዛዥ በዮሴፍ ቊጥጥር ሥር በነበ
ረው ነገር ምንም አሳብ አልነበረበትም ።

ምዕራፍ 40

ዮሴፍ የእስረኞቹን ሕልም ተረጐመ

1 ይህ ከሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የግብጽ
ንጉሥ ፈርዖን የወይን ጠጅ አሳላፊና የእንጀራ
ቤት ጎላፊ ንጉሡን የሚያሳዝን በደል ፈጸሙ ።
2 ፈርዖን በወይን ጠጅ አሳላፊውና በእንጀራ
ቤት ጎላፊው እጅግ ተቈጣ ። 3 ስለዚህ ዮሴፍ
ታስሮ ወደሚገኝበት ወደ ዘበኞች አለቃ ቤት
ተወሰደው እንዲታሰሩ አደረገ ። 4 የእስር ቤቱም
አዛዥ ለዮሴፍ እስረከባቸው ፥ ዮሴፍም ያገለግላ
ቸው ነበር ። በእስር ቤትም ለጥቂት ጊዜ ቆዩ ።

5 የንጉሡ የወይን ጠጅ አሳላፊና የእንጀራ
ቤት ጎላፊ ሁለቱም በእስር ቤት ሳሉ በአንድ
ሌሊት ሕልም አዩ ፤ የአያንዳንዳቸው ሕልም
የተለያየ ትርጕም ነበረው ።

6 በማግሥቱ ጠዋት ዮሴፍ እነርሱ ወዳሉበት
ክፍል በገባ ጊዜ ተክዘው አገኛቸውና ፥ 7 "ዛሬ
በፊታችሁ ላይ ሐዘን የሚታየው ለምንድን
ነው?" አላቸው ።

66* 38፡29 ፋሬስ ፦ በዕብራይስጥ "ፋሬጽ" ማለት ሲሆን "ጣስ" ማለት ነው ።
39፡2 ፦ ሐ.ሥ. 7፡9 ። 39፡21 ፦ ሐ.ሥ. 7፡9 ።

[8]እነርሱም "እያንዳንዳችን ሕልም አየን፥
ነገር ግን የእያንዳንዳችንን ሕልም የሚተረጕም
ማንም የለም" አሉት።
ዮሴፍም "ሕልም የመተርጐም ችሎታ የሚ
ሰጥ እግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህ የእያንዳንዳች
ሁን ሕልም ንገሩኝ" አላቸው።
[9]የወይን ጠጅ አሳላፊው እንዲህ በማለት
ሕልሙን ተናገረ፥ "በሕልሜ አንድ የወይን
ተክል አየሁ፤ [10]በተከሉም ላይ ሦስት ሐረጎች
ነበሩ፤ ቅጠሉ ለምልሞ ወዲያው አበባ አወጣ፤
የወይን ዘለላውም ወዲያው በሰለ፤ [11]የፈርዖን
ጽዋ በእጄ ነበረ፤ የወይኑን ፍሬ ወስጄ በጽ
ዋው ውስጥ ጨመቅሁና ጽዋውን ለፈርዖን ሰጠ
ሁት።"
[12]ዮሴፍም እንዲህ አለ፥ "የሕልሙ
ትርጕም ይህ ነው፤ ሦስቱ የወይን ሐረጎች
ሦስት ቀናት ናቸው፤ [13]በሦስት ቀን ጊዜ
ውስጥ ንጉሡ ከእስራት ይፈታሃል፤ በደልህንም
ይቅር ብሎ ወደ ቀድሞው ማዕርግህ ይመልስ
ሃል፤ ቀድሞ የመጠጥ ቤት ጎላፊ ሆነህ ታደር
ገው እንደነበር የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰጠዋ
ለህ። [14]ነገር ግን ሁሉ ነገር በተቃናልህ ጊዜ
እኔን አስታውሰህ ዕርዳኝ፤ ለፈርዖንም አሳስበህ
ከእዚህ ከእስር ቤት እንድወጣ አድርገኝ።
[15]ምክንያቱም እኔ ከዕብራውያን አገር ወደዚህ
የመጣሁት ወድጄ ሳይሆን ተሸጬ ነው፤ እዚ
ህም አገር ከመጣሁ ዋዲህ በእስር ቤት የምገ
ኘው ምንም በደል ሳልፈጽም ነው።"
[16]የእንጀራ ቤት ጎላፊውም ዮሴፍ ስወይን
ጠጅ አሳላፊው ሕልም የሰጠው ትርጕም መል
ካም መሆኑን ባየ ጊዜ፥ የእርሱንም ሕልም ሰየ
ሴፍ እንዲህ ብሎ ነገረው፥ "እኔም በበኩሌ ያየ
ሁት ሕልም ይህ ነው፥ 'ሦስት መሶብ እንጀራ
በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር፤ [17]ከሁሉ በላይ
ባለው መሶብ ውስጥ ለፈርዖን የተዘጋጀ ልዩ
ልዩ ምግብ ነበረበት፤ ነገር ግን ወፎች ምግቡን
ከመሶቡ እያነሡ ይበሉት ነበር።'"
[18]ዮሴፍም "የሕልሙ ትርጕም እንዲህ
ነው፤ ሦስት መሶቦች ሦስት ቀናት ናቸው፤
[19]በሦስት ቀን ጊዜ ውስጥ ፈርዖን ከዚህ እስር
ቤት አውጥቶ ራስህን ካስቈረጠ በኋላ በእንጨት
ላይ ያስቅለሃል፤ ወፎችም ሥጋህን ይበሉ
ታል።"
[20]በሦስተኛው ቀን የፈርዖን ልደት በዓል
ስለነበረ ስመኳንንቱ ሁሉ ግብዣ አደረገ፤ በዚ
ያኑ ቀን የወይን ጠጅ አሳላፊውና የእንጀራ
ቤት ጎላፊው ከእስር ቤት ወጥተው በመኳንንቱ
ፊት እንዲቀርቡ አደረገ። [21]የወይን ጠጅ አሳላ
ፊውን ወደ ቀድሞ ማዕርጉ መለሰው፤ ስለዚህ
የወይን ጠጅ ጽዋውን ለንጉሡ መስጠት
ጀመረ። [22]የእንጀራ ቤት ጎላፊውን ግን እንዲ
ሰቀል አደረገው፤ ሁሉም ነገር ዮሴፍ የእያንዳ
ንዳቸውን ሕልም እንደተረጐመው ሆነ።
[23]የወይን ጠጅ አሳላፊው ግን ዮሴፍን አላስ
ታወሰውም፤ ስለ ዮሴፍ የሆነውን ሁሉ ረሳ።

ምዕራፍ 41

ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም ተረጐመ

[1]ከሁለት ዓመት በኋላ የግብጽ ንጉሥ ፈር
ዖን ሕልም አየ፤ እርሱ በሕልሙ በዓባዩ ወንዝ
ዳር ቆሞ ነበር፤ [2]ሰባት የወፈሩና የሰቡ ላሞች
ከወንዙ ወጥተው ግር ሲብሉ አየ፤ [3]ቀጥሎም
አጥንታቸው እስከሚታይ የከሱ ሌሎች ሰባት
ላሞች ከወንዙ ወጥተው አስቀድመው ከወንዙ
ዳር ከነበሩት ላሞች አጠገብ ቆሙ። [4]የከሱት
ላሞች የወፈሩትን ላሞች ዋጡአቸው፤ በዚህ
ጊዜ ንጉሡ ከእንቅልፉ ነቃ። [5]ተመልሶም እን
ቅልፍ በወሰደው ጊዜ እንደገና ሌላ ሕልም
አየ፤ በሕልሙም በአንድ የእህል አገዳ ላይ
ሰባት የዳበሩና ያማሩ የእሸት ዛላዎች አየ፤
[6]ቀጥሎም የቀጨጩና ከበረሓ በተነሣ የምሥ
ራቅ ነፋስ ተመትተው የሰለቱ ሰባት የእሸት
ዛላዎች በቅለው አየ። [7]ሰባቱም የቀጨጩ የእ
ሸት ዛላዎች፥ ሰባቱን የዳበሩና ያማሩ የእሸት
ዛላዎች ዋጡአቸው፤ ንጉሡም ከእንቅልፉ
በነቃ ጊዜ ሕልም ማየቱን ተገነዘበ። [8]ጠዋት
ከመኝታው ሲነሣ መንፈሱ ታወከ፤ ስለዚህ በማ
ግጽ ምድር ያሉትን እስማተኞችና ጥበበኞች
ሁሉ አስጠርቶ ሕልሙን ነገራቸው፤ ነገር ግን
የሕልሞቹን ትርጕም ለመግለጥ የቻለ አንድ
እንኳ አልነበረም።
[9]በዚህ ጊዜ የወይን ጠጅ አሳላፊው ንጉሡን
እንዲህ አለው፥ "የሠራሁትን በደል ዛሬ አስታ
ውሳለሁ፤ [10]ንጉሥ ሆይ፤ አንተ በእኛና በአን
ጀራ ቤት ጎላፊው ላይ ተቈጥተህ በዘበኞች
አለቃ ቤት እንድንታሰር አድርገህ ነበር፤
[11]በዚያ ሳለን በአንድ ሌሊት ሁለታችንም የተ
ለያየ ሕልም አየን፤ የእያንዳንዳችንም ሕልም
የተለያየ ትርጕም ነበረው። [12]የዘበኞች አለቃ
እኅል ጋይ የነበረ አንድ ወጣት ዕብራዊ ከእኛ
ጋር በእስር ቤት ነበር፤ የእያንዳንዳችንን
ሕልም ለእርሱ ነገርነውና ተረጕመልን።
[13]ሁሉም ነገር እርሱ እንዳለው ሆነ፤ እኔን
ወደ ቀድሞ ማዕርጌ መለሰከኝ፤ የአንጀራ ቤቱን
ጎላፊ ግን በእንጨት ላይ እንዲሰቀል አደረግ
ኸው።"
[14]ስለዚህ ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት
አዘዘ፤ ወዲያውኑ ከእስር ቤት ይዘውት መጡ፤
ጠጕሩን ተላጭቶ ልብሱን ከለወጠ በኋላ ወደ
ንጉሡ ፊት ቀረበ። [15]ንጉሡም ዮሴፍን
"ሕልም አይቼ ነበር፤ ነገር ግን ማንም

ሊተረጕመው አልቻሰም ፤ አንተ ሕልም የመ
ተርጐም ችሎታ እንዳሰህ ሰምቻሰሁ” አሰው ።
16 የሴፍም “ንጉሥ ሆይ! አኔ ሕልም የመ
ተርጐም ችሎታ የሰኝም ፤ ትክክሰኛውን
ትርጕም ሲሰዮህ የሚችል እግዚአብሔር ነው”
አሰ ።
17 ንጉሡም እንዲህ አሰ ፥ “በሕልሜ በዓባይ
ወንዝ ዳር ቆሜ ነበር ፤ 18 ሰባት የወፈሩና የሰቡ
ላሞች ከወንዙ ወጥተው ሣር ሲበሱ አየሁ ፤
19 ቀጥሎም አዋንቶቻቸው እስከሚታይ ድረስ
የከሱ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጡ ፥ እን
ደነርሱ የሚያስከፉ ላሞች በግብጽ ምድር ከቶ
አይቼ አሳውቅም ። 20 የከሱትና አስከፊ የሆኑት
ላሞች በመጀመሪያ የወጡትን ሰባት የወፈሩ
ላሞች ዋጡአቸው ። 21 ከዋጡአቸውም በኋሳ
እንደ ቀድሞው የከሱ ስሰነበሩ ፥ እንደ ዋጡአ
ቸው ማንም ሲያውቅ አይችልም ነበር ፤ በዚህ
ጊዜ እኔ ከእንቅልፌ ነቃሁ ። 22 ደግሞም በሕ
ልሜ በአንድ የእህል አገዳ ላይ ሰባት የዳበሩና
ያማሩ የእሸት ዛላዎች አየሁ ፤ 23 ቀጥሎም የቀ
ጨጨፉና በበረሓ ነፋስ ተመትተው የሰሰቱ ሰባት
የእሸት ዛላዎች ታዩ ። 24 የቀጨጨቱትም ዛላዎች
የሚያምሩትን ዛላዎች ዋጡአቸው ፤ ያየኋቸው
ንም ሕልሞች ስአስማተኞች ነገርሁ ፤ ነገር ግን
ሕልሞቹን ማንም ሲተረጕምልኝ አልቻሰም ።”
25 የሴፍም ፊርዖንን እንዲህ አሰው ፥ “የሁሰ
ቱም ሕልሞችህ ትርጕም አንድ ነው ፤ እግዚአ
ብሔር ወደ ፊት የሚያደርገውን ነገር አስቀድሞ
ገልጦልሃል ፤ 26 ሰባቱ የሚያምሩ ላሞች ሰባት
ዓመታት ናቸው ፤ ሰባቱም ያማሩ የእሸት ዛላ
ዎች ሰባት ዓመታት ናቸው ፤ የሁሰቱም
ትርጕም አንድ ነው ። 27 ከእነርሱም በኋላ የወ
ጡት ሰባት የከሱትና አስከፊዎቹ ላሞች ሰባት
ዓመታት ናቸው ፤ እንዲሁም ሰባቱ የቀጨጩና
በበርሓ ነፋስ ተመትተው የሰሰቱ የእሸት ዛላ
ዎች ሰባት ዓመታት ናቸው ፤ የሁሰቱም
ትርጕም አንድ ነው ፤ ይሄውም ሰባት የረሀብ
ዓመታት ናቸው ። 28 ልከ እንደነገርሁህ ነው ፤
እግዚአብሔር ወደ ፊት የሚያደርገውን ነገር
አስቀድሞ ገልጦልሃል ፤ 29 በመሳው የግብጽ
ምድር ላይ ታሳቅ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት
ዓመታት ይመጣሱ ። 30 ከዚያ በኋሳ ሰባት የረ
ሀብ ዓመታት ይመጣሱ ፤ ረሀብ አገሪቱን በብርቱ
ስስሚጐዳት አነዚያ የጥጋብ ዓመታት ይረሳሱ ።
31 ተከታዩ የረሀብ ዘመን እጅግ አሠቃቂ ስለሚ
ሆን የጥጋብ ጊዜ ፈጽሞ እንዳልነበረ ይሆናል ።
32 ሕልሙን ደጋግመህ ማየትህ የሚያመስክ
ተው ፥ ነገሩ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወሰነና
በቅርብ ጊዜም ውስጥ የሚፈጸም መሆኑን ነው ።
33 “እንግዲህ ጥበብና ማስተዋል ያስውን
ሰው መርጠህ በአገሪቱ አስተዳዳሪ አድርገህ
ሹመው ፤ 34 በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት አንድ
አምስተኛውን ሰብል የሚሰበስቡ ሰዎችን መር
ጠህ ሹም ። 35 እነርሱ በሚመጡት የጥጋብ
ዓመታት ትርፍ የሆነውን ሰብል ሁሉ እንዲሰበ
ስቡ እዘዛቸው ፤ በየከተማውም እህል በጐተራ
እንዲያከማቹና እንዲጠብቁት ሥልጣን ስጣ
ቸው ። 36 ይህም የሚከማቸው እህል በግብጽ
ምድር ላይ ወደፊት በሚመጡት ሰባት የረሀብ
ዓመታት ስአገሪቱ መጠባበቂያ ይሆናል ፤ በዚህ
ሁኔታ አገሪቱ በረሀብ ከመጐዳት ትድናስች ።”

ዮሴፍ በግብጽ ላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ

37 ዕቅዱም ስፈርዖንና ስባሳሟሎቹ ሁሉ
መልካም ሆኖ ታያቸው ፤ 38 ንጉሡም “የእግዚ
አብሔር መንፈስ ካደረበት ከዮሴፍ የተሻስ ሰው
ከቶ አናገኝም” አሳቸው ። 39 ስስዚህ ንጉሡ
ዮሴፍን እንዲህ አለው ፥ “ይህን ሁሉ የገስጠ
ልህ እግዚአብሔር ነው ፤ ከማንኛውም ሰው
ይልቅ አስተዋይና ብልኅ መሆንህ የተረጋገጠ
ነው ፤ 40 ስስዚህ አንተን በአገሬ ላይ አስተዳዳሪ
አድርጌ እሾምሃስሁ ፤ ሕዝቡም ሁሉ ይታዘዝ
ሃል ፤ በሥልጣንም ከአኔ ብቀር የሚበልጥህ
የስም ። 41 እነሆ አሁን በመሳው ግብጽ ምድር
ላይ አስተዳዳሪ አድርጌሃስሁ ።” 42 ንጉሡ የሥ
ልጣኑ ምልክት ያስበትን የማኅተም ቀስበት
ከጣቱ አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገው ፤
ከጥሩ ሐር የተሠራ ልብስ አለበሰው ፤ በአንገ
ቱም የወርቅ ሐብል አደረገስት ። 43 ከንጉሡ
ሁስተኛ ሠረገላ ላይ እንዲቀመጥ አደረገው ፤
የንጉሡም የክብር ዘብ ክፊት ፊት እየሄደ
“እጅ ንሡ! እጅ ንሡ!” ይል ነበር ፤ ዮሴፍ
በግብጽ ምድር ላይ አስተዳዳሪ ሆኖ የተሾመው
በዚህ ዐይነት ነበር ። 44 ንጉሡም “እኔ ንጉሥ
ብሆንም በግብጽ ምድር ሁሉ ላይ ያለ አንተ
ፈቃድ ማንም ሰው እጁን ወይም እግሩን ማንቀ
ሳቀስ አይችልም” አለው ። 45 ፈርዖን ስዮሴፍ
“ጻፍናት ጥዕናሕ” የሚል መጠሪያ ስም አወጣ
ስት ፤ አስናት ተብላ የምትጠራውን የጰጠፌራን
ልጅ በሚስትነት ስጠው ፤ ጰጠፌራ አን ተብሎ
በሚጠራው ከተማ ካህን ነበር ።
46 የሴፍ የግብጽን ንጉሥ ፈርዖንን ማገል
ገል ሲጀምር ዕድሜው ሠሳሳ ዓመት ነበር ፤
የሴፍ ከቤተ መንግሥት ወጥቶ በመሳው የግ
ብጽ ምድር በመዘዋወር ጉብኝት ያደርግ
ነበር ፤ 47 ስሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ምድሪቱ
እጅግ ብዙ ሰብል ስጠች ። 48 በግብጽ አገር በአ
ነዚያ ሰባት የጥጋብ ዓመታት የተገኘውን ስብል
ስብስቦ በየከተሞች አከማች ፤ በየአንዳንዱ
ከተማ ያከማቸው እህል በዙሪያው ከሚገኙት
እርሻዎች የተመረተ ነበር ። 49 በዚህ ዐይነት
የሴፍ ብዛቱ እንደ ባሕር ዳር አሸዋ የሆነ

41:40 ፡- ሐ.ሥ. 7:10 ። 41:42 ፡- ፩ጣ. 5:29 ።

እጅግ ብዙ እህል አከማቸ ፤ እሀሉ እጅግ ብዙ ከመሆኑ የተነሣ እየሰፈረ መጠኑን ለማወቅ የነበረውን ዕቅድ ተወ ።

50 ሰባቱ የረሀብ ዓመታት ከመጀመራቸው በፊት ፥ ዮሴፍ፡ ከጸጠፋራ ልጅ ከእስናት ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ ጸጠፈራ እን ተብሎ በሚጠራው ከተማ ካህን ነበረ ። 51 ዮሴፍ “እግ ዚአብሔር የደረሰብኝን መከራና ዘመዶቼን እን ድረሳ አደረገኝ” በማለት የመጀመሪያ ልጹን ምናሴ ብሎ ጠራው ፤ 52 እንዲሁም “መከራ በተቀበልሁበት ምድር እግዚአብሔር ልጆች ሰጠኝ” በማለት ሁለተኛውን ልጅ ኤፍሬም ብሎ ጠራው ።

53 በግብጽ ምድር ጥጋብ የበዛባቸው ሰባቱ ዓመታት ተፈጸሙ ፤ 54 ዮሴፍ፡ እስቀድሞ እንደ ተናገረው ፥ ሰባቱ የረሀብ ዓመታት መግባት ጀመሩ ፥ በሌሎች አገሮች ሁሉ ረሀብ ሆነ ፥ ይሁን እንጂ በመላው የግብጽ ምድር በቂ ምግብ ነበር ። 55 ረሀቡ በመላው ግብጽ ምድር እየተስፋፋ በሄደ ጊዜ ፥ ሕዝቡ ወደ ፈርዖን ሄደው “ምግብ ስጠን!” ብለው ጮኹ ። ፈርዖ ንም “ወደ ዮሴፍ ሂዱና እርሱ የሚላችሁን አድርጉ” ብሎ አዘዛቸው ።

56 ረሀቡ በመላው ግብጽ እየተስፋፋና እየበ ረታ ስለሄደ ፥ ዮሴፍ ጉተራዎቹ ሁሉ ተከፍ ተው እህሉ ለግብጻውያን እንዲሸጥላቸው አደ ረገ ። 57 በዓለም ላይ ረሀብ ጸንቶ ስለነበር የልዩ ልዩ አገር ሕዝቦች ከዮሴፍ እህል ለመግዛት ወደ ግብጽ አገር መጡ ።

ምዕራፍ 42

የዮሴፍ፡ ወንድሞች ወደ ግብጽ ሄዱ

1 ያዕቆብ በግብጽ እህል መኖሩን ዘለማ ጊዜ ልጆቹን “እርስ በርሳችሁ እየተያያችሁ ከምት ቀመጡ ይልቅ አንድ ነገር አድርጉ ፤ 2 በግብጽ አገር እህል መኖሩን ሰምቼለሁ ፤ ዘረሀብ ከመ ሞታችን በፊት ወደዚያ ሂዱና እህል ግዙልን” አላቸው ። 3 ስለዚህ ዐሥሩ የዮሴፍ፡ ወንድሞች እህል ለመግዛት ወደ ግብጽ ሄዱ ፤ 4 ነገር ግን ያዕቆብ ከዮሴፍ፡ ጋር ከአንድ እናት የወለደውን ልጁን ብንያምን ከወንድሞቹ ጋር ወደ ግብጽ አልላከውም ፤ ምክንያቱም “ጉዳት ይደርስበ ታል” ብሎ ስለፈራ ነው ። 5 በነአንን ምድር ረሀብ በርትቶ ስለነበር የያዕቆብ ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር እህል ለመግዛት ወደ ግብጽ ሄዱ ።

6 ዮሴፍ፡ የግብጽ ምድር አስተዳዳሪ በመሆኑ ከዓለም ዙሪያ ለሚመጡ ሰዎች ሁሉ እህል እን ዲሸጥላቸው ያደርግ ነበር ፤ ስለዚህ የዮሴፍ ወን ድሞች ወደ እርሱ መጡና ግንባራቸው መሬት እስኪነካ ዝቅ ብለው እጅ በመንሣት ሰገዱ ለት ። 7 ዮሴፍ ወንድሞቹን ባያቸው ጊዜ ወዕቃ ቸው ፤ ነገር ግን የማያውቃቸው በመምሰል በቁጣ ቃል “ከየት ነው የመጣችሁት?” ብሎ ጠየቃቸው።

እነርሱም “እህል ለመሸመት ከከነዓን አገር መጣን” አሉት ።

8 ምንም እንኳ ዮሴፍ ወንድሞቹን ያወቃ ቸው ቢሆንም እነርሱ አላወቁትም ነበር ፤ 9 ስለ እነርሱ ያየው ሕልም ሁሉ ትዝ አለውና “እና ንተ ሰላዮች ናችሁ ፤ የመጣችሁትም የአገራች ንን ደካማነት እምን ላይ እንደሆነ ለመሰለል ነው” አላቸው ።

10 እነርሱም “ጌታችን ሆይ! እኛ ሰላዮች አይደለንም ፤ እኛ አገልጋዮችህ እዚህ የመጣ ነው እህል ለመግዛት ነው” አሉት ። 11 “እኛ ሁላችን የአንድ ሰው ልጆች ነን ፤ እኛ የምንታ መን ነን ፤ ሰላዮችም አይደለንም” አሉት ።

12 ዮሴፍም “አይደለም! እናንተ የመጣች ሁት የአገራችንን ደካማነት በምን በኩል እንደ ሆነ ለመሰለል ነው” አላቸው ።

13 እነርሱም “እኛ አገልጋዮችህ ዘከነዓን ምድር የሚኖር የአንድ ሰው ልጆች የሆንን ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን ፤ አንዱ ወንድ ማችን ሞቶአል ፤ የመጨረሻ ታናሽ ወንድማችን አሁን ከአባታችን ጋር ይገኛል” አሉት ።

14 ዮሴፍም እንዲህ አላቸው “ይኸው እኔ እንዳልሁት ያለ ጥርጥር ሰላዮች ናችሁ! 15 እን ግዲህ ታማኝነታችሁ ተፈትኖ የሚረጋገጠው በዚህ ነው ፤ ታናሽ ወንድማችሁ እስከሚመጣ ድረስ እንደማልለቃችሁ በንጉሡ በፈርዖን ስም እምላለሁ ። 16 ከእናንተ አንዱ ሂዶ ወንድማች ሁን ያምጣ ፤ የተናገራችሁት እውነት መሆኑ ተረጋግጦ ነፃ እስክትለቀቁ ድረስ የቀራችሁት እዚሁ በእስር ቤት ትቆያላችሁ ።” 17 ከዚህ በኋላ ሦስት ቀን እስሮ አቆያቸው ።

18 በሦስተኛው ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው ፥ “እኔ እግዚአብሔርን የምፈራ ሰው ስለሆንኹ በአንድ ዘዴ ሕይወታችሁን ለማዳን አስቤአ ለሁ ፤ 19 እናንተ ታማኞች ሰዎች ከሆናችሁ ከእ ናንተ አንዱ እዚህ በእስር ቤት ይቆይ ፤ የቀራ ችሁት እህሉን ይዛችሁ ወደ ተራቡት ዘመዶቻ ችሁ ሂዱ ። 20 ከዚህ በኋላ ታናሽ ወንድማችሁን ይዛችሁልኝ ኑ ፤ በዚህ ዐይነት የተናገራችሁት ሁሉ እውነት መሆኑ ይረጋገጣል ፤ ከመሞትም ትድናላችሁ ።”

እነርሱም በዚህ ነገር ተስማምተው ፥ 21 እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ “በእርግጥ በወንድማችን ላይ ስላደረስነው በደል ተገቢውን ቅጣት በመቀበል ላይ ነን ፤ ምሕረት እንድናደ ርግለት ተጨንቆ ሲለምነን ልመናውን አልተቀ በልንም ነበር ፤ በእኛም ላይ ይህ ጭንቀት ሊደ ርስብን የቻለው በዚህ ምክንያት ነው ።”

41:54 ፡- ሐሥ. 7:11 ። 41:55 ፡- ዮሐ. 2:5 ። 42:2 ፡- ሐሥ. 7:12 ። 42:9 ፡- ዘፍ. 37:5-10 ።

22 ሮቤልም "አኔ እኮ በልጁ ላይ ጕዳት እን
ዳታደርሱ ነግሬአችሁ ነበር ፤ ነገር ግን አልሰማ
ችሁኝም ፤ እነሆ ፥ እርሱን በመግደላችን በቀ
ሉን እየተቀበልን ነው" አላቸው ። 23 ዮሴፍ
እነርሱ የሚሉትን ሁሉ ያዳምጥ ነበር ፤ እነርሱ
ግን ከዮሴፍ ጋር የሚነጋገሩት በአስተርጓሚ ሰለ
ነበር የአነርሱን ንግግር ዮሴፍ እንደሚሰማቸው
አላወቁም ። 24 ዮሴፍ ከእነርሱ ነጠል ብሎ አለ
ቀሰ ፤ እንደጥም ወደ እነርሱ ተመልሶ አነጋገ
ራቸውና ሰምዖንን ከመካከላቸው ወስዶ በፊታ
ቸው አሰረው ።

የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ከነዓን ተመለሱ

25 ዮሴፍ አገልጋዮቹን "ለአነዚህ ሰዎች በየ
ሰልቻዎቻቸው እህል ሙሉላቸው ፤ ገንዘባቸው
ንም መልሳችሁ በየሰልቻዎቻቸው ውስጥ ቋጥሩ
ላቸው ፤ ለጕዞአቸውም ስንቅ አስይዙአቸው"
ብሎ አዘዘ ። ይህም ከተደረገላቸው በኋላ ፥
26 የዮሴፍ ወንድሞች የገዙትን አህል በአህዮቻ
ቸው ጭነው ጕዞ ጀመሩ ።

27 በመንገድ ላይ ሳሉ ለአዳር በሰፈሩበት
ቦታ ከአነርሱ አንዱ ለአህያው ጥሬ ለመስጠት
ሰልቻውን በፈታ ጊዜ በሰልቻው አፍ ላይ ገን
ዘቡ ተቋጥሮ አገኘው ። 28 እርሱም ለወንድሞቹ
"ገንዘቤ ተመልሶልኛል ፤ ይሄው በሰልቻዬ
ውስጥ አገኘሁት" ብሎ ነገራቸው ። ሁሉም
በፍርሃት ልባቸው ቀልጦ "እግዚአብሔር ያደረ
ገብን ይህ ነገር ምንድን ነው?" ተባባሉ ።

29 በከነዓን ወዳለው ወደ አባታቸው ወደ ያዕ
ቆብ ተመለሱ ፤ የደረሰባቸውን ሁሉ እንዲህ
ብለው ነገሩት ፤ 30 "የግብጽ አገር አስተዳዳሪ
'አገሬን ልትሰልሉ የመጣችሁ ናችሁ' በማለት
በቁጣ ቃል ተናገረን ፤ 31 እኛም 'ታማኞች
ሰዎች ነን እንጂ ሰላዮች አይደለንም ፤ 32 እኛ
የአንድ ሰው ልጆች የሆንን ዐሥራ ሁለት ወንድ
ማማቾች ነን ፤ አንዱ ሞቶአል ፤ የመጨረሻ
ታናሽ ወንድማችን በከነዓን ከአባታችን ጋር
አለ' አልነው ። 33 ሰውየውም እንዲህ አለን ፥
'ታማኞች ሰዎች መሆናችሁን የማውቀው ይህን
አንድ ነገር ብታደርጉ ነው ፤ ይሄውም ከእናንተ
አንዱ ከእኔ ጋር ይቆይ ፤ ሌሎቻችሁ ለተራቡት
ቤተሰቦቻችሁ እህል ይዛችሁ ወደ አገራችሁ
ተመለሱ ፤ 34 ታናሽ ወንድማችሁንም ይዛችሁ
ልኝ ኑ ፤ በዚህ ዐይነት ታማኞች ሰዎች መሆና
ችሁንና ሰላዮችም አለመሆናችሁን አረጋግጣ
ለሁ ፤ ወንድማችሁንም መልሼ አሰጣችኋለሁ ፤
በዚህም አገር እንደፈለጋችሁ መነገድ ትችላላ
ችሁ ።'"

35 ከዚህ በኋላ እህላቸውን ከሰልቻዎቻቸው
ባራገፉ ጊዜ በየሰልቻዎቻቸው ውስጥ ገንዘባቸ
ውን እንደተቋጠረ አገኙ ፤ እነርሱና አባታቸው
የተመለሰውን ገንዘብ ባዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ ።
36 በዚህ ጊዜ አባታቸው "ልጆቼን ሁሉ እን
ዳጣ ትፈልጋላችሁን? ዮሴፍ የለም ፤ ስምዖንም
የለም ፤ አሁን ደግሞ ብንያምን ለመውሰድ ትፈ
ልጋላችሁ ፤ በዚህ ሁሉ መከራ የምሠቃየው አኔ
ነኝ" አለ ።

37 ሮቤል አባቱን እንዲህ አለው ፥ "ብንያ
ምን ወደ አንተ መልሼ ባላመጣው ሁለቱን ወን
ዶች ልጆቼን ወስደህ ግደላቸው ፤ ስለዚህ በአኔ
ኀላፊነት ላከው ፤ አኔም መልሼ አመጣዋ
ለሁ ።"

38 ያዕቆብም "ምንም ቢሆን ከእናንተ ጋር
አይሄድም ፤ ወንድሙ ሞቶአል ፤ የቀረው እርሱ
ብቻ ነው ፤ በመንገድ አንድ ጕዳት ቢደርሰበት
በእርጅናዬ ዘመን በመሪር ሐዘን ወደ መቃብር
እንድወርድ ታደርጉኛላችሁ" አላቸው ።

ምዕራፍ 43

የዮሴፍ ወንድሞች ብንያምን ይዘው
እንደገና ወደ ግብጽ ሄዱ

1 በከነዓን ምድር ረዘቡ እጅግ አየበረታ
ሄደ ፤ 2 የያዕቆብ ቤተሰብ ከግብጽ የመጣውን
እህል ተመግበው በጨረሱ ጊዜ አባታቸው
"እንደገና ወደ ግብጽ ሂዱና ጥቂት እህል ሸም
ቱልን" አላቸው ።

3 ይሁዳ ግን ለአባቱ እንዲህ ብሎ መለሰ
ለት ፥ "ሰውየው 'ወንድማችሁን ይዛችሁ ካል
መጣችሁ እፊቴ አንዳትቀርቡ' በማለት በብርቱ
አስጠንቅቆናል ፤ 4 ስለዚህ ወንድማችንን ይዘን
እንድንሄድ ከፈቀድክልን ሄደን እህል በመሸ
መት ትእዛዝህን እንፈጽማለን ። 5 ይህን የማትፈ
ቅድልን ከሆነ ግን ወደዚያ አንሄድም ፤ ምክንያ
ቱም 'ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ
እፊቴ አንዳትቀርቡ' ብሎናል ።"

6 ያዕቆብም "'ሌላ ወንድም አለን' ብላችሁ
ለሰውየው በመናገር ለምን ይህን ያህል መከራ
አመጣችሁብኝ?" አለ ።

7 እነርሱም "ሰውየው ስለ ራሳችንና ስለ
ቤተሰባችን አጥብቆ መረመረን ፤ 'አባታችሁ
በሕይወት አለን? ሌላስ ወንድም አላችሁን?'
ብሎ ጠየቀን ፤ እኛም ለጥያቄው ተገቢውን
መልስ ሰጠን ፤ ስለዚህ ሰውየው 'ወንድማችሁን
ይዛችሁ እንድትመጡ' እንደሚለን እንዴት
ልናውቅ እንችል ነበር?"

8 ይሁዳም አባቱን እንዲህ አለ ፥ "ልጁን
በእኔ ኀላፊነት አብሮን እንዲሄድ አድርግ ፥ ሳን
ዘገይ አሁኑኑ ጕዞ እንጀምር ፤ ይህ ከሆነ ፥
እኛም አንተም ልጆቻችንም ሁሉ በረሀብ ከመ
ሞት እንድናለን ። 9 ልጁን በእኔ ዋስትና

42፡22 ፦ ዘፍ. 37፡21-22 ።

ስጠኝ ፥ ስለእርሱ እኔ ተጠያቂ እሆናለሁ ፥ በደ
ጎና ወደ እንተ መልሼ ባላመጣው በሕይወቴ
ዘመን የተረገምሁ ልሁን ። 10 ይህን ያህል ባንዘ
ገይ ኖሮ እስከ አሁን ሁለት ጊዜ እዚያ ደርሰን
መመለስ በቻልን ነበር ።”

11 አባታቸው ያዕቆብም እንዲህ አላቸው ፥
“እንግዲህ መሄዳችሁ የማይቀር ከሆነ ለአገሪቱ
ገጸ በረከት የሚሆን ምድራችን ከምታፈራው
ምርጥ ነገር ሁሉ በስልቻዎቻችሁ ጨምራችሁ
ሂዱ ፥ ይኸውም በለሳን ፥ ማር ፥ ቅመማ
ቅመም ፥ ከርቤ ፥ ተምርና ለውዝ ይዛችሁ
ሂዱ ። 12 ከዚህ በፊት በየስልቻዎቻችሁ ሜዳ
ተመልሶ የነበረው ገንዘብ በስሕተት ሊሆን ስለ
ሚችል እጥፍ ገንዘብ ይዛችሁ ሂዱ ። 13 ወንድ
ማችሁን ይዛችሁ ወደ ሰውየው ቦታሎ ሂዱ ።
14 ብንያምንና ሌላውንም ወንድማችሁን መልሶ
እንዲሰጣችሁ ሁሉን የሚችል አምላክ የዚያን
ሰው ልብ ያራራላችሁ ። እኔ በበኩሌ ልጆቼን
ካጣሁ ፥ ባዶ እጄን መቅረቴ ነው ።”

15 ስለዚህ ወንድማማቾቹ ገጸ በረከቱንና
እጥፍ ገንዘብ ይዘው ከብንያም ጋር ወድ ግብጽ
ለመሄድ ጉዞ ጀመሩ ፥ እዚያም በደረሱ ጊዜ
ዮሴፍ ፊት ቀረቡ ። 16 ዮሴፍ ብንያምን ከእነ
ርሱ ጋር ባየው ጊዜ የቤቱን አዛዥ ጠራውና
“እነዚህን ሰዎች ወደ ቤት ውሰዳቸው ፥ ዛሬ
ቀን ከእኔ ጋር ምሳ ስለሚበሉ አንድ ከብት ዕረ
ድና አዘጋጅ” አለው ።

17 አዛዡም ዮሴፍ በነገረው መሠረት ሰዎ
ቹን ወስዶ ወደ ቤት አስገባቸው ። 18 ሰዎቹም
ወደ ዮሴፍ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ አጅግ ፈሩ ፥
ምክንያቱም “ወደዚህ ያመጡን በመጀመሪያ
ጊዜ በስልቻዎቻችን ውስጥ ተመልሶ ስለተገ
ኘው ገንዘብ ሳይሆን አይቀርም ፥ በዚህ ምክን
ያት ያሠቃዩናል ፥ አህዮቻችንን ወስደው እኛ
ንም የአነርሱ ባሪያዎች ያደርጉናል” ብለው
ስላሰቡ ነው ።

19 ስለዚህ ወደ ቤቱ በር አጠገብ ሲደርሱ
የቤቱን አዛዥ እንዲህ አሉት ፥ 20 “ጌታዬ ከዚህ
በፊት አህል ለመሸመት ወደዚህ መጥተን
ነበር ፥ 21 ስንመለስ በመንገድ ለአዳር በሰፈርን
በት ቦታ ስልቻዎቻችንን ስንፈታ የያንዳንዳች
ንን ገንዘብ ምንም ሳይጐድልለት በየስልቻዎቻ
ችን አፍ ላይ ተቋጥሮ አገኘነው ። እነሆ ፥ ያንን
ገንዘብ መልሰን አምጥተናል ። 22 አሁን አህል
የምንሸምትበትንም ገንዘብ በተጨማሪ ይዘናል ፥
ከዚያን ጊዜ ገንዘባችንን መልሶ በየስልቻዎቻ
ችን ማን እንደከተተው እናውቅም ።”

23 የቤቱም አዛዥ “በዚህ ጉዳይ ጭንቀትና
ፍርሃት አይድረስባችሁ ፥ የአናንተና የአባታችሁ
አምላክ ይህን ገንዘብ በየስልቻዎቻችሁ አስቀም
ጦላችሁ ይሆናል ፥ የአናንተን ገንዘብ ግን እኔ
ተቀብዬአለሁ” አላቸው ። ከዚህ በኋላ ስምዖንን
ወደ እነርሱ አመጣው ።

24 የቤቱ አዛዥ ወንድማማቾቹን ወደ ዮሴፍ
ቤት አስገባቸውና እግራቸውን የሚታጠቡበት
ውሃ ሰጣቸው ፥ ለአህዮቻቸውም ገፈራ ሰጣ
ቸው ። 25 ከዮሴፍ ጋር ምሳ እንደሚበሉ ተነግ
ሮአቸው ስለነበር ፥ ዮሴፍ በምሳ ሰዓት እስከሚ
መጣ ድረስ ለእርሱ የሚያቀርቡለትን ስጦታ
አዘጋጁ ።

26 ዮሴፍ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ፥ እርሱ መዳለ
በት ክፍል ገብተው ያመጡትን ስጦታ አበረከቱ
ለት ፥ ወደ መሬት ዝቅ ብለውም በመስገድ
እጅ ነሡት ። 27 እርሱም ስለ ደኅንነታቸው
ከጠየቃቸው በኋላ “ያ የነገራችሁኝ ሽማግሌ
አባታችሁ እንዴት ነው ? አሁንም በሕይወት
አለን ?” አላቸው ።

28 እነርሱም “እግልጋያብ አባታችን በሕይ
ወት አለ ፥ ጤንነቱም የተሟላ ነው” አሉት ።
ወደ መሬት ዝቅ ብለውም በመስገድ እጅ
ነሡት ።

29 ዮሴፍ የእናቱ ልጅ የሆነውን ወንድሙን
ብንያምን ባየው ጊዜ “‘ታናሽ ወንድም አለን’
ብላችሁ ነግራችሁኝ ነበር ፥ ይህ እርሱ
ነውን ?” አለና “ልጄ ፥ እግዚአብሔር ይባር
ክህ” አለው ። 30 ዮሴፍ ወንድሙን በማየቱ
ስሜቱ ስለተነካ ከዚያ ተነሥቶ ሄደ ፥ ወደ አል
ፍኾም ገብቶ ምርር ብሎ አለቀሰ ።

31 ፊቱንም ከታጠበ በኋላ ወጣ ፥ ራሱንም
በመቈጣጠር ምሳ እንዲቀርብ አዘዘ ።

32 ለዮሴፍ ብቻውን አንድ ገበታ ፥ ለወንድማ
ማቾቹ ሌላ ገበታ ፥ እዚያ ይመገቡ ለነበሩ ግብ
ጻውያንም ሌላ ገበታ ተዘጋጀ ፥ ምክንያቱም
ግብጻውያን ከዕብራውያን ጋር አብሮ መመገብን
እንደ ጸያፍ ይቈጥሩት ስለነበር ነው ። 33 ወንድ
ማማቾቹ ከታላቁ እንሥቶ እስከ ታናሹ በዕድሜ
ተራ በዮሴፍ ፊት ለፊት ተቀመጡ ፥ እንዴት
እንደተቀመጡ ባዩ ጊዜ በመደነቅ እርስ በርሳ
ቸው ተያዩ ። 34 ለዮሴፍ ከተቀረበለት ምግብ እየ
ተወሰደ ይሰጣቸው ነበር ፥ ለብንያም ግን ከሌ
ሎቹ እምስት እጥፍ ተሰጠው ፥ በዚህ ሀይነት
ከዮሴፍ ጋር አስኪጠግቡ በልተው ጠጥተው
ተደሰቱ ።

ምዕራፍ 44

ጠፉ የተባለው ዋንጫ በብንያም ስልቻ ውስጥ ተገኘ

1 ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ እንዲህ ብሎ አዘ
ዘው ፥ “ለመጫን የሚችሉትን ያህል በየስልቻ
ዎቻቸው ሙላላቸው ፥ የአያንዳንዱንም ገንዘብ
በየስልቻው አፍ አስቀምጠው ። 2 የእኔን የብር
ዋንጫ ውሰድና በታናሽ ወንድማቸው ስልቻ
ውስጥ አህል ለመሸመት ከመጣው ገንዘብ ጋር
ከተተው ።” የቤቱም አዛዥ ዮሴፍ እንደነገረው
አደረገ ።

[3]ጠዋት በማለዳ ወንድማማቾቹ አህዮቻቸውን ይዘው እንዲሄዱ ተደረገ። [4]ከከተማው ወጥተው ገና ጥቂት መንገድ ርቀው እንደ ሄዱ፥ ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ እንዲህ አለው፥ “እነዚያን ሰዎች ተከታትለህ ያዛቸው፤ ወደ እነርሱም ስትደርስ ‘በመልካም ፈንታ ከፋ የመለሳችሁት ስለምንድን ነው፤ [5]የጌታዬን የብር ዋንጫ የሰረቃችሁት ለምንድን ነው? ዋንጫው ጌታዬ የሚጠጣበትና ሁሉን ነገር መርምሮ የሚያውቅበት እንደሆነ አታውቁምን? ይህ ያደረጋችሁት በደል እጅግ ከባድ ነው’ ብለህ ንገራቸው።”

[6]የቤቱም አዛዥ ወደ ሰዎቹ እንደ ደረሰ ልክ እንደተባለው ነገራቸው፤ [7]እነርሱም እንዲህ በማለት መልስ ሰጡት፥ “ጌታችን ሆይ! እንዲት እንዲህ ትናገራለህ? እኛ ይህን የመሰለ ነገር እንዳላደረግን በመሐላ እናረጋግጣለን፤ [8]ከአሁን ቀደም በየስልቻችን ያገኘነውን ገንዘብ እንኳ ከከነዓን መልሰን እንዳመጣንልህ ታውቃለህ፤ ታዲያ አሁን ከጌታህ ቤት ብርም ሆነ ወርቅ የምንሰርቀው ለምንድን ነው? [9]ከእኛ አንዱ ይህን ዕቃ ይዞ ቢገኝ በሞት ይቀጣ፤ የተ ረነውም የአንተ ባሪያዎች እንሁን።”

[10]እርሱም “መልካም ነው፤ እናንተ ባላችሁት አስማማለሁ፤ ሆኖም ዋንጫውን የወሰ ደው ሰው ብቻ የእኔ ባሪያ ይሆናል፤ የቀራች ሁት ግን በነፃ ልትሄዱ ትችላላችሁ” አላ ቸው። [11]ስለዚህ በፍጥነት ስልቻዎቻቸውን አወረዱ፤ እያንዳንዱም የራሱን ስልቻ ከፈተ። [12]የዮሴፍ አገልጋይ ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ የሁሉንም ስልቻ በተራ በመበርበር ዋንጫውን በጥንቃቄ ፈለገ፤ በመጨረሻ ግን ዋንጫው በብንያም ስልቻ ውስጥ ተገኘ። [13]ወንድማማቾቹ ይህን ባዩ ጊዜ በሐዘን ልብ ሰቻቸውን ቀደዱ፤ ስልቻዎቻቸውንም ጭነው ወደ ከተማ ተመለሱ።

[14]ይሁዳና ወንድሞቹ ወደ ዮሴፍ ሲመጡ ገና በቤት ሳለ አገኙት፤ ወደ መሬት ጐንበስ ብለው በመሰገድ እጅ ነሡት፤ [15]ዮሴፍም “ይህ ያደረጋችሁት ነገር ምንድን ነው? እኔ ባለሁበት ደረጃ የሚገኝ ሰው በተለየ ጥበብ ሁሉን ነገር መርምሮ ማወቅ የማይችል መሰላች ሁን?”

[16]ይሁዳም “እንግዲህ ለጌታችን ምን መልስ እንሰጣለን? ራሳችንን ነፃ የምናደርግበት መልስ መስጠት ከቶ አንችልም፤ ምክንያቱም እግዚአ ብሔር የሠራነውን በደል ገልጦታል፤ እንግዲህ ዋንጫው የተገኘበት ሰው ብቻ ሳይሆን ሁላች ንም ባሪያዎችህ እንሁን” አለ።

[17]ዮሴፍም “ይህንን ከቶ አላደርገውም፤ ዋንጫው የተገኘበት ሰው ብቻ የእኔ ባሪያ መሆን አለበት፤ ሌሎቻችሁ በሰላም ወደ አባታ ችሁ መመለስ ትችላላችሁ” አለ።

ይሁዳ ስለ ብንያም ዮሴፍን ለመነ

[18]ይሁዳ ወደ ዮሴፍ ቀርቦ እንዲህ አለ፥ “ጌታዬ ሆይ! አባክህ አንድ ቃል እንድናገር ፍቀድልኝ፤ ምንም እንኳ የፈርዖንን ያህል የተ ከበርክ ብትሆንም እባክህ አትቈጣኝ። [19]ጌታዬ ከእሁን ቀደም ‘አባት አላችሁ ወይ? ሌላ ወን ድምስ አላችሁ ወይ?’ ብለህ ጠየቅኸን፤ [20]እኛም ‘ሽማግሌ አባት አለን፤ በስተርጅና የወለደውም ታናሽ ወንድም አለን፤ የልጁ ወን ድም ሞቶአል፤ ከእናቱ ልጆች የቀረው እርሱ ብቻ ስለሆነ አባቱ በጣም ይወደዋል’ ብለንህ ነበር፤ [21]እንተም ‘አየው ዘንድ ይዛችሁልኝ እንድትመጡ’ አልከን፤ [22]እኛም ‘ልጁ አባቱን ትቶ መምጣት አይችልም፤ ትቶ ከመጣ ግን አባትየው መሞቱ የማይቀር ነው’ ብለንህ ነበር። [23]አንተም ‘ታናሽ ወንድማችሁን ይዛ ችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ በፊቴ አትቀር ቡም’ ብለህ በብርቱ አስጠነቀቅኸን።

[24]“እኛም ወደ አባታችን ቡተመለስን ጊዜ ያልከንን ሁሉ ነገርነው፤ [25]ከዚህ በኋላ እርሱ ‘አሁንም ወደ ግብጽ ተመለሱና ጥቂት እህል ሸምቱልን’ አለን። [26]እኛም ‘ወደዚያ መሄድ እንችልም፤ ምክንያቱም ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር ካልሆነ በስውየው ፊት መቅረብ አን ችልም፤ ስለዚህ ወደዚያ መሄድ የምንችለው ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር የሄደ እንደሆነ ብቻ ነው’ አልነው። [27]አባታችንም እንዲህ አለን፥ ‘ሚስቴ ራሔል ሁለት ወንዶች ልጆች ብቻ እንደወለደችልኝ ታውቃላችሁ። [28]ከእነ ርሱ አንዱ ከአሁን በፊት ተለይቶኛል፤ ከተለ የኝ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ስላላየሁት ከፋ አውሬ በልቶት ይሆናል፤ [29]አሁን ደግሞ ይህ ንን መለዳችሁ በእርሱ ላይ አደጋ ቢደርስበት በእርጅናዬ ዘመን የምታመጡብኝ ሐዘን ወደ ሞት ያደርሰኛል።’”

[30-31]ቀጥሎም ይሁዳ “ስለዚህ ጌታዬ! ልጁን ሳንይዝ ወደ አባታችን ብንመለስ፥ ልጁ ከእኛ ጋር አለመኖሩን ሲያይ ወዲያውኑ ይሞ ታል፤ ምክንያቱም የእርሱ ሕይወት ከልጁ ሕይወት ጋር የተሳሰረ ስለሆነና እጅግ ከማር ጀቱ የተነሣ የሚገጥመው ሐዘን ወደ ሞት ያደ ርሰዋል። [32]ከዚህም በላይ ስለልጁ ደኅንነት ራሴን ዋስ አድርጌ ለአባቴ ሰጥቼአለሁ፤ ደግ ሞም ‘ልጁን በደኅና መልሼ ባላመጣው በሕይ ወቴ ዘመን ሁሉ የተረገምሁ ልሁን’ ብዬ ቃል ገብቼለታለሁ።

[33]“ስለዚህ እኔ በልጁ ፈንታ የአንተ የጌታዬ ባሪያ ሆኜ እዚሁ ልቅር፤ ልጁ ግን ከወንድሞቹ ጋር ይመለስ፤ [34]ልጁን ሳልይዝ እንዴት ወደ አባቴ መመለስ እችላለሁ? ይህን የመሰለ ከባድ ሥቃይ በአባቴ ላይ ሲደርስ ማየት አልች ልም።”

ምዕራፍ 45

ዮሴፍ ማንነቱን ለወንድሞቹ ገለጠ

1 ዮሴፍ የናፋቆት ስሜቱን በአገልጋዮቹ
ፊት መቋጣጠር ባለመቻሉ “ሁላችሁም ከዚህ
ውጡ!” ብሎ አዘዘ፤ ስለዚህ ዮሴፍ ማንነቱን
ለወንድሞቹ በገለጠ ጊዜ ማንም የውጭ ሰው
በአጠገቡ አልነበረም። 2 በዚህ ጊዜ ግብጻውያን
እስኪሰሙት ድረስ ድምፁን ከፍ አድርጎ አለ
ቀሰ፤ የፈርዖንም ቤተሰብ ወሬውን ሰማ።
3 ዮሴፍ፦ ወንድሞቹን “እኔ ዮሴፍ ነኝ፤
አባቴ እስከ አሁን በሕይወት አለን?” አላ
ቸው። ወንድሞቹ የተናገረውን በሰሙ ጊዜ
እጅግ ደነገጡ፤ መልስ መስጠትም ተሳናቸው።
4 በዚህ ጊዜ ዮሴፍ፦ “እስቲ ወደ እኔ ቀረብ
በሉ” አላቸው፤ ከቀረቡም በኋላ እንዲህ አላ
ቸው፦ “እኔ ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ ወንድማ
ችሁ ዮሴፍ ነኝ፤ 5 ነገር ግን ይህን በማድረጋ
ችሁ በመጸጸት አትበሳጩ፤ ምክንያቱም እግዚ
አብሔር እኔን እስቀድሞ የላከኝ የሰዎችን ሕይ
ወት እንዳተርፍ ነው። 6 በምድር ላይ ረሀብ
ከገባ ሁለተኛ ዓመቱን ይዞአል፤ ሰዎች አርሰው
መከር መሰብሰብ የማይችሉባቸው አምስት ዓመ
ታት ገና ይመጣሉ። 7 እግዚአብሔር አስቀድሞ
ወደዚህ የላከኝ በዚህ በአስደናቂ ዘዴ የአናንተን
ሕይወት በማዳን በምድር ላይ ዘር እንዲቀርላ
ችሁ አስቦ ነው።
8 “ስለዚህ ወደዚህ የላከኝ ራሱ እግዚአብ
ሔር እንጂ እናንተ አይደላችሁም፤ እግዚአብ
ሔር ለፈርዖን እንደ መካሪ አባት፥ በቤት ንብ
ረቱ ላይ ጌታና የመላው ግብጽ አገር ገዥ አደረ
ገኝ። 9 አሁን በፍጥነት ተመልሳችሁ ወደ
አባቴ ሂዱና ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ይልሃል
በሉት፥ ‘እግዚአብሔር የመላው ግብጽ ገዥ
አድርጎኛል፤ ስለዚህ ሳትዘገይ ወደ እኔ ና፤
10 ልጆችህን፥ የልጅ ልጆችህን፥ በጎችህን፥
ፍየሎችህን፥ ከብቶችህን ሌላም ያለህን ነገር
ሁሉ ይዘህ ና፥ በአኔው አቅራቢያ በሚገኘው
በጌሤም ምድር ትኖራለህ። 11 አምስት የረሀብ
ዓመታት ገና ስለሚቀሩ እንተና ቤተሰብህ እንስ
ሳትህም ሞምር ረሀብ እንዳይደርስባችሁ በጌ
ሤም አመግብሃለሁ።’”
12 ቀጥሎም ዮሴፍ እንዲህ አለ፥ “አሁን
የምናገራችሁ እኔ ዮሴፍ መሆኔን እናንተና እን
ተም ወንድሜ ብንያም አይታችሁ ለማረጋገጥ
ችላችኋል፤ 13 በግብጽ አገር ያለኝን ታላቅ ክብ
ርና ያያችሁትንም ሁሉ ለአባቴ ንገሩት፤ በፍጥ
ነትም ወደዚህ አምጡት።”
14 ከዚህ በኋላ የወንድሙን የብንያምን አን
ገት አቅፎ አለቀሰ፤ ብንያምም ወንድሙን
አቅፎ አለቀሰ፤ 15 ዮሴፍ የቀሩትንም ወንድሞ
ቹን አንድ ባንድ እየሳመ አለቀሰ፤ ከዚህ በኋላ
ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መነጋገር ጀመሩ።
16 የዮሴፍ ወንድሞች መምጣት በፈርዖን
ቤተ መንግሥት በተሰማ ጊዜ ፈርዖንና ባለሥል
ጣኖቹ ደስ አላቸው፤ 17 ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ
አሰው፥ “ወንድሞችህ አህዮቻቸውን ጭነው
ወደ ከነዓን እንዲመለሱ ንገራቸው፤ 18 አባታቸ
ውንና ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ይምጡ፤ እኔም
በግብጽ አገር ለም የሆነውን ቦታ መርጬ እስ
ጣቸዋለሁ፤ በቂ ምግብ አግኝተው በደስታ
መኖር ይችላሉ። 19 እንዲሁም ሚስቶቻቸውን፥
ልጆቻቸውንና አባታቸውን አሳፍረው የሚያመ
ጡበት ከግብጽ አገር ሠረገላዎችን ይዘው እንዲ
ሄዱ አዘዛቸው። 20 በግብጽ ምድር ለም የሆነ
ውን ቦታ ስለሚያገኙ ቤት ንብረታቸውን
ትተው በመምጣታቸው ቅር አይሰኙ።”
21 የያዕቆብ ልጆች ልክ እንደተነገራቸው
አደረጉ፤ ዮሴፍም በንጉሡ ትእዛዝ መሠረት
ሠረገላዎችንና ሰንዞዞ የሚሆናቸውን ስንቅ ሰጣ
ቸው፤ 22 ለአያንዳንዳቸውም አንድ አንድ የክት
ልብስ ሰጣቸው፤ ለብንያም ግን አምስት የክት
ልብስና ሦስት መቶ ብር ሰጠው። 23 ለአባቱም
በዐሥር አህዮች የተጫነ ከግብጽ ምድር የሚገ
ኘውን መልካም ነገር ሁሉ ላከለት፤ እንዲሁም
በሚመጣበት ጊዜ ለስንቅ የሚሆነው በሌሎች
ዐሥር እንስት አህዮች የተጫነ እህል፥ ዳቦና
ሌላም ምግብ ላከለት። 24 በዚህ ሁኔታ ወንድሞ
ቹን ካሰናበታቸው በኋላ “በመንገድ አትጣሉ”
ብሎ መከራቸው።
25 የዮሴፍ ወንድሞች ከግብጽ ተነሥተው
በከነዓን ወደሚኖረው አባታቸው ወደ ያዕቆብ
ተመለሱ። 26 እዚያም እንደደረሱ አባታቸውን
“ዮሴፍ በሕይወት አለ፤ እንዲያውም በመላው
ግብጽ ላይ አስተዳዳሪ ሆኖአል” አሉት። ያዕ
ቆብ ግን አጅግ ደነገጠ፤ ሊያምናቸውም አልቻ
ለም።
27 ነገር ግን ዮሴፍ፦ ያላቸውን ሁሉ በነገሩት
ጊዜና እርሱን ወደ ግብጽ የሚወስዱበትን
ዮሴፍ የላከለትን ሠረገላ ባየ ጊዜ ሕይወቱ በደ
ስታ ታደሰ፤ 28 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ “ልጄ
ዮሴፍ በሕይወት መኖሩን ካረጋገጥሁ ከመሞቴ
በፊት ሄጄ አየዋለሁ” አለ።

ምዕራፍ 46

ያዕቆብ ከነቤተሰቡ ወደ ግብጽ ሄደ

1 ያዕቆብ ጓዙን ሁሉ ይዞ ተነሣ፤ ቤርሳቤ
ሀም በደረሰ ጊዜ ለአባቱ ለይስሐቅ አምላክ
መሥዋዕት አቀረበ።
2 እግዚአብሔር፥ ሌሊት በራእይ ተገለጠለ
ትና “ያዕቆብ! ያዕቆብ!” ብሎ ጠራው።

45:1 ፦ ሐሥ. 7:13። 45:9-11 ፦ ሐሥ. 7:14።

እርሱም "አቤት ጌታ ሆይ! እነሆ አለሁ" አለ።
3 እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፥ "እኔ የአባትህ እምላክ፥ እግዚአብሔር ነኝ፤ ወደ ግብጽ ለመሄድ አትፍራ፤ እኔ ዘርህን በግብጽ እገር ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ፤ 4 እኔ ወደ ግብጽ አብሬህ እሄዳለሁ፤ ዘርህንም ወደዚህ ምድር መልሼ አመጣለሁ፤ በምትሞትበትም ጊዜ ዮሴፍ ከአጠገብህ ይገኛል።"
5 ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ወደ ግብጽ ጕዞ ጀመረ፤ ልጆቹም አባታቸውን ያዕቆብን፥ ሕፃናት ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን የግብጽ ንጉሥ በላካቸው ሠረገላዎች አሳፍረው፤ 6 ከብቶቻቸውንና በከነዓን ያፈሩትን ሀብት ሁሉ ይዘው ወደ ግብጽ ሄዱ፤ በዚህ ዐይነት ያዕቆብ ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ወደ ግብጽ ሄደ፤ 7 አብረው የሄዱትም ወንዶች ልጆቹ፥ ሴቶች ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ናቸው።
8 ከእስራኤል ጋር ወደ ግብጽ የወረዱት የእስራኤላውያን ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው፤
የያዕቆብ የመጀመሪያ ልጅ ሮቤል፥
9 የሮቤል ልጆች፦ ሔኖክ፥ ፋሉ፥
ሔጽሮንና ካርሚ ናቸው።
10 የስምዖን ልጆች፦ ይሙኤል፥ ያሚን፥
ኦሃድ፥ ያኪን፥ ጾሐርና
ከከነዓናዊቲቱ ሴት የተወለደው
ሻኡል ናቸው።
11 የሌዊ ልጆች፦ ጌርሾን፥ ቀሃትና መራሪ
ናቸው።
12 የይሁዳ ልጆች፦ ዔር፥ አናን፥ ሼላ፥
ፋሬስና ዛራሕ ናቸው፤ ዔርና አናን
ግን በከነዓን ምድር ሞተዋል።
የፋሬስ ልጆች ሔጽሮንና ሐሙል
ናቸው።
13 የይሳኮር ልጆች፦ ቶላዕ፥ ፉዋ፥ ያሹብና
ሺምሮን ናቸው።
14 የዛብሎን ልጆች፦ ሴሬድ፥ ኤሎንና
ያሕልኤል ናቸው።
15 እነዚህ ወንዶች ልጆችና ሴቷም ልጅ ዲና በመስጴጦምያ ሳሉ ልያ ለያዕቆብ የወለደቻት ናቸው። ያዕቆብ ከልያ ያፈራቸው ልጆችና የልጅ ልጆች ሠላሳ ሦስት ናቸው።
16 የጋድ ልጆች፦ ጸፎን፥ ሐጊ፥ ሹኒ፥
ኤጽቦን፥ ዔሪ፥ አሮድና እርኤሊ
ናቸው።
17 የአሴር ልጆች፦ ይምና፥ ይሽዋ፥
ይሽዊና በሪዓ ናቸው። እኅታቸው
ሤራሕ ትባላለች።
የበሪዓ ልጆች ዶማ ሐቤርና
ማልኪኤል ናቸው።
18 እነዚህ ዐሥራ ስድስቱ ላባ ለልጁ ለልያ
በሞግዚትነት ከሰጣት ከዚልፋ
የተወለዱ የያዕቆብ ልጆችና የልጅ
ልጆች ናቸው።
19 ያዕቆብ ከራሔል የወለዳቸው ዮሴፍና
ብንያም ናቸው።
20 የዮሴፍ ልጆች ምናሴና ኤፍሬም
ናቸው፤ እንርሱም ዮሴፍ በግብጽ
ምድር ከአን
ከተማ ካህን ከጰጥፌራ ሴት ልጅ
ከአሰናት የወለዳቸው ናቸው።
21 የብንያም ልጆች፦ ቤላዕ፥ ቤኬር፥
አሽቤል፥ ጌራ፥ ናዕማን፥ ኤሒ፥
ሮሽ፥ ሙፊም፥
ሑፊምና አረድ ናቸው።
22 እነዚህ ዐሥራ አራቱ ያዕቆብ ከራሔል
የወለዳቸው ልጆችና የልጅ ልጆች
ናቸው።
23 የዳን ልጅ ሑሺም ነው።
24 የንፍታሌም ልጆች፦ ያሕጽኤል፥ ጉኒ፥
ዬጼርና ሺሌም ናቸው።
25 እነዚህ ሰባቱ ላባ ለልጁ ለራሔል ከሰጣት
ከባላ የተወለዱ የያዕቆብ ልጆችና
የልጅ ልጆች ናቸው።
26 ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ የሄዱት
የያዕቆብ ዝርያዎች ስልሳ ስድስት
ናቸው፤
ይህም የልጆቹን ሚስቶች ቍጥር
ሳይጨምር ነው።
27 ለዮሴፍ በግብጽ ከተወለዱት ከሁለቱ
ወንዶች ልጆች ጋር፥ ከያዕቆብ
ጋር ወደ ግብጽ የገቡት የያዕቆብ
ዝርያዎች ቍጥር በአጠቃላይ ሰባ
ነበር።

ያዕቆብና ቤተሰቡ በግብጽ አገር

28 በጌሤም ምድር እንዲቀበለው ያዕቆብ ይሁዳን ወደ ዮሴፍ አስቀድሞ ላከው፥ እንርሱ ጌሤም በደረሱ ጊዜ፥ 29 ዮሴፍ አባቱን ለመገናኘት በሠረገላው ተቀምጦ ወደዚያ ሄደ፤ በተገናኙም ጊዜ ዮሴፍ በአባቱ አንገት ላይ ተጠምጥሞ ጥሞ ለብዙ ጊዜ አለቀሰ።
30 ያዕቆብ ዮሴፍን "እንግዲህ በሕይወት መኖርህን በዐይኔ አይቼ እረፈጥሁ፤ ብሞት እንኳ ግድ የለኝም" አለው።
31 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹንና የቀረውን የአባቱን ቤተሰብ እንዲህ አላቸው፥ "ወደ ፈርዖን ልሂድና 'ከከነዓን ምድር ይኖሩ የነበሩት ወንድሞቼና የቀሩትም የአባቴ ቤተሰቦች ወደ እኔ መጥተዋል፤ 32 እንርሱ እንስሳትን

46፥6 ፦ ሐሥ. 7፥15። 46፥20 ፦ ዘፍ. 41፥50-52። 46፥27 ፦ ሐሥ. 7፥14።

የማርባት ችሎታ ያላቸው ከብት ጠባቂዎች ናቸው፤ በጎቻቸውንና ፍየሎቻቸውን፥ ከብቶቻቸውን ያላቸውን ንብረት ሁሉ ይዘው መጥተ ዋል' ብዬ ልንገረው። 33እናንተም ፈርዖን አስ ጠርቶ 'የምትተዳደሩበት ሙያችሁ ምንድን ነው?' ብሎ ቢጠይቃችሁ፥ 34'እኛ ልክ እንደ ቀድሞ አባቶቻችን ከልጅነታችን ጀምሮ የምን ተዳደረው ከብት በማርባት ነው' ብላችሁ መል ሱለት። ከብት አርቢዎች በግብጻውያን ዘንድ የተናቁ ስለሆኑ ይህን በመናገር በጌሤም ምድር ለመኖር ፈቃድ ታገኛላችሁ።"

ምዕራፍ 47

1ዮሴፍም ወደ ፈርዖን ሄዶ "አባቴና ወንድ ሞቼ በጎቻቸውንና ፍየሎቻቸውን ከብቶቻቸው ንና ሌላም ያላቸውን ነገር ሁሉ ይዘው ከከነዓን ወደዚህ መጥተዋል፥ አሁንም በጌሤም ምድር ይገኛሉ" አለው። 2ከወንድሞቹ መካከል መርጦ ያመጣቸውንም አምስቱን ወንድሞቹን በፈርዖን ፊት አቀረባቸው።

3ፈርዖንም የዮሴፍን ወንድሞች፡- "የምት ተዳደሩበት የሥራ ሙያችሁ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቃቸው።

እነርሱም እንዲህ ብለው መለሱለት፥ "እኛ አገልጋዮችህ ከብት አርቢዎች ነን፤ አባቶቻች ንም ይተዳደሩበት የነበረ የሥራ ሙያ ይዤው ነበር። 4በከነዓን ምድር ረዘብ እጅግ ከመበር ታቱ የተነሣ ለእንስሳዎቻችን ግጦሽ ስላጣን ለጊ ዜው ብዚህች አገር ለመኖር መጥተናል፤ ስለ ዚህ አገልጋዮችህ በጌሤም ምድር እንድንኖር ፍቀድልን።"

5ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፥

"አባትህና ወንድሞችህ ከመጡልህ፤ 6እነሆ መላው የግብጽ ምድር የአንተ ነው፤ ስለዚህ አባትህና ወንድሞችህ ምርጥ በሆነችው በጌ ሤም ምድር እንዲኖሩ አድርግ። ከእነርሱ መካ ከል ልዩ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ካሉ፥ በእኔ እንስሳት ላይ የበላይ ጎላፊዎች አድርገህ ሹማ ቸው።"

7ከዚህ በኋላ ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ወደ ፈርዖን አቀረበው፤ ያዕቆብም ፈርዖንን ባረ ከው፤ 8ፈርዖንም "ዕድሜህ ስንት ነው?" በማ ለት ያዕቆብን ጠየቀው።

9ያዕቆብም "በመንከራተት ያሳለፍሁአቸው ዘመናት መቶ ሠላሳ ናቸው። እነርሱም የቀ ድሞ አባቶቼ ዘመንከራተት ካሳለፉአቸው ዘመ ናት እጅግ ያነሡና ችግር የበዛባቸው ናቸው" አለ። 10ያዕቆብ ፈርዖንን ባረከውና ተሰናብቶት ወጣ።

11ከዚህ በኋላ ዮሴፍ አባቱና ወንድሞቹ በግ ብጽ ምድር እንዲቀመጡ አደረገ፤ ፈርዖን ባዘ ዘው መሠረት በግብጽ ምድር ምርጥ የሆነ ውን፥ በራምሴ ከተማ አጠገብ ያለውን ቦታ ሰጣቸው። 12ዮሴፍ ለአባቱና ለወንድሞቹ በል ጆቻቸው ቍጥር ልክ እህል ይሰጣቸው ነበር።

የረሀቡ ጽናትና የዮሴፍ አመራር

13ይሁን እንጂ ረሀቡ እየጸና ስለሄደ፥ ከየ ትም አገር እህል ለማግኘት አልተቻለም ነበር፤ የግብጽና የከነዓን ሕዝቦችም በረሀቡ እጅግ ተጐድተው ነበር። 14ስለዚህ የግብጽና የከነዓን ሕዝቦች ወደ ዮሴፍ እየመጡ እህል ሲሸምቱ፥ ዮሴፍ ገንዘቡን ሰብስቦ ወደ ፈርዖን ግምጃ ቤት ያስገባው ነበር። 15በዚህ ሁኔታ የግብጽና የከነ ዓን ሕዝቦች ገንዘባቸውን በእህል ሸመታ ስለጨ ረሱ፥ ግብጻውያን ወደ ዮሴፍ ተሰብስበው መጥ ተው "የምንመገበው እህል ስጠን፤ ምክንያ ቱም ገንዘባችንን ስለጨረስን በረሀብ ማለቃችን ነው" አሉት።

16ዮሴፍም "ገንዘባችሁ ካለቀ ከብቶቻችሁን አምጡና በእነርሱ ለውጥ እህል እሰጣችኋለሁ" አለ። 17እነርሱም ከብቶቻቸውን ወደ ዮሴፍ አመጡ፤ እርሱም በፈረሶቻቸውና በአህዮች ቸው፥ በበጎቻቸውና በፍየሎቻቸው በከብቶቻቸ ውም ለውጥ እህል ሰጣቸው፤ ያንንም ዓመት በሙሉ በከብቶቻቸው ልዋጭ እህል ሰጣቸው።

18በሚቀጥለውም ዓመት ወደ እርሱ መጡና እንዲህ አሉት "ጌታችን ሆይ! ከእንተ የምንሰ ውረው ነገር የለም፤ ገንዘባችን ሁሉ አልቆ አል፤ ከብቶቻችንንም ለአንተ አስረክበናል፤ እንግዲህ ለጌታችን የምንሰጠው ከሰውነታችንና ከመሬታችን በቀር ሌላ ምንም ነገር የለንም። 19እንድ ነገር አድርግልን እንጂ አስከንሞት ዝም ብለህ አትየን፤ እርሻዎቻችን ጠፍ ሆነው እንዲቀሩ አታድርግ፤ እኛንና መሬታችንን ገዝ ተህ እህል ስጠን፤ እኛ የንጉሡ ባሪያዎች እን ሆናለን፤ መሬታችንም የእርሱ ይሁን፤ በልተን በሕይወት እንድንኖር እህል ስጠን፤ በመሬታ ችን ላይ የምንዘራውም ዘር ስጠን።"

20ዮሴፍ በግብጽ ያለውን መሬት ሁሉ ለን ጉሡ ገዛ፤ ከረሀቡ ጽናት የተነሣ ግብጻውያን ሁሉ መሬታቸውን መሸጥ ግድ ሆነባቸው፤ በዚህ ዐይነት መሬት ሁሉ የንጉሡ ንብረት ሆነ። 21ዮሴፍ በግብጽ አገር ዳር እስከ ዳር ያሉት ሰዎች ሁሉ የንጉሡ ባሪያዎች እንዲሆኑ አደረገ። 22ዮሴፍ ያልገዛው የካህናቱን መሬት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ካህናት ከፈርዖን በየጊ ዜው ድርጎ ይቀበሉ ስለነበር መሬታቸውን ለመ ሸጥ አልተገደዱም።

23ዮሴፍ ለሕዝቡ እንዲህ አላቸው፥ "እነሆ፥ እንግዲህ አናንተንና መሬታችሁን ሰፈ ርዖን ስለገዛሁ ዘር ውሰዱና በመሬታችሁ ላይ ዝሩ። 24ነገር ግን በመከር ጊዜ ከምታመርቱት ከአምስት አንዱን እጅ ለፈርዖን መስጠት አለባ ችሁ፤ የቀረው አራት አምስተኛው አጅ ግን

ስመፈታችሁ ዘር ፥ ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ
ለቤተሰባችሁም ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ ።”
25 ሕዝቡም “ጌታችን ሆይ! ሕይወታችንን
ሰላዳንክልንና መልካም ነገር ስላደረግህልን ሁላ
ችንም የፈርዖን ባሪያዎች እንሆናለን” አሉት ።
26 በዚህ ዐይነት ዮሴፍ ከመከር ሁሉ አንድ
አምስተኛው እጅ ለፈርዖን እንዲሰጥ የግብጽን
መሬት ይዞታ በሚመለከት ሕግ አወጣ ፥ ይህም
ሕግ እስከ ዛሬ ድረስ ይሠራበታል ፥ የፈርዖን
ንብረት ያልሆነው የካህናት መሬት ብቻ ነው ።

የያዕቆብ የመጨረሻ ማሳሰቢያ

27 እስራኤላውያን በግብጽ አገር ጌሤም በተ
ባሉ ምድር ይኖሩ ነበር ፥ እዚያም ብዙ ሀብት
አገኙ ፥ ብዙ ልጆችም ወለዱ ።
28 ያዕቆብ ዐሥራ ሰባት ዓመት በግብጽ አገር
ኖረ ፥ ዕድሜውም መቶ አርባ ሰባት ዓመት
ሆኖት ነበር ። 29 ያዕቆብ የሚሞትበት ቀን በተ
ቃረበ ጊዜ ልጁን ዮሴፍን አስጠርቶ እንዲህ
አለው “በፊትህ ሞገስን አግኝቼ ከሆነ ፥ በምሞ
ትበት ጊዜ በግብጽ ምድር እንዳትቀብረኝ እጅ
ህን በጕልበቴ ላይ አኑረህ በመሐላ ቃል ግባ
ልኝ ። 30 አባቶቼ በተቀበሩበት መቃብር መቀ
በር ስለምፈልግ በምሞትበት ጊዜ ከግብጽ አገር
ወስደህ እነርሱ በተቀበሩበት ሰፍራ ቅበረኝ ።”
ዮሴፍም “እሺ እንዳልከኝ አደርጋለሁ”
አለው ።
31 ያዕቆብም “ይህን እንደምታደርግ በመ
ሐላ ቃል ግባልኝ” አለው ። ዮሴፍ ይህንኑ በመ
ሐላ አረጋገጠለት ፥ ያዕቆብም በመኝታው ላይ
እንዳለ በመስገድ እግዚአብሔርን አመሰገነ ።

ምዕራፍ 48

ያዕቆብ ኤፍሬምንና ምናሴን እንደ ልጆቹ አድርጎ በመቀበል ባረካቸው

1 ጥቂት ጊዜ ካለፈ በኋላ “አባትህ ታሞ
አል” ተብሎ ለዮሴፍ ተነገረው ፥ ስለዚህ ዮሴፍ
ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን ይዞ ያዕ
ቆብን ለማየት ሄደ ። 2 ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍ ሊጐ
በኘው መምጣቱን በሰማ ጊዜ ሰውነቱን አበረ
ታቶ በመኝታው ላይ ተቀመጠ ።
3 ያዕቆብ ዮሴፍን እንዲህ አለው ፥ “ሁሉን
የሚችል አምላክ በከነዓን ምድር ሎዛ በምት
ባል ቦታ ተገለጠልኝ ፥ ባረከኝም ፥ 4 ደግሞም
‘ዘርህን አበዛሰሁ ፥ ዝርያዎችህም ብዙ ሕዝቦች
ይሆናሉ ፥ ይህችንም ምድር ከአንተ በኋላ ለሚ
መጡት ዝርያዎችህ ለዘላለም ርስት አድርጌ
እሰጣቸዋለሁ’ አለኝ ።”
5 ያዕቆብ ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ ፥
“ልጄ ዮሴፍ! እኔ እዚህ ከመምጣቴ በፊት በግ
ብጽ ምድር የተወለዱልህ ሁለት ልጆችህ ከእን
ግዲህ የእኔ ልጆች ናቸው ፥ ኤፍሬምና ምናሴ
እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን ይቈጠራሉ ። 6 ከእ
ንግዲህ ወዲህ ሌሎች ልጆች ቢወለዱልህ የአ
ንተ ናቸው ፥ ርስት የሚያገኙትም በኤፍሬምና
በምናሴ ስም በመጠራት ይሆናል ። 7 ከመሰደዴ
ምያ ስመለስ በከነዓን ምድር ገና ከኤፍራታ
ሳልርቅ እናትህ ራሔል ሞተችብኝ ፥ እርስዋን
ወደ ኤፍራታ በሚወስደው መንገድ ዳር
ቀበርኋት ።” (ይህችም ኤፍራታ ዛሬ ቤተል
ሔም ተብላ የምትጠራው ቦታ ነች ።)
8 ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ባየ ጊዜ “እነዚህ
ልጆች እነማን ናቸው?” ብሎ ጠየቀ ።
9 ዮሴፍም “እነዚህ እግዚአብሔር በዚህ
አገር ሳለሁ የሰጠኝ የእኔ ልጆች ናቸው።” ብሎ
አስላቱ መለሰለት ።
ያዕቆብም “እባርካቸው ዘንድ ወደ እኔ አቅር
ብልኝ” አለው ። 10 የያዕቆብ ዐይኖች በእርጅ
ናው ምክንያት ስለደከሙ አዋርቶ ማየት አይች
ልም ነበር ፥ ስለዚህ ዮሴፍ ልጆቹን ወደ እርሱ
አቀረበለት ፥ እርሱም እቅፍ አድርጎ ሳማቸው ።
11 ዮሴፍንም “አንተን እንደገና አያለሁ ብዬ አላ
ሰብሁም ነበር ፥ እግዚአብሔር ግን አንተን ብቻ
ሳይሆን ልጆችህንም ጭምር አሳየኝ” አለው ።
12 ዮሴፍ ልጆቹን ከያዕቆብ ጕልበት ፈቀቅ አደረ
ገና ወደ መሬት ጐንበስ ብሎ ሰገደ ።
13 ዮሴፍ ሁለቱን ልጆቹን ወስዶ ኤፍሬምን
በቀኙ ለያዕቆብ በስተግራው በኩል ፥ ምናሴን
በግራው ለያዕቆብ በስተቀኝ በኩል አድርጎ አቀ
ረበለት ። 14 ያዕቆብ ግን እጆቹን በማመሳቀል
አስተላልፎ ቀኝ እጁን በታናሹ በኤፍሬም ራስ
ላይ ፥ ግራ እጁን በበኵሩ በምናሴ ራስ ላይ
አኖረ ።
15 “ከዚህ በኋላ ዮሴፍን እንዲህ ሲል
ባረከው ፥
አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ መንገዱን
በመከተል ያገለገሉትና
እኔንም ሕይወቴን ሙሉ እስከ ዛሬ
ድረስ አርኖ ሆኖ የጠበቀኝ
አምላክ እነዚህን ልጆች ይባርክ ።
16 እኔን ከጕዳት ሁሉ የጠበቀኝ መልአክ
እነርሱንም ይጠብቃቸው ።
የእኔ ስም ፥ የአባቶቼም የአብርሃምና
የይስሐቅ ስም በነዚህ ልጆች ሲታወስ
ይኑር ፤
ዘራቸውም በምድር ላይ ይብዛ ።”
17 ዮሴፍ አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ
ማድረጉን ባየ ጊዜ ቅር ተሰኘ ፥ ስለዚህ ከኤፍ
ሬም ራስ ላይ እንሥቶ በምናሴ ራስ ላይ ሰማ
ኖር የአባቱን እጅ ያዘና ፥ 18 “አባቴ ሆይ! እን
ደዚህ አይደለም ፥ በኵሩ ይህኛው ስለሆነ ቀኝ
እጅህን በእርሱ ራስ ላይ አኑር” አለው ።

47፥29-30 ፡- ዘፍ. 49፥29-32 ፤ 50፥6 ። 48፥3-4 ፡- ዘፍ. 28፥13-14 ። 48፥7 ፡- ዘፍ. 35፥16-19 ።

19 አባቱ ግን "ዐውቁእለሰው ፥ ልጂ ዐውቁእ
ለሰ ፥ የምናሴም ዘር ታላቅ ሕዝብ ይሆናል ፥
ይሁን እንጂ የእርሱ ታናሽ ወንድም ከእርሱ
ይበልጥ ታላቅ ይሆናል ፥ ዝርያዎቹም ታላላቅ
ሕዝቦች ይሆናሉ" ብሎ እምቢ አለ ። 20 ስለዚህ
በዚያን ቀን እንዲህ ሲል ባረካቸው ፥ "እስራኤ
ላውያን በሚመርቁበት ጊዜ የእናንተን ስም
በማስታወስ

'እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደ
ምናሴ ያድርጋችሁ' ይላሉ ።"

በዚህ አኳኋን ያዕቆብ ኤፍሬምን ከምናሴ አስቀ
ደመው ።

21 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ዮሴፍን እንዲህ
አለው ፥ "እነሆ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦ
አል ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር
ነው ፥ ወደ ቀድሞ አባቶቻችሁም ምድር ይመ
ልሳችኋል ፥ 22 በሰይፌና በቀስቴ ከአሞራውያን
እጅ የወሰድሁትን ለሙን ምድር ሴኬምን ፥
ከወንድሞችህ ጋር ከምታገኘው ድርሻ በላይ
ለአንተ ብቻ ስጥቼሃለሁ ።"

ምዕራፍ 49

ያዕቆብ ልጆቹን ሲመርቅ የተናገረው ቃል

1 ያዕቆብ ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥
"በእንድነት ተሰብሰቡና ወደ ፊት የሚደርሳች
ሁን ነገር ልንገራችሁ ፥

2 "እናንተ የያዕቆብ ልጆች ፥
በእንድነት ተሰብሰባችሁ ስሙ ፤
አባታችሁ እስራኤል የሚነግራችሁንም
አድምጡ ።

3 "ሮቤል ፥ ኀይልና የኰልማሳነት ብርታት
በነበረኝ ጊዜ
የወለድሁህ የበኵር ልጂ ነህ ።
ከልጆቼ ሁሉ በክብርና በኀይል
የምትበልጥ አንተ ነህ ።
4 ይሁን እንጂ እንደ ውሃ የምትዋልል
ስለሆንክ ፥
የበላይ አለቅነት ለአንተ አይገባም ፤
ምክንያቱም ከቁባቴ ጋር ተኝተሃል ፤
የአባትህንም መኝታ አርክሰሃል ።

5 "ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው ፤
ዐመፅ ለመፈጸም የጦር መሣሪያቸውን
ያነሣሉ ።
6 እነርሱ በቅጣታቸው ብዙ ወንዶችን
ስለገደሉ ፥
ከንቱ ምኞታቸውን ለማርካት ብዙ
ኮርማዎችን ስለሰባበሩ ፥
በእነርሱ ምክር አልገባም ፤
የጉባኤውም ተካፋይ አልሆንም ።
7 እጅግ አስፈሪ የሆነ ቍጣቸው ፥
እጅግ ጨካኝ የሆነ መዓታቸው ፥
የተረገመ ይሁን ።
በእስራኤል ምድር ሁሉ
እበታትናቸዋለሁ ፤
በሕዝቡም መካከል እከፋፍላቸዋለሁ ።

8 "ይሁዳ ፤ ወንድሞችህ ያመሰግኑሃል ፤
እጅህ በጠላቶችህ አንገት ላይ
ይበረታል ፥
ወንድሞችህ በፊትህ ራሳቸውን
ዝቅ አድርገው አጅ ይነሡሃል ።
9 ይሁዳ እንደ ደቦል አንበሳ ነው ፤
ልጂ መብል የሚሆነውን አድኖ ፥
ወደ ዋሻው ይመለሳል ፤
እንደ አንበሳ ተዝናንቶ ይተኛል ፤
ሊቀሰቅሰው የሚደፍር አይገኝም ።
10 'ሴሎ' ተብሎ የሚጠራው ፥ ሕዝቦች
ሁሉ የሚታዘዙለትና
ለዘላለም የሚነግሠው እስኪመጣ
ድረስ ፥
በትረ መንግሥት (የገዥነት ሥልጣን)
ከይሁዳ እጅ አይወጣም ።
11 አህያውን በወይን ግንድ ላይ ፥
ውርንጫውን በወይን ሐረግ ላይ
ያስራል ፤
ልብሱን በወይን ጠጅ ፥
መጐናጸፊያውን እንደ ደም በቀላ
የወይን ጭማቂ ያጥባል ።
12 ዐይኖቹ ከወይን ጠጅ ይልቅ ይቀላሉ ፤
ጥርሶቹ ከወተት ይልቅ ይነጣሉ ።

13 "ዛብሎን በባሕር ዳር ይኖራል ፤
ወደቡም የመርከቦች ማረፊያ
ይሆናል ፤
የመኖሪያውም ወሰን እስከ ሲዶና
ይደርሳል ።

14 "ይሳኮር በጭነት መደላደል መካከል
እንደሚተኛ ብርቱ ልማኛ አህያ
ነው ።
15 ነገር ግን ማረፊያው መልክም
ምድሩም አስደሳች መሆኑን ባየ ጊዜ ፥
ጭነቱን ለመሸከም ትከሻውን ዝቅ
ያደርጋል ፤
እንደ አገልጋይ ሆኖም ከባድ
የጕልበት ሥራ ይሠራል ።

16 "ዳን ፥ ከእስራኤል ነገዶች አንዱ ለሆነው
ሕዝቡ ፈራጅ ይሆናል ።

48:20 ፦ ዕብ. 11:21 ። 49:9 ፦ ዘኍ. 24:9 ፤ ራእ. 5:5 ።

17 ዳን እንደ መንገድ ዳር አባብ ይሆናል ፣
ፈረሰኛውን ከፈረሰ ላይ ለመጣል
በሰላች መንገድ ላይ አድብቶ
የፈረሱን ቍርጭምጭሚት እንደሚነድፍ
መርዘኛ እባብ ይሆናል ።

18 “እግዚአብሔር ሆይ!
አዳኝነትህን እጠባበቃለሁ ።

19 “ጋድን ቀማኞች ያጠቁታል ፣
እርሱም ዱካቸውን በመከተል
መልሶ ያሳድዳቸዋል ።

20 “አሴር ከምድሩ ብዙ ሀብት አግኝቶ
ይበለጽጋል ፣
በነገሥታት ፊት መቅረብ የሚችል
ጥሩ ምግብ ያዘጋጃል ።

21 “ንፍታሌም በነፃነት እየተዘዋወረች
እንደምትኖር ፣
ደስ የሚያሰኙ ግልገሎችን
እንደምትወልድ
ሚዳቋ ነው ።

22 “ዮሴፍ ፣ በውሃ ምንጭ አጠገብ ተተክሎ
ሐረጎቹ በግድግዳ ላይ እንደሚዘረጉ
ፍሬያማ ዛፍ ነው ።
23 ቀስተኞቹ በብርቱ ያጠቁታል ፣
በቀስታቸውም እየነደፉ ያሳድዱታል ።
24 ነገር ግን ብርቱ ዘሆነ በያዕቆብ አምላክ
ኀይል ፣
በእሰራኤል እረኛና ጠባቂ ብርታት ፣
የእርሱ ቀስት ጽኑ ይሆናል ፤
ክንዱም ይበረታል ።
25 የአባትህ አምላክ ይረዳሃል ፣
ሁሉን የሚችል አምላክ ከላይ ከሰማይ
ዝናምን ፣
ከምድርም ጥልቀት ውሃን በመስጠት
ይባርክሃል ፤
ብዙ ከብትና ብዙ ልጆችም
ይሰጥሃል ።
26 ከጥንት ጀምሮ ጸንተው ከሚኖሩት
ተራራዎችና ዘላለማውያን ከሆኑት
ኮረብታዎችም
ከሚገኘው ደስ ከሚያሰኝ ስጦታ ሁሉ
የአባትህ በረከት ይበልጣል ።
እንግዲህ ይህ ሁሉ በረከት በዮሴፍ ራስ
ላይ ይሁን ፤
በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነውም
በዮሴፍ እናት ላይ ይውረድ ።

27 “ብንያም እንደ ነጣቂ ተኵላ ነው ፣
በማለዳ ያደነውን ራሱ ይበላል ፣
በምሽት ያደነውን ግን ያካፍላል ።”

28 እንግዲህ እነዚህ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው ፤ አባታቸው በባረካቸው ጊዜ ለእያንዳንዱ ተስማሚ የሆነውን የበረከት ቃል የተናገረው በዚህ ሁኔታ ነበር ።

የያዕቆብ መሞትና መቀበር

29 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልጆቹን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው ፤ “እኔ በሞት ወደ ወገኖቼ የምሄድ በት ጊዜ ደርሶአል ፤ ስለዚህ በሒታዊው በዔፍሮን እርሻ ላይ ባለው ዋሻ ውስጥ ከአባቶቼ ጋር ቅበሩኝ ፤ 30 ይህም ዋሻ በከነዓን ምድር ከመ ምሬ በስተምሥራቅ በኩል በማክፌላ የሚገኘው ነው ፤ አብርሃም ይህ ዋሻ የሚገኝበትን እርሻ ለመቃብር ቦታ የገባው ከሒታዊው ከዔፍሮን ነው ። 31 አብርሃምና ሚስቱ ሣራ ፣ ይስሐቅና ሚስቱም ርብቃ የተቀበሩት እዚያ ነው ፤ እኔም ልያን የቀበርኋት እዚያው ነው ። 32 እርሻውና ዋሻው በእንድነት የተገዙት ከሒታውያን ነው ፤ ስለዚህ እኔንም እዚያው ቅበሩኝ ።”

33 ያዕቆብ ለልጆቹ ትእዛዝ መስጠቱን ካበቃ በኋላ ፣ እግሮቹን በመኝታው ላይ ሰብሰብ አድርጎ ጋደም እንዳለ በሞት ወደ ወገኖቹ ሄደ ።

ምዕራፍ 50

1 ዮሴፍ በአባቱ ራሳ ላይ ወደቀና ፊቱን እየ
ሳመ እሰቀሰ ። 2 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ አገልጋዮቹ
የሆኑትን መድኀኒት ቀማሚዎች የአባቱን ራሳ
መልካም መዓዛ ባለው ሽቶ እያሹ እንዲያደር
ቁት ትእዛዝ ሰጠ ። 3 መድኀኒት ቀማሚዎቹም
በሀገሩ ልማድ መሠረት ሬሳውን ለማድረቅ
አርባ ቀን ፈጀባቸው ። ግብፃውያን ሰባ ቀን
ሙሉ አለቀሱለት ።

4 የሰቅሶው ወራት በተፈጸመ ጊዜ ዮሴፍ የፈ
ርዖንን ባለ ሥልጣኖች እንዲህ አላቸው ፦
“መልካም ፈቃዳችሁ ቢሆን እባካችሁ ለፈር
ዖን ፣ 5 ‘አባቴ ለመሞት ሲቃረብ በከነዓን
ምድር ባዘጋጀው መቃብር እንድቀብረው በመ
ሐላ ቃል አስገብቶኛል ፤ ስለዚህ እዚያ ሄጀ
አባቴን ቀብሬ እንድመለስ ይፈቀድልኝ ሲል
ጠይቆአል’ ብላችሁ ንገሩልኝ” አላቸው ።

6 ፈርዖንም ይህን ሰምቶ “ቃል በገባህለት
መሠረት ሄደህ አባትህን ቅበር” አለው ።

7 ስለዚህ ዮሴፍ አባቱን ለመቅበር ሄደ ፤ የፈር
ዖን ባለሥልጣኖችና በቤተ መንግሥቱ የሚገኙ
ታላላቅ ሰዎች ፣ ሌሎችም የግብጽ መኳንንት
ዮሴፍን ተከትለው ሄዱ ። 8 እንዲሁም የዮሴፍ

49:30 ፦ ዘፍ. 23:3-20 ። 49:31 ፦ ዘፍ. 25:9-10 ፣ 35:29 ። 49:33 ፦ ሐ.ሥ. 7:15 ። 50:5 ፦ ዘፍ. 47:29-31 ።

ቤተሰቦች ፥ ወንድሞቹና ሌሎችም የአባቱ ቤተሰቦች ሁሉ ከዮሴፍ ጋር ጌዴ ፥ በጌሜም የቀሩት ሕፃናት ልጆቻቸው ፥ በጎቻቸው ፥ ፍየሎቻቸውና ከብቶቻቸው ብቻ ነበሩ ። 9 ባለ ሠረገላዎችና ፈረሰኞች ተከትሰውት ወጡ ፥ በጠቅላላው የተከተሰው አጀብ እጅግ ብዙ ነበር ።

10 ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ "አጣድ" ተብላ ወደምትጠራው አውድማ ደረሱ ፥ እዚያም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመጮኽ አለቀሱ ፥ ዮሴፍም እዚያ ስባት ቀን ሙሉ የሐዘን ውሎ አደረገ ። 11 በዚያ የሚኖሩ ከነዓናውያን በአጣድ አውድማ ለቅሶውን ባዩ ጊዜ "ይህ የግብጻውያን ለቅሶ እንዴት መሪር ነው?" አሉ ። በዚህ ምክንያት በዮርዳኖስ ሜዳ ያለው የዚያ ቦታ ስም "አቤል ምጽራይም" ተባለ ፥ ትርጉሙም በዕብራይስጥ "የግብጻውያን ለቅሶ" ማለት ነው ።

12 በዚህ ሁኔታ የያዕቆብ ልጆች አባታቸው እንዳዘዛቸው አደረጉ ፥ 13 አስከሬኑን ወደ ከነዓን ወስደው ከመምሬ በስተምሥራቅ በምትገኘው በማክጴላ ዋሻ ቀበሩት ፥ ይህም ዋሻ አብርሃም ለመቃብር ቦታ እንዲሆን ከሒታዊው ከኤፍሮን በገዛው እርሻ ውስጥ የሚገኝ ነው ። 14 ዮሴፍ አባቱን ከቀበረ በኋላ ከወንድሞቹና ስቀብር አጅበውት ከሄዱት ሰዎች ሁሉ ጋር ሆኖ ወደ ግብጽ ተመለሰ ።

ዮሴፍ ወንድሞቹን አረጋጋ

15 አባታቸው ከሞተ ባኋላ የዮሴፍ ወንድሞች "ምናልባት ዮሴፍ ቢማላንና ስሳደረስን በት በደል ሁሉ ሊበቀልን ቢፈልግ ምን እንሆና ለን?" ተባባሉ ። 16 ስለዚህ እንዲህ የሚል መል እክት ወደ ዮሴፍ ላኩ ፥ "አባትህ ከመሞቱ በፊት ፥ 17 'ወንድሞችህ በበደሉህ ጊዜ ያደረሱ ብህን ጉዳት ሁሉ አትቍጠርባቸው ብሎሃል' ብለን እንድንነግርህ አዝዞናል ፤ ስለዚህ እኛ የአ ባትህ አምላክ አገልጋዮች ያደረስንብህን በደል ሁሉ ይቅር እንድትለን እንለምንሃለን ።" ዮሴፍ ይህን በሰማ ጊዜ አለቀሰ ።

18 ከዚህ በኋላ ወንድሞቹ ራሳቸው በፊቱ ቀርበው ጕንበስ ብለው እጅ ነሡና "እነሆ እኛ ሁሳችን አገልጋዮችህ ነን" አሉት ።

19 ነገር ግን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው ፥ "አይ ዞአችሁ አትፍሩ ፤ እኔ እኮ በእግዚአብሔር ምትክ የምሆን አይደለሁም ፤ 20 በእርግጥ አና ንተ ክፉ ነገር መክራችሁብኝ ነበር ፤ እግዚአብ ሔር ግን ወደ መልካም ነገር ለመጠው ፥ ያዘን ንም ያደረገው አሁን በሕይወት ያሉትን የብዙ ሰዎች ሕይወት ለማትረፍ ብሎ ነው ። 21 ምንም የሚያስፈራችሁ ነገር የለም ፤ እኔ እና ንተንና ልጆቻችሁን እመግባችኋለሁ ።"

በዚህም ዐይነት መልካም ንግግር በማጽና ናት አረጋጋቸው ።

የዮሴፍ መሞት

22 ዮሴፍ ከአባቱ ቤተሰቦች ጋር በግብጽ ተቀመጠ ፥ ከዚያም ዕድሜው መቶ ዐሥር ዓመት እስኪሆነው ኖረ ፤ 23 የኤፍሬምንም ልጆ ችና የልጅ ልጆች እስኪሚያይ ድረስ ቆየ ፥ ከም ናሴ የተወለዱንም የማኪርንም ልጆች እንደ ልጆቹ አድርጎ ተቀበላቸው ።

24 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው ፥ "እነሆ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃር ቧአል ፤ እናንተን ግን እግዚአብሔር በረድኤት ይጐበኛችኋል ፥ ከዚህም አገር አውጥቶ ለአብር ሃም ፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ለመስጠት በመሐላ ቃል ወደ ገባላቸው ምድር ይመልሳችኋል ።
25 እግዚአብሔር በሚጐበኛችሁና ወደዚያች ምድር በሚመልሳችሁ ጊዜ አፅሜን ከዚህ ይዛ ችሁ የምትወጡ መሆናችሁን በማረጋገጥ ቃል ግቡልኝ" ብሎ አስማላቸው ።

26 ዮሴፍም ዕድሜው መቶ ዐሥር ዓመት ሲሞላው ሞተ ፤ አስክሬኑንም በሽቶ አሽተው በማድረቅ በግብጽ ምድር በሣጥን ውስጥ አኖ ሩት ።

50፡13 ፦ ሐሥ. 7፡16 ። 50፡25 ፦ ዘጽ. 13፡19 ፤ ኢያሱ 24፡32 ፤ ዕብ. 11፡22 ።